
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ጥር/የካቲት ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.



## እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ !!

በቤተልሔም የሚገኘው ጌታችን የተወለደበት ዋሻ
(የኮከቡ ምልክት ሰብአ ሰገልን የመራው ኮከብ የቆመበት ቦታ ነው።)



www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## በከተማው ዳርቻ ላይ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትንም ብናስታውሳቸው

ታኅሣሥ ሦስት ቀን 1997 ዓ.ም የተከበረውን የመልአኩ ቅዱስ ሩፋኤልንና የበአታ ለማርያም ክብረ በዓል በረከት ለመሳተፍ ወደ መሪ ደብረ ታቦር ቅዱስ ሩፋኤል አብርሃ ወአጽብሓ ቤተ ክርስቲያን ተጉዤ ነበር። ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ የካቲት 8 ቀን 1993 ዓ.ም የተመሠረተ ነው። ካሉበት ዋነኛ ችግሮች አንዱ «በአያት» የመኖሪያ መንደር የሚገኙ ነዋሪዎች ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚሄዱበት መንገድ መከልከላቸው መሆኑ በዕለቱ ተጠቅሷል። ቤተ ክርስቲያኑ በከተማው ዳር ላይ የሚገኝ በመሆኑ በአጥቢያው ነዋሪዎ እምብዛም አይገኙም። እንዲያውም በዕለቱ እንደ ተገለጸው የጥበቃ ሠራተኞቹ ደመወዛቸውን በየወሩ አያገኙም፤ በክብረ በዓሉ ዕለት በተሰበሰበ መብዓና ምጽዋት ብቻ ዓመት ለመጠበቅ ይገደዳሉ። በእውነቱ በዓመታዊ ክብረ በዓል ይቅርና በወር በዓል እንኳን በሺ እና ከዚያም በላይ የሚቆጠር ገንዘብ በሚሰበሰብበት አዲስ አበባ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ገቢ የሚያገኝ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መኖሩ በእጅጉ አሳዝኖኛል። ስለሆነም «በአያት መንደር» የሚገኙ ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚሄዱበት አመቺ መንገድ እንዲፈቀድላቸው፣ በመዲናይቱ በአጠቃላይ የምንገኘውም በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን መብዓ ይዘን ብንጎበኛቸው መልካም ነው። በዚህ አጋጣሚ በክብረ በዓሉ ተገኝተው አገልግሎት የሰጡትን የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰንበት ት/ቤት አባላትን አርአያነት ሌሎችም እንዲከተሉት እያስታወስኩ ከፍ ያለ ምስጋናዬን ላቀርብላቸው እወዳለሁ።

*ደመላሽ አሰፋ*
*6 ኪሎ - አ.አ*

## «ብዙ ሰዎች ጠፍተዋል÷ እየጠፉም ነው»

ከግምቢ 25 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እንገኛለን። አጥቢያችንም ሆማ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ይባላል። አገልጋይ ካህናትና ዲያቆናት እንዲሁም የሰንበት ት/ቤት መዘምራን አሉት። ሆኖም ግን በትምህርተ ወንጌልና በስብከተ ወንጌል ረገድ ምንም ነገር የለም ማለት ይቻላል። በአሁኑ ሰዓት ብዙ ሰዎች «ጠፍተዋል፤ እየጠፉም ነው።» በእውነቱ በመዝሙር አገልግሎት ያለነ ውም የመዝሙር ምንነት ስላልገባን፣ ስላልተማርን፣ የሚያስተምረንም ስለ ጠፋ፣ ዘፈኑ መዝሙር የሚመስለን፤ አንዴ የምንዘምር ሌላ ጊዜ ደግሞ ጨርሶ የምንተወው ሆነናል። ከትምህርተ ቤተ ክርስቲያንም ባዶ ስለሆንን በመናፍቃን ተውጠናል፤ ተበልተናል፤ እየተበላንም ነው። ስለዚህ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በወርቀ ደሙ የዋጀው ምእመን ደም በእጃችሁ መሆኑን ተረድታችሁ ስለሆማ መድኃኔ ዓለም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ችግር ብታስቡ፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ብታዘክሩልን ምን አለበት?

*ነቢዩ ተስፋዬ*
*ምዕ.ወለጋ - ሆማ ከተማ*

## ሓላፊነትን በታማኝነት

በርካታ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች መንግሥታዊ በኾኑና መንግሥታዊ ባልኾኑ ድርጅቶች ተቀጥረን፣ በየደረጃው በተለያዩ የሓላፊነት ቦታዎች ላይ ተቀምጠን ሕዝብንና መንግሥትን እንዲሁም ራሳችንን እናገለግላለን። በሥራ ገበታችን ላይ የተጣለብንን ሓላፊነት በታማኝነት እንድንፈጽም ከአደራ ጭምር የተሰጠን መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና ብዙዎቻችን ታማኞች ነን ለማለት እቸገራለሁ። በተለይ እኔ እስከ ማውቀው ድረስ ይኼ ችግር በጽሕፈት መሣሪያዎችና በስልክ አጠቃቀም ላይ ጐልቶ ይታያል። በሥራ ቀናት የሚፈጸመውን ብልሹ ተግባር ትተን ሥራ በማይኖርባቸው ቅዳሜና እሑድ እንኳን በቤታችን ስልክ እያለን ቢሮ ገብተው በመንግሥት ስልክ የግል ጉዳያችንን የምናስፈጽም ጥቂቶች አይደለንም። «በራስህ ላይ ሊደረግብህ የማትሻውን በሌ ላው ወንድምህ ላይ አትፈጽም» የሚለውን የወንጌል ቃል እንዘነጋለን። በመሆኑም ሰው ባያየን እግዚአብሔር ያየናል፤ ብለን በታማኝነት ሓላፊነታችንን እንወጣ። በሥጋም በነፍስም ከመኮነን እንዳን።

*አድነው በርጋ*
*መቐለ ዩኒቨርስቲ*

## ልክና መጠን ይኑረው

በቤተ ክርስቲያናችን በተለይም በክብረ በዓላት በአንዳንድ አጥቢያዎች ታቦታት ከመንበራቸው ወጥተው፣ ዑደት አድርገው በዐውደ ምሕረቱ ከቆሙ በኋላ ለሕንፃ ቤተ ርስቲያን ማሠሪያ፣ ለዚህ ማስጀመሪያ፣ ለዚያ ማስጨረሻ እየተባሉ የሚካሄዱ ቅስቀሳዎች የሚያስመርሩ ሆነዋል። ሥራዎቹ እስከ ታመነባቸው ድረስ በራሳቸው ተገቢ ቢሆኑም ለስብከተ ወንጌልና ለትምህርተ ወንጌል የሚሰጠውን ጊዜ ግን በመተካት /በመሻማት/ መሆን የለበትም። በተለይ ዕለቱ ቅዳሜና እሑድ ሲሆን ደግሞ ከረፋድ በኋላ ምእመኑ የሚኖርበትን ማኅበራዊ ግዴታዎች የሚዘነጋ፣ የአረጋውያንን ዐቅም፣ ከምግብ ጋር የተያያዘውን የሕሙማንን ጤንነት ግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ በአጠቃላይ ካህናቱንም ይሁን ምእመናኑን ለአሰልቺና አድካሚ ሁኔታ ማጋለጥ የለበትም። በጊዜ አጠቃቀማችንም ለገማቾችና ለተቺዎች በር መክፈት አይኖርበትም። ሁሉም ነገር ልክና መጠን ይኑረው።

*መ/ር ይስማው ሀገር*
*-አ.አ*

## ቤተ ክርስቲያን ከኤምባሲ በላይ ነች

በአገራችንም ይሁን በዓለም ዙሪያ በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈጠሩ አለመግባባቶች ሳቢያ ግጭቶች ሲከሰቱ ከሚደርስባቸው እንግልትና ስቃይ ለመዳን ቅጽረ ቤተ ክርስቲያንን መማፀኛ አድርገው የሚጠለሉባት ወገኖች እንዳሉ ይታወቃል። በዚህ ረገድ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን የተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ይጠቀሳሉ። ይሁንና የተማሪዎቹ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን የመጠለል መብትና በታሪክ የሚታወቀው የቤተ ክርስቲያናችን መጠለያ /መማፀኛ/ የመስጠት ሥልጣን (Right of Asylum) ሲከበር አይታይም። በመሆኑም በየትኛውም ደረጃ የሚገኘው የመንግሥት አካል ይህን የምእመናን መብትና የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ካለወቀ ሊማር፣ ካወቀም ሊያከብር ይገ ባዋል። ቤተ ክርስቲያን ከምድራውያን መንግሥታት ኤምባሲዎች በላይ ናትና።

*ወለተ ብርሃን፣ ወለተ ሃና፣ወለተ ሥላሴ*
*መቐለ ዩኒቨርስቲ*



| የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለባለው ታደለ እና/ወይም መስፍን ጥላሁን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ
Balew Tadelle and/or Mesfin Tilahun
የባንክ ሒሳብ ቁጥር 68608 አዲስ አበባ ከፍለው
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ

አንዳንድ ወጣቶች «አባቴና እናቴ ማግባቴን ባያውቁ ምን አለበት? የንስሐ አባቴ ባያውቁት ምን አለበት?» ይላሉ። ነገር ግን ለመንፈሳዊ አባትና ለቤተሰብ ተናግረን ቤተሰብም እንደ ቤተሰብነቱ መንፈሳዊ አባትም እንደ ሃይማኖታችን ሥርዓት ጸልየውልን መሸኘት ለበረከት ያበቃናልና ችላ ልንለው አይገባም። የሠርግ ድንኳን ዘወትር የሐዘን እንጉርጉሮ ይደመጥበት ነበር። ምክንያቱም የቤቱ እመቤት ሣራ ዐረፍተ ዘመን ወስኗታል።

## በረከተ ወንጌል

እንደ የደረጃቸው ቤተ ክርስቲያኗ በሰጠቻቸው ሥልጣንና መዓርግ ረዘም ላሉ ዓመታት አገልግሎት ሲፈጽሙ የቆዩት አበው ወደ አካባቢው መሄድ በመካከሉ የነበረውን አንድነት ጠብቆ የቆየውን ምእመን ለመከፋፈሉ ምክንያቱ ደግሞ የእነዚህ አባቶች "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ከእኛው ጋር ተሰዶ ወደ አሜሪካ መጥቷል" ብለው በይፋ ማወጃቸው ነበር። ይህ የተሳሳተ ዐዋጅ፤ ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ በተነሣው የኢትዮጵያውያን በቋንቋና በጐሳ መለያየት ችግር ጋር ተዳምሮ በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ ቅድስት ቤተ ክርስቲያኑን የማንነቱ መገለጫ አድርጐ በሰላምና በፍቅር ይኖር የነበረውን ምእመን ወዳልተገባ ውዥንብርና መከፋፈል ከተተው።

## ወቅታዊ ጉዳዮች

አንድ ክርስቲያን በተጋድሎ እንዲጸና፣ ሓላፊነቱን እንዲወጣ፣ ከኃጢአት እንዲጠበቅ ለቤተ ክርስቲያን እንዲቀናና እንዲተጋ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አንዱ ዓላማ ነው። ቅዱስ ዳዊትን ወደ ቤቱ ድንኳን እንዳይገባ፣ ወደ አልጋውም እንዳይወጣ፣ ለዐይኖቹ መኝታ፣ ለሽፋሽፍቶቹም እንቅልፍ፣ ለጉንጮቹም ዕረፍትን ከመስጠት እንዲከለከል ያደረገው ለእግዚአብሔር ስፍራ፣ ለያዕቆብ አምላክ ማደርያ ለማግኘት የነበረው ዓላማ ነው።

## ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ


ዋና አዘጋጅ - ዲ.ን መርሻ አለኸኝ
ም/ዋና አዘጋጅ - አሉላ ጥላሁን
ከፍተኛ ሪፖርተር - መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው
መ/ ሪፖርተር - ዲ.ን ፋሲል አስረስ
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊዎች - ፍቅርተ ኃይሌ
- ጸዳሉ ሁንዴሳ



ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ

E -mail:Hamer@EOTC-Mkidusan.org
Website: – www.EOTC-Mkidusan.org


**«ማኅበረ ቅዱሳን»**

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል።


ሐመር
፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩
ጥር/የካቲት ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.


## ይዘት


*የማኅበሩ መልእክት*
- ትምህርተ ወንጌል ለሁሉም ........ ፪

*ደብዳቤዎች* ........ ፬

*ከሰሞኑ በረከት*
- ዘመነ መርዓዊ /የሙሽራ ዘመን/ ........ ፮

*ትምህርተ ሃይማኖት*
- ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም ........ ፱
- የጥምቀት ንባብ በአባ ጊዮርጊስ ........ ፲፩

*የጥያቄዎቻችሁ መልስ*
- ተአምረ ማርያም ........ ፲፫

*ኪነ ጥበብ*
- አስቂኝ ማርያም ........ ፲፮

*እናስተዋውቃችሁ*
- በማኅበረ ቅዱሳን የተጠኑ፥ የተተገበሩና በመተግበር ላይ የሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶች ........ ፲፰
- አቡነ ዘዮሐንስ ዘከብራን ........ ፳፩

*ዓምደ ወራዙት*
- ጋብቻ እና የሰርግ ወጪ ........ ፳፫

*ሐመረ ሕይወት*
- የጠባይ ለውጥ እንዴት ........ ፳፭

*ቃለ መጠይቅ*
- እነዚህ ድርጅቶች ሕዝቡን ለመሳብ ልዩ ልዩ ማታለያዎችንና ........ ፳፯

*ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ*
- ቸልተኝነት? ........ ፳፱

*ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ*
- የክርስትና ስም ........ ፴፩
- የሥርዓት መፈጸሚያ ........ ፴፬

*ወቅታዊ ጉዳዮች*
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ ........ ፴፭

*አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት*
- አያያዥ ........ ፴፰
- «በእውነቱ ለጥንታውያኑ መዛግብቶቻችን ........ ፵



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

ይህንን ዐቢይ አገልግሎት ለመፈጸም የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል።

1. የቤተ ክርስቲያን አካላት ለስብከተ ወንጌል ልዩ ትኩረት መስጠት፡- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን ለማፋጠን ያመቻት ዘንድ ከቅዱስ ሲኖዶስ ጀምሮ በተዋረድ እስከ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ድረስ የተዋቀሩ ልዩ ልዩ አካላት አሏት። እነዚህ አካላት በየራሳቸው እንዲያከናውኑ የሚጠበቅባቸው ተግባራት አሏቸው። የሁሉም የጋራ ዓላማ ግን ምእመናን በትምህርተ ወንጌል ታንጸው፣ በክርስቲያናዊ ሕይወት ኖረው፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲወርሱ ማድረግ ነው። ስለዚህ ሁሉም አካላት ምእመኑ ከመደበኛ ዓመታዊ የሰበካ ጉባኤ አስተዋጽአውና አሥራት በኩራቱ ባለፈ ከዕለት ጉርሱ ቀንሶ ለቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ አገልግሎት በሚል እንዲያወጣ ከሚያደርጉት በተጨማሪ ለክርስቲያናዊ ሕይወቱ መሠረት ለሆነው ትምህርተ ወንጌል ልዩ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል።

2. ጠንካራ የስብከተ ወንጌል ቅንጅትና አሠራር መፍጠር፡- በአሁኑ ወቅት ቀደም ሲል በወረት ተጀምረው የነበሩ የዐውደ ምሕረት ጉባኤያት በአብዛኛው ተዳክመው ይገኛሉ። የዚህ ምክንያቱም በዚያ ወቅት አጠናክረው የጀመሩት አጥቢያዎች በአካባቢያቸው ሲደረግ ስላዩ «እኛ ለምን እናንሳለን?» በሚል ስለነበረ፣ በወቅቱ ባለ በሌለ ዐቅማቸው ከጉባኤ ጉባኤ እየተዘዋወሩ ሲያስተምሩ የነበሩት ያንን እንደ አንድ ወቅት ፋሽን ስላዩት ነበር ማለት ይቻላል። ያኔ ዐውደ ምሕረቶቻቸውን በሰርክ ጉባኤያት ተካፋይ ምእመናን አጨናንቀውት የነበሩ በርካታ አጥቢያዎች ዛሬ በሮቻቸውን ለሰርክ ተሰላሚ ምእመናን ክፍት ከማድረግ ያለፈ ቃለ እግዚአብሔርን አያስተምሩም። ቢያስተምሩም ደንቡ እንዳይቀር ያኽል ነው። ያኔ ትጉኃን የነበሩ መምህራን ዛሬ ትተውታል። አልፎ አልፎ ቢያስተምሩም በከፍተኛ ጉትጎታ ነው። በተመሳሳይ ቀደም ሲሉ ተጀምረው የነበሩ የስብከተ ወንጌል እንቅስቃሴዎች ተዳክመዋል። በጥቂት የሰው ኃይልና የገንዘብ ወጪ ቃለ እግዚአብሔርን በሰፊው በማዳረስ ከፍተኛ ሚና ይጫወቱ የነበሩ ኅትመቶች ዛሬ የሉም። ያሉትም ቢሆኑ ትኩረታቸውን ቃለ እግዚአብሔር ከማድረግ ይልቅ እዚህም እዚያም በሚፈጸሙ ተግባራት ሪፖርት ላይ ካደረጉ ቆይተዋል።

ስለዚህ አባቶቻችን በቃል ስብከትም ሆነ በጽሑፍ ምእመናንን እያስተማሩ ቅድስት ቤተ ክርስ ቲያናችንን ከነሙሉ ክብሯና ማንነቷ እንዳስረከቡን ሁሉ፤ ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት የሚያግዙ ሁነኛ የቤተ ክርስቲያን አካላትንና መንገዶችን ሁሉ በማቀናጀት ቃለ እግዚአብሔር ለደረሳቸው የሚጠናከርበትን፣ ላልደረሳቸው ደግሞ የሚዳረስበትን መንገድ ዕለት ዕለት በማሰብ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅብናል።

3. ለካህናት እና ለአብነት መምህራን «የስብከተ ወንጌል ዘዴ» ሥልጠና መስጠት፡-ጌታ በዓለም ሁሉ ተበትኖ ለሚኖረው የሰው ዘር የወንጌልን ትምህርት ያስፋፉ ዘንድ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት፣ ሰባ ሁለቱን አርድዕትና ሠላሳ ስድስቱን ቅዱሳት አንስት በማሠልጠን አሠማርቶ ነበር። እነርሱም ከጌታ የተቀበሉትን አደራ ደከመን፣ ሰለቸን፣ ራበን፣ ጠማን፣ ተራቆትን፣ ተቸገርን ወዘተ ሳይሉ ዓለምን ሁሉ ዞረው በደማቸው ጭምር በማስተማር አልፈዋል። ዓለምን በትምህርተ ወንጌል /በክርስትና/ ፈውሰዋል፤ አጣፍጠዋል። ከዚህም በኋላ የተነሡ ሐዋርያውያን አበው፣ ሰማዕታትና ሊቃውንት በትምህርተ ወንጌል ኖረው፣ ትምህርተ ወንጌልን ሰብከው አልፈዋል።

ይህ ቀደምትና ትውልድ እየተቀባበለ ይጠቀምበት ዘንድ በጌታችን ተባርኮ የተሰጠው የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያና ማጠናከሪያ ሥልት ዛሬም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የመሠረተ አምላክ ምሥጋና ይግባውና ቤተ ክርስቲያናችን በርካታ ካህናትና የአብነት መምህራን አሏት። እነዚህ ሊቃውንት ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን እንዲከናወን በሚያስፈልገው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ሰፊውን ድርሻ ሊይዙ ይገባል። ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያኑ በዕውቀት መንፈሳዊት ምግብነት ተኮትኩተው እንደ ማደጋቸው ከእነሱ አልፎ ለዓለም ብርሃን የሚሆን ዕውቀት አላቸው። ይህ ለዘመናት የካበተ ዕውቀታቸው ዘመኑና ትውልዱ በሚፈልገው መልኩ ተደራጅቶ እንዲቀርብ ደግሞ ተከታታይ ሥልጠናዎችና የልምድ ልውውጦች ያስፈልጋሉ። እነዚህ ሥልጠናዎች እንደየ አስፈላጊነታቸው ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ በየደረጃው ባሉ የቤተ ክርስቲያ አካላት ሊዘጋጁ ይችላሉ።

4. «የስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ፈንድ» /የገንዘብ ተቋም/ ማቋቋም፡- የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ኃይልና ጉልበት እግዚአብሔር ነው። አስቀድመን እንደ ገለጽነው እውነተኛውን ትምህርተ ወንጌል ይዛ የተገኘችው በሰው ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነት፥ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፥ በቅዱሳን ተጋድሎ ነው። የእግዚአብሔርን ጸጋና በረከት ለማግኘት ደግሞ የራስ ዝግጅት ያስፈልጋል። ከዚህ ውስጥ አንዱ ከዕለት ጉርሳችን ከዓመት ልብሳችን ቀንሰን ለቃለ እግዚአብሔር ማስፋፊያ ማዋል ነው።

5. ሁሉም በያለበት በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መኖር፡- ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ወንጌልን የምታስተምረው ደጋፊ ለማብዛት ወይም ሌላ ልዩ ጥቅም ለማግኘት አይደለም። የሰው ዘር ሁሉ ለሥጋው ፈውስን ለነፍሱ ድኅነትን እንዲያገኝ ለማዘጋጀት፥ ከእግዚአብሔር የተሰጣትን ተልእኮ ለመፈጸም ነው። ይህ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ፍሬ በማፍራት ሌላውንም ሊስብ የሚችለው ምእመናንም ሆኑ ካህናት በትምህርተ ወንጌል ታንጸው በክርስቲያናዊ ሕይወት ሲኖሩ ነው። እግዚአብሔርን ፈርቶ ሰውን አክብሮ በእውነት መኖር ለቀዳሽም፣ ለአንጋሽም፣ ለነጋሽም ተገቢ ነው። ይህ ከሆነ የወንጌል ፍሬ በምድር ላይ ይታያል፤ የቅዱሳን መዓዛ ዓለምን ማወድ ይጀምራል፤ ንብ በአበባ ዙሪያ እንደ ምትዞር በደጋግ ሰዎች ምክንያት ኢ-አማንያን ወደ ክርስትና ሕይወት ይመለሳሉ፤ ወደ እናት ሃይማኖት ይገባሉ፤ ረድኤተ እግዚአብሔር ለሀገር ይተርፋል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕይወት በሚሆናት ስብከተ ወንጌል ለዓለሙ ሕይወት እየሰጠች ትኖራለች።

የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ጸሎትና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።



' www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## ስለአዲሱ ሚሊኒየም

በሐመር መጽሔት 12ኛ ዓመት ቁጥር አራት እትም በደብዳቤዎች ዓምድ «ለአዲሱ ሚሊኒየም ምን ታስቧል?» በሚል ርእስ በመ/ር አንዱ ዓለም ታደሰ የቀረበው ሐሳብ በእጅጉ ወቅታዊና ልንወያይበት የሚገባ ነው:: በእውነቱ÷ እርሳቸው ቀደሙኝ እንጂ በውስጤ ረዘም ላለ ጊዜ ሲመላለስ የነበረ አሳብ ነው:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በታሪክ ጥንታዊት በጥበብም የሥልጣኔ ምንጭና ፍኖተ አእምሮ አደራጅ የመሆንዋን ያህል የኋለኞች ቀድመዋት ሲሄዱ ልትከተላቸው አለመቻሏና ለምእመናኗም በሚጠበቅባት መልኩ ምላሽ ለመስጠት መቸገሯ ያሳስበኛል:: ስለሆነም ከሁሉ አስቀድመን አሳብ ልንለዋወጥባቸው የሚገባቸው ነጥቦች እንደ ቅደም ተከተላቸው ተለይተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል:: በውይይቱ ሂደት ዳብረው የሚወጡት አሳቦች አፈጻጸምና በአፈጻጸሙ ድርሻ የሚኖራቸው አካላትም በግልጽ መመልከት አለባቸው:: በተለይም የምእመናንን ተሳትፎ በመጨመሩና የተባበረ ዐቅማቸውን በመጠቀሙ ረገድ እምነት ሊኖር ይገባል:: በዚህም መሠረት በእኔ በኩል የምስነዝራቸው የመነሻ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው::

1. የቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን ግንኙነት /መንፈሳዊ ሕይወትን/ እንዴት እናጠናክር?
2. የከተማና የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን ዕድገት አንጻራዊ በኾነ መልኩ ለማመጣጠን ምን መደረግ አለበት?
3. ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ጀምሮ በአህጉረ ስብከትና በወረዳ ቤተ ክህነት ያለውን የአስተዳደር መዋቅር እንዴት ማጠናከር ይቻላል?
4. ትምህርተ ሃይማኖትንና መዝሙርን የተመለከቱ ልዩ ልዩ ኅትመቶችን ዝግጅትና ሥርጭት በተመለከተ የቤተ ክርስቲያንን ዐቅም እንዴት ማጠናከር ይቻላል? የሚሉት ናቸው::

*ደመላሽ አሰፋ*
*ስድስት ኪሎ-አ.አ*

## «አዛኝ ቅቤ አንጓች»

ይህን አስተያየት ለመጻፍ ያነሣሣኝ «ልሳነ ሕዝብ» በተባለ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 11 ሰኔ 1996 ዓ.ም እትም «ማኅበረ ቅዱሳን በሉስ አንጀለስ» በሚል ርእስ የወጣው የአጽራረ ቤተ ክርስቲያንና የተረፈ ሉተራውያን ጽሑፍ ነው:: መልካም የሚሠሩትን መንቀፍና ማነወር ዲያብሎሳዊ ተግባር ነው:: ከባሕር ማዶ ያሉ ወገኖቻችን ለእናት ቤተ ክርስቲያናቸው የሚያደርጉትን በጎ አድራጎት እንዲያቆሙ ማከላከል ለቤተ ክርስቲያን ከማሰብ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለማዳከም የታቀደ ደባ ነው:: ትላንት በአገር ቤት ሳሉ አስተዳደራዊ ችግሮቻቸውን በውይይት÷ ሃይማኖታዊ ስሕተታቸውን በንስሓ አርመው እንዲመለሱ ሲወሰንባቸው አገር ጥለው ፈረጠጡ:: ይሁንና ማንነታቸውን በቅጡ ባልተረዳው ወገናችን መካከል ሆነው በስደት የሚንገላታውን ምእመን ይባሱኑ በኑፋቄ ትምህርትና በፖለቲካ አቅዋም ለመከፋፈል እየተራወጡ መሆናቸው ሀገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው እውነት ነው:: ከዚህም በላይ «የዕውቀት ማዕድ ከሆነው ትምህርት ቤት የተማርን ነን» እያሉ ራሳቸውን ያነጋግሣሉ፤ ሌላውን ያንኳስሳሉ:: የዘነጉት ነገር ግን ዕውቀት በመንፈሳዊነት ካልታገዘ «አርዮሳዊነት» መሆኑን ነው:: እንዲህም ስለሆነ አለን የሚሉት «ዕውቀት» ለክሕደት አድርሷቸዋል:: አክለውም ደግሞ «ቅዱስ ሲኖዶስን የሚመራው ማኅበረ ቅዱሳን ነው» ማለታቸው «አዛኝ ቅቤ አንጓች» ያደርጋቸዋል፤ ከዚህም በላይ ብፁዓን አባቶችን ከመዝለፍ፤ የቅዱስ ሲኖዶስን ክብር ከማሳነስም ተለይቶ አይታይም:: ዞሮ ተደምሮ ግን ከተረፈ ሉተራውያን የሚጠበቀው ይኸው በመሆኑ አይገርመኝም:: ቁም ነገሩ ከምንጊዜውም በላይ ማኅበረ ቅዱሳን በአገር ቤትም ኾነ በውጭ ከሚገኙ ምእመናን ጋር ተቀናጅቶ በውይይትና በመግባባት የጀመረውን አገልግሎት ማጠናከር እንዳለበት ነው::

*አሸብር ጥሩነህ*
*ደ/ገ/ቅ/ገ/ቤ/ክን ሰንበት ት/ቤት- አ.አ*

## ተባዕቱን ጾታ በሴት አንቀጽ...

አንዳንዴ የወዳጅነትም ይሁን የሥልጣኔ መገለጫ እየመሰለን የወንዱን /ተባዕቱን/ ጾታ በሴት አንቀጽ መጥራት ተለምዷል:: በይበልጥ የሚያሳዝነው ደግሞ የለመደ አይቀርምና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አልፎ አልፎ ካህናቱ እርስ በርሳቸው «እዚህ ነይ÷ እዚያ ኺጂ» እያሉ መጠራራት፣ መነጋገር ልንሰማ ጀምረናል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎችም ባዕድና ከሥርዓት ውጪ የኾኑ ልምዶች ሥር ሰደው እየገቡ ነው:: ከወዲሁ ማረሙ ሊታሰብበት ይገባል:: በሐመር መጽሔት 12ኛ ዓመት ቁጥር አራት እትም በመንገደኛው ዓምድ ሥር «ፎቶ ኮፒ ሥርዓት ወይስ...?» በሚል ርእስ የተነሡት ችግሮችም ከዚሁ ጋር የሚዛመዱ÷ ተገቢና አፋጣኝ የእርምት ርምጃ የሚሹ ናቸው:: እግረ መንገዴን አክዬ ላስታውሳችሁ የምፈልገው ወደ ቅዱሳት መካናት ጉዞዎች ሲደረጉ አንዳንድ ወንድሞችና እኅቶች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከነጫማቸው ወደ መቅደስ ለመግባት ሲታገሉ፣ ሊበላሹ /ሊደበዝዙ/ የሚችሉ ቅዱሳት ሥዕላትን በፎቶ ካሜራ ብልጭታ /ፍላሽ/ ሲያነሡ ይታያሉ:: በመሆኑም ጉዞውን የሚያዘጋጀው ክፍል ሓላፊነቱን ወስዶ ለቅዱሳት መካናቱ ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ አበክሮ ማሳወቅ ይኖርበታል እላለሁ::

*ተክለ ማርያም ኃይለ ኢየሱስ*
*ጅማ ዩኒቨርስቲ ግቢ ጉባኤ*

## በመረዳት እንድንጸልይና እንድንማር አግዙናል

በሐመር መጽሔት የትምህርተ ሃይማኖት ዓምድ «ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም» በሚል ርእስ ማቅረብ የጀመራችሁት ጽሑፍ ለምእመናን በሚረዳ መልክ የተዘጋጀ ነው:: ባለሁበት አገር በአንድ የቤተ ክርስቲያን አባት መምህርነት የውዳሴ ማርያምን ዜማ እየተማርኩ ነው:: ይሁንና የማጠናው በ«ሽምደዳ» ስለ ነበር ጽሑፉ ትርጉሙንና ምሥጢሩን በመረዳት ረገድ



www.eotcmk.org

እገዛ አድርጎልኛል፡፡ በተለይም የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን ትምህርት መሠረት በማድረግ ያቀረባችሁት ማብራሪያ ምሥጢረ ሥጋዌን በሚገባ ለመረዳት ያስችለናል፡፡ እግዚአብሔር ጸጋውን ያብዛላችሁ፡፡ በመጨረሻም በ12ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት እትም በእናስተዋውቃችሁ ዓምድ ያወጣችሁት የቅዱስ አርሳንዮስ ታሪክ የውስጤን ጥያቄ የመለሰልኝ በመሆኑ ከልቤ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡

*ሜሪ ደጉ - አቡዳቢ*

*አስቻለው ወርቁ - ድሬዳዋ*

*ከአዘጋጁ፡-* በሥራ ምክንያት በአቡዳቢ የምትገኚው የዘወትር ተሳታፊያችን ሜሪ ደጉ ከግብፃዊ አሠሪዬ አገኘሁት ያልሽው የቅዱስ አርሳንዮስ ሥዕለ ገጽ ደርሶናል፡፡ እናመሰግናለን፡፡

## የቤተ ክርስቲያን ይዞታ

የአገራችንን የድህነትና የኋላ ቀርነት መንሥኤዎች በተመለከተ ባሕረ ጥበባት የኾነችውን ቤተ ክርስቲያናችንን በምክንያትነት ለሚጠቅሱት ሁሉ አስተዋይ ልቡናን ይስጣቸውና በሐመር መጽሔት 12ኛ ዓመት ቁጥር አራት እትም «ድህነት እንዲቀነስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሚና ምን መሆን አለበት?» በሚል ርእስ በዶ/ር ዓለማየሁ ረዳ፤ እንዲሁም በማኅበረ ቅዱሳን የተጠኑ፣ የተተገበሩና በመተግበር ላይ የሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ያቀረባችኋቸው ጽሑፎች በእጅጉ አስደስተውናል፡፡ በጥናቱ በቀረቡት የወደፊት ዕቅዶችም ተስማምተናል፡፡ ገንዘብ ባይኖረንም በጸሎትና በሐሳብ ከእናንተ ጋር ነንና ግፉበት እንላለን፡፡ በተለይም በጀመራችሁት የልማት ፕሮጀክቶች ዳሰሳ በመቀጠል በአርአያነት ሊጠቀሱ የሚችሉ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን እንቅስቃሴ ብትዘግቡ መልካም ነው፡፡ በሌላ በኩል እስከ ማውቀው ድረስ ስምጥ ሸለቆን ተከትለው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ከአስተዳደር ድክመት የተነሣ ይዞታቸው ለባለ ሀብቶች እየተሰጠ ነው፡፡ የልማት ፕሮጀክቱ የጥናትና ትግበራ ዕድል ለእነርሱም ቢደርሳቸው መልካም ነው፡፡ በአዋሽ ወንዝ ዳር ያሉቱም እንዲሁ ተገቢ የልማት ፕሮጀክት ቢቀረጽላቸው የቤተ ክርስቲያንን፣ የነዳያንንና የድኾቿን ችግር በመቅረፍ ረገድ ታላቅ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል፡፡

*ዮሐንስ ቦጋለ - ናዝሬት*

*ዲ.ን ምንተስኖት - አ.አ*

## መልካም ጅምር

በሐመር መጽሔት 12ኛ ዓመት ቁጥር አራት እትም «ሐመረ ሕይወት» በተሰኘ አዲስ ዓምድ «መፍትሔው ከዚህ አለ» በሚል ርእስ ከ"Action Aid Ethiopia" ጋር በመተባበር ማቅረብ የጀመራችሁትን በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ላይ የሚያተኩረውን ትምህርታዊ ጽሑፍ በጥሞና ተመልክቸዋለሁ፡፡ ሃይማኖታዊውንና ሳይንሳዊውን አስተ ምህሮ ባጣመረ መልኩ ተገቢ መፍትሔ ያቀ ረበ ነው፡፡ ይህን መልካም ጅምራችሁን አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉበት እግዚአብሔር ብርታቱን ይስጣችሁ፡፡

*ሠመረ ውቤ*

*ደ/ኃ/ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን*

## አቁሜያስሁ

በተለያየ ጊዜ የተለያዩ አስ ተያየቶችን ልኬላችሁ ነበር፡፡ ነገር ግን አስተያየቶቼ በብዛት ሂስ ስለሚበዛባቸው ማለትም ስሕተቶችን ስለሚጠቁሙ ይመስለኛል ደፍተው ሊስተናገዱ አል ቻሉም፡፡ መስተናገዱስ ይቅርባቸውና የደርሶናል ዝርዝር ውስጥ እንኳን ስሜ ሊጻፍ አልቻለም፡፡ በመሆኑም ከዛሬ ጀምሮ ሂስ መጻፍ፣ አስተያየት መስጠት እና ስሕተት መጠቆሜን አቀሜአለሁ፡፡

*ዶ/ር ዘርፉ መልአኩ*

*በደሌ*

*ከአዘጋጁ፡-* ውድ ወንድማችን በደብዳቤዎ በስፋት የዘረዘሩልንን ቅሬታ ከእርስዎ ይመጣል ብለን ጠብቀን አናውቅም ነበር፡፡ ምክንያቱም ያለማቋረጥ ከሚደርሱን በሳልና ተገቢ አስተያየቶች ዘወትር የምንገነዘበው የሚጽፉልን በዋናነት የእኛን ይሁንታ ለማግኘት ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ልጅነትዎና መጽሔታችንንም ከጅምሩ ጀምሮ ስለሚያውቋት የማረምና አስተያየት የመስጠት የውዴታ ግዴታ እንዳለብዎ በመገንዘብዎ እንደ ሆነ ነበረና፡፡ በመሆኑም በእጅጉ የሚያስፈልጉንና ከስሜት ነጻ የሆኑ አስተያየቶችዎን፣ ጥቆማዎችዎንና ትምህርቶችዎን አሁንም ይላኩልን፡፡ ከእኛ ከዝግጅት ክፍሉ አባላት እንደ አንዳችን ስለምንቆጥርዎ አስተያየት በሰጡን ቁጥር ስምዎትን ማውጣት አልፈለግንም፡፡ ስሕተት ከሆነ ወደ ፊት እናርማለን፡፡ እግዚአብሔር ይጠብቅዎት፡፡

## መንፈሰ ርኩስ ደም ሲያፋስስ

በአጥቢያዬ በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን በሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ስም የፈለቀ ጠበል አለ፡፡ በጠበሉ በርካታ ምእመናንና ምእመናት ተፈውሰዋል፡፡ ይሁንና በጠበሉ ሥፍራ ከሚጠመቁት በአንዳንዶቹ ላይ ያደረው ርኩስ መንፈስ «እገሌ እንዲህ አደረገኝ /አደረገሽ/» በማለት ሲለፈልፍ እርሱ የተናገረውን እያመኑ በአካባቢው ቆይታ የሚያደርጉት ጠበለተኞች እርስ በርስ እየተወዛገቡ ነው፡፡ እስከ ደም መፋሰስ የደረሱም አሉ፡፡ በመሆኑም በሚመለከተው አካል ለአካባቢው ነዋሪዎችም ይሁን ለጠበለተኞቹ ተገቢው ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል እላለሁ፡፡

*ተክለ ዮሐንስ*

*አ.አ*

## ኃጢአቴ በግልጽ ተረድቶኛል

ሰይጣን በተለያየ መልክ እየመጣ በዝሙት አሸንፎኛል፤ ከተለያዩ ሴቶች አልፎ ከእንስሳትም ጋር አጸያፊ ተግባር ፈጽሜያለሁ፡፡ ከአምስት ጊዜ በላይ ንስሐ ገብቼ ተመልሼ÷ ተዳድፌአለሁ፡፡ እውነትን ተናግሬ አላውቅም፡፡ ይሁንና ከጊዜ በኋላ ራሴን አስተካክዬ በንስሓ ሕይወት ውስጥ እገኛለሁ፡፡ በዚህም ላይ በጥር ወር በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ትዳር ለመመስረት ሓሳብ አለኝ፡፡ በሐመር መጽሔት 12ኛ ዓመት ቁጥር ሦስትና አራት እትሞች የእናስተዋውቃችሁና የክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምዶች ላይ «ቅድስት ማርያም ግብፃዊት»ና «ፈተና ከየት ይመጣል?» በሚሉ ርእሶች የቀረቡት ጽሑፎች ኃጢአቴን በግልጽ አስረድተውኛል፡፡ በእውነቱ እንዲህ ያሉት ዝግጅቶች እኔን የመሰሉ ደካሞችን ሕይወት የሚያጸናኑና የሚያጽኑ ናቸው፡፡ በመጨረሻም የተሰጠኝን ቀኖና ፈጽሜ ለተቀደሰ ሕይወት እንድበቃ ምክራችሁና ጸሎታችሁ አይለየኝ፡፡

*መ/ር ወልደ ገብርኤል*

*አኩስም*

## አስተዋይ ልብ ይስጣቸው!!

ሐመረ ጽድቅ - መስከረም 1997 ዓ.ም እትምን በሚገባ አንብቤዋለሁ፡፡ በእውነቱ «የቤተ ክርስቲያን አባቶች» የምንላቸው ሰዎች እንደዚያ ስሕተትና ጥፋት መፈጸማቸው በእጅጉ ያሳዝናል፡፡ በተለይ አንዳንዶቹ ባለሁበት አገር የሚታወቁበት የካሴት ትምህርታቸውና እውነተኛ ማንነታቸው ፍጹም ተቃራኒ ነው፡፡ ምእመኑን ከነጫማችሁ ወደ ቤተ መቅደስ ግቡ እያሉ መገፋፋታቸውን በራሱ ብቻ ወስነን የምናየው ሳይሆን ሥርዓተ እምነታችንንና ክርስቲያናዊ ትውፊታችንን ለማስጣል የሚያደርጉትን መራወጥ የሚያመለክት ነው፡፡ እንዲያው ለመሆኑ የሚታየውን ጫማውን ጎንበስ ብሎ ማውለቅ ያቃተው ግለሰብ በእነርሱ «ትምህርት» ኃጢአትን ከውስጡ ለማስወገድ ይበቃል ብለው ያስቡ ይሆን? ለሁሉም አስተዋይ ልብ ይስጣቸው፡፡ እናንተንም ረድኤተ እግዚአብሔር አይለያችሁ፡፡

*አዳነች አብዲ*

*ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ተስፋ*

*ስዱዳን ሰንበት ት/ቤት*

*አቡዳቢ*



www.eotcmk.org

የነበረው ሲጐድል የምንጨካከን አለን:: ኢዮብን ያገኙት ችግሮች አግኝቶ ማጣት፣ መከዳዳት፣ መጨካከን፣ ጤና ማጣት ትዳራችንን ሲያጋጥሙት የመጀመሪያውን ትተን በምትኩ ሌላ ጓደኝነት፣ ሌላ ፍቅር፣ ሌላ ጋብቻ የምንፈልግ ወገኖች የሚሳካልን ይመስለናል እንጂ አይሳካልንም:: እዚህ ላይ ሌላ ፍለጋ የተጓዘችው የኢዮብ ሚስት አፈረች እንጂ በትዳሩ የጸናው ጻድቁ ኢዮብ እንዳላፈረ ልብ ማለት ያስፈልጋል:: «እግዚአብሔርም ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛውን ለኢዮብ ባረከ::» እንዲል:: ኢዮ. 42÷12 ::

ደገኛው ኢዮብ የሀብቱ መውደም፣ የጤናው መታወክ ሳይሰማው ቀርቶ አይደለም:: «እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔር ነሳ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን::» ብሏል:: ኢዮብ 1÷22:: ደገኛው ኢዮብ ዐሥር ልጆቹ የተለዩት የዐሥር ልጆቹ ፈጣሪ እንደማይለየው ጽኑ እምነት ስለ ነበረው ነው:: በጐቹ ናቸው እንጂ ያለቁት በጐቹን የሰጠው አምላክ በጐደለው እንደሚሞላለት ያውቃል:: ሚስቱ ብትከዳውም የሚስቱ ፈጣሪ እንደማይከዳው ተገንዝቧል:: ጓደኞቹ ቢከዱትም ጓደኞቹን የፈጠረ ፈጣሪ እንደማይለየው ያውቅ ነበር:: ስለዚህ በትዕግሥት ይህን ሁሉ ጠበቀ:: በመጨረሻም ውጤቱንም ተመልክተናል:: «እግዚአብሔር ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛውን ለኢዮብ ባረከ::» ኢዮ.42÷12:: ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም የኢዮብን የትዕግሥት ፍሬ አስመልክቶ እንዲህ በማለት ይመክረናል:- «እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፤ ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል፣ ጌታም እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና::» /ያዕ.5÷1/ ይለናል:: በትዳር ሕይወት ፈተና ቢያጋጥመን ከእግዚአብሔር ጋር ከሆንን የማናልፈው የፈተና ወጥመድ እንደሌለ ልብ ልንል ይገባል::

## የተሳካ ጋብቻ:-

ጠቢቡ ሰሎሞን «ቤትና ባዕለጸግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳሉ፤ አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት::» ይላል:: ምሳ.19÷14:: ደገኛው አብርሃም በሸመገለ ጊዜ ሎሌውን:- «እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ፤ እኔም አብሬ ከምኖራቸው ከከነዓን ሴቶች ልጆች ለልጄ ሚስት እንዳትወስድለት በሰማይና በምድር አምላክ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ:: ነገር ግን ወደ አገሬና ወደ ተወላጆቼ ትሄዳለህ፤ ለልጄ ለይስሐቅም ሚስትን ትወስድለታለህ::» /ዘፍ. 24÷3/ ይለዋል:: ሎሌውም የአብርሃምን እጅና ጉልበት ይመታል:: አብርሃም እጄን ምታ ማለቱ:- «የሰጠኸኝ አይባረክልኝ በል» ሲያሰኘው ሲሆን ዳግመኛም «ጉልበቴን ምታ» ማለቱ «የወለድኩት አይባረክልኝ ገል» ሲያሰኘው ነው:: እርሱም ጠንቅቆ ይምላል::

## የእምነት አንድነት

እጅና ጉልበትን ጸፍቶ /መትቶ/ መማማል እጅግ አስፈሪ መሐላ ነው:: የአብርሃም ሎሌ የማለውን መሐላ ቢያፈርስ አብርሃም የሰጠው ጥሪት እንደ ማይባረክለት፣ ልጅም ቢወልድ እንደ ማይባረክለት ተማምለዋል:: ይህ ሁሉ መሐላ ለምን አስፈለገ? ትልቁ ነገር ይስሐቅ አዋልደ ከነዓንን /የከነዓን ሴቶችን/ እንዳያገባ ነው::

ከነዓን በአባቱ የተረገመ የካም ልጅ ነው:: ከነዓናውያን ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ናቸው:: ብዙ አማልክትን ያመልኩ ነበር:: ከሁሉም የታወቀው «በኣል» የተባለው ጣዖት ነው:: ዘፍ. 9÷18-27 :: ኢያ. 17÷13:: እንግዲህ አብርሃም ሎሌውን ያስጠነቀቀው ከጣዖት አምላኪዎች ልጁን እንዳያጋባው ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ:- «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና?... ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ፤ ርኩስንም አትንኩ::» 2ኛ.ቆሮ. 6÷14–17:: ሲል እንደ ተናገረው የአብርሃም ጥንቃቄ ሃይማኖትን ይመለከታል:: በጋብቻ የሃይማኖት አንድነት መኖር ተገቢ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል:: ምክን ያቱም:- «የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?» ተብሎ ተጽፏልና:: ሌላው «ወደ ተወላጆቼ ሂድ» ሲል ያስጠነቀቀው «ዘረኛ» ሆኖ አይደለም:: ከነዓናውያን ጣዖትን አምላኪ ስለሆኑ ነው:: የሃይማኖት አንድነት የትዳር መሠረት ነው:: ዳግመኛ «የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ» እንዲል:: 1ኛ ጴጥ. 1÷23-25:: አንዳንድ ወገኖች ብኩርናውን ለምሥር ወጥ እንደ ለወጠ እንደ ዔሳው በሃይማኖት ሳይመሳሰሉ እምነታቸውን ለውጠው ትዳርን የሚመሠርቱ ወገኖች አሉ:: አብርሃም ሎሌውን ያስማለውን መሐላ ማጤን ተገቢ ነው:: ዔሳው እንደ ዋዛ ያጣውን ብኩርና:- «በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሐ ሥፍራ አላገኘም::» ዕብ.፲፪÷፲፯:: ብዙዎች የተሻለ ነገር ፍለጋ እንዲሁም በአጉል ወደድኩህ ወደድኩሽ ፈሊጥ ሃይማኖትን ያህል የሕይወት መሠረት ረግጠው÷ ገንዘብ ያለው /ገንዘብ ያላት/ ከተገኘ /ከተገኘች/ ብለው የሚጀምሩት ሕይወት ለዘላለም ጸጸት ሊያጋልጥ ስለ ሚችል ቅድመ ትዳር የሃይማኖት አንድነት መኖር እንዳለበት ማጤን ያስፈልጋል::

## እግዚአብሔር የተጠራበት ጋብቻ /ትዳር/

ኢያውብር /የአብርሃም ሎሌ/ የጌታውን እጅና ጉልበት ከመታ በኋላ ስጋት ተሰማው:: «ለይስሐቅ የማመጣት ብላቴና ወደ ነበርክበት አልመጣም ያለች እንደ ሆነ እርሱን ይገፍው ልሂድን?» ይለዋል:: አብርሃምም ልጁን ከከነዓን ሴቶች እንዳያጋባው:- «እግዚአብሔር መንገድህን ያቃናልሃል፤ አምጥተህ አጋባው እንጂ ልጄን አትውሰደው» አለው:: ያን ጊዜ ሎሌው በዐሥር ግመል ጭኖ የልጠጅቷን እናቷንና አባቷን ሰፈሯንም ወደማያውቅበት አገር እግዚአብሔርን መሪ አድርጎ ጉዞውን ይጀምራል:: ጀንበር ሳታዘቀዝቅ ከውኃ ዳር ተቀምጦ:- «የጌታዬ የአብርሃም አምላክ ሆይ÷ እለምንሃለሁ÷ ውኃ ከሚቀዱት ሴቶች ከጌታዬ ከአብርሃም ወገን ኾና መልክ ከደም ግባት አስተባብራ የያዘች ብላቴና /ልጃገረድ/÷ ውኃ እጠጣ ዘንድ እንስራሽን አዘንብዪ የምላት እርስዋም አንተም ጠጣ፤ ግመሎችን ደግሞ አጠጣለሁ የምትለኝ ቆንጆ እርሷን ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን» ሲል ወደ እግዚአብሔር አመለከተ:: ጸሎት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ሕያው መስመር ነው:: እግዚአብሔር የአብርሃም ሎሌ የሚፈልጋትን ልጅ ከነምልክቷ አስረከበው:: እንዲያውም:- «ይህን መናገር ሳይፈጽም ወንድ የማታውቅ ድንግል የባቱኤል ልጅ ርብቃ በአጭር ታጥቃ ማድጋዋን ነጥቃ መጣች:: እንስራዋን አውርዳ አጠጣችው፤ ለግመሎቹም እስከሚረኩ ድረስ ቀድታ አጠጣችለት::» ይላል:: ዘፍ.፳፬÷፲፪–፲፰ ::

## ጸሎት

ሐዋርያው ያዕቆብ:- «የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች::» ይላል:: ያዕ.፭÷፲፮:: አብርሃም ሎሌውን ወደ ሜስጶጦምያ /ሶርያ/ ሲልከው መንገዱ ሁሉ እንዲቃናለት ይጸልይ ነበር:: ብዙዎቻችን ለልጆች የጋብቻ ሕይወት መቃናት የአባትና እናት እንዲሁም የጓደኛ ጸሎት አስፈላጊ ነው:: ለወላጆቻችን÷ለንስሐ አባታችን ስለ እጮኞችን ግልጽ አንሆንም:: የጋብቻችን ሰዓት እንኳ መቃረቡን የምንናገረው በመጨረሻ ሰዓት ነው:: ከድብቅነታችን የተነሣ ራሳችንንና ሌሎችን እንጐዳበታለን:: ቤተሰቦቻችንና መንፈሳዊ አባታችን በጸሎት እንዳያግዙን መንገዱን ዝግ ስለምናደርግ እንጐዳበታለን እንጂ አንጠቀምም:: በጸሎት ሊረዱን የሚችሉ ወላጆቻችንን እንዲሁም መንፈሳዊ አባትን ማማከር ተገቢ መሆኑን ልንረዳ ይገባናል::

የአብርሃም ሎሌ መንገዱ ሁሉ የተቃናለት አስቀድሞ በመጸለዩ ነው:: መልካም የትዳር ጓደኛ ለማግኘት





www.eotcmk.org

የነበረው ሲጐድል የምንጨካከን አለን:: ኢዮብን ያገኙት ችግሮች አግኝቶ ማጣት፣ መከዳዳት፣ መጨ ካከን፣ ጤና ማጣት ትዳራችንን ሲያ ጋጥሙት የመጀመሪያውን ትተን በም ትኩ ሌላ ጓደኝነት፣ ሌላ ፍቅር፣ ሌላ ጋብቻ የምንፈልግ ወገኖች የሚሳካልን ይመስለናል እንጂ አይሳካልንም:: እዚ ህ ላይ ሌላ ፍለጋ የተጓዘችው የኢዮብ ሚስት አፈረች እንጂ በትዳሩ የጸናው ጻድቁ ኢዮብ እንዳላፈረ ልብ ማለት ያስፈልጋል:: «እግዚአብሔርም ከፊተ ኛው ይልቅ የኋለኛውን ለኢዮብ ባረከ::» እንዲል:: ኢዮ. 42÷12 ::

ደገኛው ኢዮብ የሀብቱ መውደም፣ የጤናው መታወክ ሳይሰማው ቀርቶ አይደለም:: «እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግ ዚአብሔር ነሳ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን::» ብሏል:: ኢዮብ 1÷ 22:: ደገኛው ኢዮብ ዐሥር ልጆቹ የተለዩት የዐሥር ልጆቹ ፈጣሪ እንደ ማይለየው ጽኑ እምነት ስለ ነበረው ነው:: በጐቹ ናቸው እንጂ ያለቁት በጐቹን የሰጠው አምላክ በጐደለው እንደሚሞላለት ያውቃል:: ሚስቱ ብትከዳውም የሚስቱ ፈጣሪ እንደማይ ከዳው ተገንዝቧል:: ጓደኞቹ ቢክዱትም ጓደኞቹን የፈጠረ ፈጣሪ እንደማይለ የው ያውቅ ነበር:: ስለዚህ በትዕግሥት ይህን ሁሉ ጠበቀ:: በመጨረሻም ውጤቱ ንም ተመልክተናል:: «እግዚአብሔር ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛውን ለኢዮብ ባረከ::» ኢዮ.42÷12:: ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም የኢዮብን የትዕግሥት ፍሬ አስመልክቶ እንዲህ በማለት ይመክረናል:- «እነሆ በትዕግሥት የ ጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፤ ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል፣ ጌታም እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና::» /ያዕ.5÷1/ ይለናል:: በትዳር ሕይወት ፈተና ቢያጋጥመን ከእግዚአብሔር ጋር ከሆንን የማናልፈው የፈተና ወጥ መድ እንደሌለ ልብ ልንል ይገባል::

## የተሳካ ጋብቻ:-

ጠቢቡ ሰሎሞን «ቤትና ባዕለ ጸግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳሉ፤ አስ ተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት::» ይላል:: ምሳ.19÷14:: ደገኛው አብርሃም በሸመገለ ጊዜ ሎሌውን:- «እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ፤ እኔም አብሬ ከምኖራቸው ከከነዓን ሴቶች ልጆች ለልጄ ሚስት እንዳትወስድለት በሰማይና በምድር አምላክ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ:: ነገር ግን ወደ አገሬና ወደ ተወላጆቼ ትሄዳለህ፤ ለልጄ ለይስሐቅም ሚስትን ትወስድለታለህ::» /ዘፍ. 24÷3/ ይለዋ ል:: ሎሌውም የአብርሃምን እጅና ጉል በት ይመታል:: አብርሃም እጄን ምታ ማለቱ:- «የሰጠኸኝ አይባረክልኝ በል» ሲያሰኘው ሲሆን ዳግመኛም «ጉልበቴን ምታ» ማለቱ «የወለድኩት አይባ ረክ ልኝ ገል» ሲያሰኘው ነው:: እር ሱም ጠ ንቅቆ ይምላል::

## የእምነት አንድነት

እጅና ጉልበትን ጸፍቶ /መትቶ/ መ ማማል እጅግ አስፈሪ መሐላ ነው:: የአ ብርሃም ሎሌ የማለውን መሐላ ቢያ ፈርስ አብርሃም የሰጠው ጥሪት እንደ ማይባረክለት፣ ልጅም ቢወልድ እንደ ማይባረክለት ተማምለዋል:: ይህ ሁሉ መሐላ ለምን አስፈለገ? ትልቁ ነገር ይስሐቅ አዋልደ ከነዓንን /የከነዓን ሴቶችን/ እንዳያገባ ነው::

ከነዓን በአባቱ የተረገመ የካም ልጅ ነው:: ከነዓናውያን ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ናቸው:: ብዙ አማልክትን ያመልኩ ነበር:: ከሁ ሉም የታወቀው «በኣል» የተባለው ጣዖት ነው:: ዘፍ. 9÷18-27 :: ኢያ. 17÷13:: እንግዲህ አብርሃም ሎሌውን ያስጠነቀቀው ከጣዖት አምላኪዎች ልጁ ን እንዳያጋባው ነው:: ቅዱስ ጳው ሎስ: - «ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና?... ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ፤ ርኩስንም አትንኩ::» 2ኛ.ቆሮ. 6÷14–17:: ሲል እንደ ተናገረው የአብርሃም ጥንቃቄ ሃይ ማኖትን ይመለከታል:: በጋብቻ የሃይ ማኖት አንድነት መኖር ተገቢ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል:: ምክን ያቱም: - «የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?» ተብሎ ተጽፏልና:: ሌላው «ወደ ተወላጆቼ ሂድ» ሲል ያስጠ ነቀቀው «ዘረኛ» ሆኖ አይደለም:: ከነዓ ናውያን ጣዖትን አምላኪ ስለሆኑ ነው:: የሃይማኖት አንድነት የትዳር መሠረት ነው:: ዳግመኛ «የተወለዳችሁት ከሚጠ ፋ ዘር አይደለም በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ» እንዲል:: 1ኛ ጴጥ. 1÷23-25:: አንዳንድ ወገኖች ብኩ ርናውን ለምሥር ወጥ እንደ ለወጠ እንደ ዔሳው በሃይማኖት ሳይመሳሰሉ እምነታቸውን ለውጠው ትዳርን የሚመ ሠርቱ ወገኖች አሉ:: አብርሃም ሎሌ ውን ያስማለውን መሐላ ማጤን ተገቢ ነው:: ዔሳው እንደ ዋዛ ያጣውን ብኩ ርና:- «በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሐ ሥፍራ አላገኘም::» ዕብ.፲፪÷፲፯:: ብዙዎች የተሻለ ነገር ፍለጋ እንዲሁም በአጉል ወደድኩህ ወደድኩሽ ፈሊጥ ሃይ ማኖትን ያህል የሕይወት መሠረት ረግጠው÷ ገንዘብ ያለው /ገንዘብ ያላት/ ከተገኘ /ከተገኘች/ ብለው የሚጀምሩ ት ሕይወት ለዘላለም ጸጸት ሊያጋልጥ ስለ ሚችል ቅድመ ትዳር የሃይማኖት አንድነት መኖር እንዳለበት ማጤን ያስፈልጋል::

## እግዚአብሔር የተጠራበት ጋብቻ /ትዳር/

ኢያውብር /የአብርሃም ሎሌ/ የጌታውን እጅና ጉልበት ከመታ በኋላ ስጋት ተሰማው:: «ለይስሐቅ የማ መጣት ብላቴና ወደ ነበርክበት አልመ ጣም ያለች እንደ ሆነ እርሱን ይገፎው ልሂድን?» ይለዋል:: አብርሃምም ልጁ ን ከከነዓን ሴቶች እንዳያጋባው: - «እግዚአብሔር መንገድህን ያቃና ልሃል፤ አምጥተህ አጋባው እንጂ ልጄን አትውሰደው» አለው:: ያን ጊዜ ሎሌው በዐሥር ግመል ጭኖ የልጠ ጅቷን እናቷንና አባቷን ሰፈሯንም ወደማያውቅበት አገር እግዚአብሔርን መሪ አድርጎ ጉዞውን ይጀምራል:: ጀንበር ሳታዘቀዝቅ ከውኃ ዳር ተቀ ምጦ:- «የጌታዬ የአብርሃም አምላክ ሆይ÷ እለምንሃለሁ÷ ውኃ ከሚቀዱት ሴቶች ከጌታዬ ከአብርሃም ወገን ኾና መልክ ከደም ግባት አስተባብራ የያዘች ብላቴና /ልጃገረድ/÷ ውኃ እጠ ጣ ዘንድ እንስራሽን አዘንብዪ የምላት እርስዋም አንተም ጠጣ፤ ግመሎችን ደግሞ አጠጣለሁ የምትለኝ ቆንጆ እርሷን ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን» ሲል ወደ እግዚአብሔር አመ ለከተ:: ጸሎት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ሕያው መስመር ነው:: እግዚአብሔር የአብርሃም ሎሌ የሚፈ ልጋትን ልጅ ከነምልክቷ አስረከበው:: እንዲያውም:- «ይህን መናገር ሳይፈ ጽም ወንድ የማታውቅ ድንግል የባቱ ኤል ልጅ ርብቃ በአጭር ታጥቃ ማድጋዋን ነጥቃ መጣች:: እንስራዋን አውርዳ አጠጣችው፤ ለግመሎቹም እስከሚረኩ ድረስ ቀድታ አጠጣች ለት::» ይላል:: ዘፍ.፳፬÷፲፪–፲፰ ::

## ጸሎት

ሐዋርያው ያዕቆብ:- «የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደር ጋለች::» ይላል:: ያዕ.፭÷፲፮:: አብርሃም ሎሌውን ወደ ሜስጶጦምያ /ሶርያ/ ሲ ልከው መንገዱ ሁሉ እንዲቃናለት ይ ጸልይ ነበር:: ብዙዎቻችን ለልጆች የጋ ብቻ ሕይወት መቃናት የአባትና እናት እንዲሁም የጓደኛ ጸሎት አስ ፈላጊ ነው:: ለወላጆቻችን÷ለንስሐ አባ ታችን ስለ እጮኛችን ግልጽ አንሆንም:: የጋብቻችን ሰዓት እንኳ መቃረቡን የምንናገረው በመጨረሻ ሰዓት ነው:: ከድብቅነታችን የተነሣ ራሳችንንና ሌሎችን እንጐዳበታለን:: ቤተሰቦቻች ንና መንፈሳዊ አባታችን በጸሎት እን ዲያግዙን መንገዱን ዝግ ስለምናደርግ እንጐዳበታለን እንጂ አንጠቀምም:: በ ጸሎት ሊረዱን የሚችሉ ወላጆቻችንን እንዲሁም መንፈሳዊ አባትን ማማከር ተገቢ መሆኑን ልንረዳ ይገባናል::

የአብርሃም ሎሌ መንገዱ ሁሉ የተ ቃናለት አስቀድሞ በመጸለዩ ነው:: መልካም የትዳር ጓደኛ ለማግኘት



www.eotcmk.org

እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ያስፈልጋል:: የጋብቻ ሕይወት ምድር ላይ መሠረቱ ቢጣልም ወደ ረቂቅ ጉዞ አምርቶ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ልዩ ዝማሬ ወደ ሚያቀርቡበት ብቃት ይዘልቃል:: ለዚህ የክብር ሕይወት ለመብቃት መጸለይ የሚያሳፍር ጉዳይ አይደለም:: ስለዚህ እንደ አብርሃምና እንደ ሎሌው እንደ ይስሐቅ ለጋብቻ ሥምረትም ይሁን በሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሔ ለማግኘት መጸለይ ይኖርብናል::

ርብቃ ለጋብቻ የተገኘችው በጸሎት ነው:: ርብቃ በእናት አባቷ በወንድሞቿ «አንቺ እኅታችን÷እልፍ አእላፋት ሁኚ ዘርሽም የጠላቶችን ደጅ ይውረስ»:: ዘፍ.24÷60:: ተብላ ተመርቃለች:: ይህ የእናት አባቷና የወንድሞቿ ምርቃት ርብቃን በሕይወት ዘመኗ ተከትሏታል:: «ዘርሽ የጠላትን ምድር ይውረስ» እንደ ተባለች እስራኤልን ከእሷ አብራክ የተገኙ ዘሮቿ ምድረ ርስት ከነአንን ወርሰዋል:: ፍጻሜው ግን በልጅነት የምንወርሳትን መንግሥተ ሰማያትን የሚያመላክት ትንቢታዊ ቃል ነው:: ከእርሷ የልጅ ልጅ የተወለደው መድኀን የጠላትን ግዛት በመስቀሉ አፍርሶ ከእርሱ ርቀን የነበርነውን ወደራሱ አቅርቦናል:: መንግሥተ ሰማያትም እንደ ሚያወርሰን ቃል ገብቶልናል:: ዛሬ በካህናት አባቶች መባረክ፣በእናት አባት አንደበት መመረቅ ምን ያህል በረከት እንደ ሚያስገኝ ማስተዋል ያስፈልጋል::

አንዳንድ ወጣቶች «አባቴና እናቴ ማግባቴን ባያውቁ ምን አለበት? የንስሐ አባቴ ባያውቁት ምን አለበት?» ይላሉ:: ነገር ግን ለመንፈሳዊ አባትና ለቤተሰብ ተናግረን ቤተሰብም እንደ ቤተሰብነቱ መንፈሳዊ አባትም እንደ ሃይማኖታችን ሥርዓት ጸልየውልን መሸኘት ለበረከት ያበቃናልና ችላ ልንለው አይገባም::

የሣራ ድንኳን ዘወትር የሐዘን እንጉርጉሮ ይደመጥበት ነበር:: ምክንያቱም የቤቱ እመቤት ሣራ ዐረፍተ ዘመን ወስዷታል:: ይስሐቅም እናቱን ሞት በሚባል ባላጋራ ስለ ተነጠቀ ከድንኳኑ ውስጥ የተሰቀሉትን ልብሶቿንና ጌጣጌጦቿን እየተመለከተ ዘወትር ያነባ ነበር:: ርብቃ ለይስሐቅ በዚህ ሰዓት ነበር የደረሰችለት:: «ይስሐቅም ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን አገባት፤ ርብቃንም ወሰዳት:: ሚስትም ሆነችው ÷ ወደዳትም፤ ይስሐቅም ከእናቱ ሞት ተጽናና::» ይላል:: ዘፍ.24÷27:: ማንም ሰው እንደ ሚያውቀው የእናት ውለታ ታላቅ ነው:: ይስሐቅ ርብቃን በማግኘቱ እያደር እንደ ድንጋይ ትራስ የሚቆረቁረውን የእናቱን ሞት ረስቶ ከሐዘኑ ተጽናንቷል:: ጌታችን «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል÷ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል÷ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» ያለው ስለዚህ ነው:: ማቴ. ፲፱÷፭:: ርብቃ ይስሐቅን ከእናቱ ሞት ልታጽናናው ችላለች:: ለምን? ቢባል ርብቃ በጸሎት ስለ ተገኘች ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞን «ቤትና ባለጠግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳሉ፤ አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት::» ያለው ስለዚህ ነው:: ምሳ.19÷14:: የርብቃ አስተዋይነት የባሏን ሐዘን በማስረሳት ተመስክሯል:: ሚስት መሆን ታላቅ ሓላፊነት ነው:: ሚስትነት ከእግዚአብሔር የሚሆን ማስተዋልንና ጸጋን የሚጠይቅ ነው:: ርብቃ በነበራት ጸጋ እግዚአብሔር ነው የባለቤቷን የይስሐቅን እያደር የሚቆረቁር የእናት ሐዘን ልታስረሳው የቻለችው:: ዛሬ ይህን ጸጋ ለማግኘትና በአግባቡ ለመጠቀም የሚስትን አስተዋይነት ይጠይቃል:: ባል አዝኖ ቢመጣ፣ ቢጐሰቁል፣ ቢያዝን ከጐን ሆኖ ማጽናናት ተገቢ እንደ ሆነ ከርብቃ ልንማረው የሚገባ ብልሃት ነው:: የእርሷንም አስተዋይነት ገንዘብ ማድረግ በትዳራችን ሞገስ እንድናገኝ እገዛ ያደርግልናል::

## ፈተናን መቋቋም

ሥርዓተ ጋብቻ ፈጽሞ ሳለ ልጅ አለመውለድ ለተጋቢዎች ትልቅ ፈተና ነው:: ለዚህም ወደ ኋላ ተመልሰን የራሔልን ሕይወት መመልከት ይቻላል:: ራሔል ልጅ መውለድ እየፈለገች ማኅፀኗ ዝግ ይሆናል:: የን ጊዜ ያዕቆብን «ልጅ ስጠኝ፤ ይህስ ካልሆነ እሞታለሁ አለችው::» ይላል:: ዘፍ. 30÷1:: ተጋብቶ ልጅ አለመውለድ ምን ያህል ፈታኝ እንደ ሆነ ከዚህ መገንዘብ ይቻላል::

ራሔል የማኅፀኗን ፍሬ በማጣትዋ ሞት ተመኝታለች:: ርብቃና ይስሐቅ ተጋብተው ሃያ ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ልጅ አልወለዱም:: ይህ ሁኔታ የርብቃን ሥነ ልቡና በጥቂቱ መጉዳቱ አይቀርም:: ይስሐቅ በእናት ሞት ሐዘን ሲንገላታ ርብቃ ከጐኑ ቀርባ እንዳጽናናችው፣ ዛሬ እርሱም በተራው ሚስቱ ልጅ ባለመውለዷ ስትፈተን ስለ ሚስቱ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ:: መካን ነበረችና እግዚአብሔር ተለመነው ና ሚስቱ ፀነሰች:: ዘፍ.፳፭÷፳፩::

በትዳር ውስጥ ለሚፈጠር ፈተና ጸሎት ምን ያህል ኃይል እንዳለው መገንዘብ ተገቢ ነው:: ዛሬ ተጋብተን ልጅ በማጣታችንም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች ብንፈተን÷ ባሎች ለሚስቶቻችን ብንጸልይ ለርብቃና ለይስሐቅ መፍትሔ የሰጠ አምላክ መፍትሔ ሊሰጠን እንደ ሚችል ከሁለቱ የትዳር ሕይወት ልንማር ይገባል:: እንዲህ ሲባል ሚስት ለባል መጸለይ አይገባትም ማለት አይደለም:: ርብቃ ባለመውለዷ ይስሐቅ ጠንቋይን አላማከረም:: ያማከረው እግዚአብሔርን ነው:: እግዚአብሔር የተዘጋውን ይከፍታል:: ስንታበይ ደግሞ የተከፈተውን ይዘጋል::

## ንጽሕና

ድንግልና ለሴቷም ይሁን ለወንዱ የመታመን መገለጫ ነው:: ለዚህ የመታመን መገለጫ መጥፋት ብዙ እስራኤላውያት ወጣቶች አመድ ነስንሰው ማቅ ለብሰው አንብተዋል:: ትዕማር አላግባብ ለጠፋ ድንግልናዋ አመድ ነስንሳ በአደ ባባይ አልቅሳለታለች:: የዮፍታሔ ልጅ ለተከበረ ድንግልናዋ ከጓደኞዋ ጋር ሁለት ወር አልቅሳለች:: መሳ. 16÷37–40:: ሳሙ.ካል.13÷19::

ርብቃን ወንድ የማያውቃት ድንግል ነበረች:: ዘፍ.24÷16:: ድንግልና የእውነተኛ ትዳር ትክክለኛ መንገድ ነው:: ለትዳራችን ሥምረት ማረጋገጫ÷ ማዕበል ሳይመታው ጐርፍ ሳይጐርፍበት÷ ነፋስ ሳያዘመው ፀንቶ እንዲዘልቅ ድንግልና ሥነ ልቡናዊ ዋጋ አለው:: የጋብቻ ጨዋነት÷ መንፈሳዊ ጥንካሬ ከፍ የሚለው የትዳር ባልደረቦች በሚኖራቸው የቅድመ ጋብቻ ድንግልና ነው:: በጋራ ወስነው በድንግልናቸው አሐዱ ብለው የጀመሩትን ሕይወት በቅድስና አብረው ስለሚካፈሉት ጋብቻቸው ስኬታማ የመሆኑ ዕድል ከፍ ያለ ነው::

አንዳንዶች ይህን የተከበረ ንጽሕናቸውን አላግባቡ ያጠፉታል:: ለትዳር ትልቁ ነገር መተማመን ነው:: ያለድንግልና የተመሠረተ ጋብቻ አለመተማመን እንዲፈጠር በተወሰነ መልኩ ክፍተት ይፈጥራል:: ስለዚህ መተማመን የሰፈነበት የትዳር ሕይወት ለመምራት የሁለቱም ወገን ድንግልና አስፈላጊ ነው::

በእርግጥ ከዚህ ጋር በተያያዘ «ጉዳይ ከደም ጋር ከሆነ ዶሮ እረድ፣ ጣት ቁረጥ» ሌላም የሚሉ ዘመነኞች አይታጡም:: እነዚህ ወገኖች በአጭሩ የድንግልናን ምንነት ያልተረዱ ናቸው:: በሴት እኅቶቻችን ድንግልናቸውን በተፈጥሮና በሥራ ብዛት እንዲሁም ተገድዶ በመደፈር ንጽሕናዋን ልታጣ ትችላለች:: ይህ እንግዲህ በተወሰነ ደረጃ ንጽሕናን እንዳያጉድፍ በግልጽና በአግባቡ ለጓደኛ ማስረዳት ዓይነተኛ መፍትሔ ነው:: ሌላው ንስሐ ዘማዊን ድንግል ስለሚያደርግ፣ ንስሐ ገብቶ መጋባት አንድ የሕይወት አቅጣጫ ስለሆነ ድኅረ ንስሐ ተማምሎ በመጋባት አዲስ ሕይወት ለመምራት ይቻላል::

## ፍቅር

«የሺህ ፍልጥ ማሠሪያው አንድ ልጥ» እንዲሉ የጋብቻ ሕይወት ለዘላለም ጸንቶ እንዲኖር መሣሪያው ፍቅር ነው:: ፍቅር በዚህኛውም ዓለም ሆነ በወዲያኛው ዓለም የተረጋጋና የሰከነ ኑሮ ለመኖር ማረጋገጫም ነው:: በፍቅር ላይ ያልተመሠረተ ሰብአዊ ግንኙነት ሁሉ ሊሠምር አይችልም:: ፍቅር ድሃን

/ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል/



www.eotcmk.org

# ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም

*ባለፈው እትም ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም የኢየሱስ ክርስቶስን ቃልነት÷ በውላጤ ሳይሆን በተዋሕዶ ሰው መሆኑን በስፋት እንደ ሰበከ ተመልክተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ ሊቁ በነቢያት የትንቢት መጻሕፍት የተነገረውን ምሳሌ ከዘመነ ሐዲስ ጋር በማነጻጸር የሰበከውን «ምሥጢረ ሥጋዌ» እንቃኛለን፡፡*

/መምህር ኃይለ ማርያም ላቀው/

/ካለፈው የቀጠለ/

ቀደምት ነቢያት ስለ አምላክ ሰው መሆን የተለያዩ ምሳሌዎችን መስለዋል፤ ይኸውም ሰው እግዚአብሔርን እንደ ጌትነቱ መጠን በሥጋ ዐይን ሊመለከተው ባለመቻሉ ነው፡፡ እንግዲህ አምላካችን በቀላሉ በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ የሰዎች አእምሮ ሊረዳው በሚችለው መጠን ምሳሌዎችን አመላክቷል፡፡ ለምሳሌ፡– ለደገኛው ሙሴ በኋለኛው ዘመን የሚፈጸመውን የመለኮትንና የትስብእትን መዋሐድ በአምሳለ ነበልባል ወሐመልማል /በነበልባልና በሐመልማል ምሳሌ/ ዘጸ.3÷2–5/፣ ለጌዴዎን በጸምርና በጠል /መሳ.6÷37–40/ ለዳንኤል በደንጋ /ዳን.2÷34፣/ ለነቢዩ ኢሳይያስ በጉልበቱ ጽናት በሚራመድ፣ ስለ ጽድቅ በሚናገርና ለማዳንም በሚበረታ ሰው አምሳል /ኢሳ.63÷1/ ለነቢዩ ዕዝራ በሚያስፈራ አንበሳ የዘመነ ሥጋዌን ምሳሌ አሳይቷል፡፡

በዘመነ ብሉይ በነቢያትና በካህናት÷ በዘመነ ሐዲስ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በቅዱሳን ሐዋርያት የቀረቡትን ምሳሌያዊ (symbolic) እና ምሥጢራዊ /alligorical/ የሆኑ ጉዳዮች ለመረዳት መንፈሳዊ የሆነ ብቃትና ዕውቀት ይጠይቃል፡፡ መንፈሳዊ ብቃት ስንል ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቅን ያመለክታል፡፡ «ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው የእርሻውን እንክርዳድ ምሳሌ ተርጉምልን አሉት፡፡» እንዲል፡፡ ማቴ.13÷37፡፡ አባቶቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሰፈረውን ምሳሌ ለመረዳት ፈቃደ እግዚአብሔርን ቀን በስግደት ሌሊት ደግሞ በጸሎት ጠይቀዋል፡፡ በአጠቃላይ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የምናገኛቸው የምሳሌና የትርጉም ሥራዎች አበው ቀን በጽሕፈት ሌሊት በጸሎት ደክመው ያቆዩት ቅርስ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ሌላው የአንድን ምሳሌ ትክክለኛ ትርጉም ለመረዳት የሥነ ፍጥረት ዕውቀት ጠቀሜታ አለው፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ «ኮረብታው ዝቅ ይበል ጠማማው መንገድ ይቅና» ሲል የዚህን ምሳሌ ትርጉም ለመረዳት ኮረብታን ምን ዓይነት አቀማመጥ እንዳለው መገንዘብና ከሰዎች ሕይወት ጋር ማነጻጸርን ያስፈልጋል፡፡ የእንስሳትን ጠባይ ብናነሣ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እንስሳት ጠባይ በምሳሌ የተነገሩ በርካታ መልእክቶችን እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ ኃጥአን በፍየሎቹ ጻድቃንን በበጐች የተመሰሉበትን ምሳሌ ትርጉም ለማወቅ ስለ ፍየልና ስለ በግ ማወቅ ግድ ይላል፡፡

እንግዲህ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም «ነቢያት የመሰሉትን፣ሐዋርያት ያስተማሩትን የምሥጢረ ሥጋዌ ምሳሌዎች በልዩ ድርሰቱ ይሰብክልናል፡፡ ለዚሁም በቅዳሜና እሑድ የእመቤታችን የምስጋና ክፍል ውስጥ የሰፈሩትን በርካታ ምሳሌዎችን እንመለከታለን፡፡ «አንቲ ውእቱ ደብተራ እንተ ተሰመይኪ ቅድስተ ቅዱሳን ወውስቴታ ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኵለሄ ውስቴታ ጽላተ ኪዳን መሶበ ወርቅ እንተ መና ኅቡእ ዘውእቱ ወልደ እግዚአብሔር፤ ከተለዩ የተለየሽ የተባልሽ የኪዳን ጽላት ያለብሽ የተሰወረ መና ያለበት የወርቅ መሶብ ያለብሽ ደብተራ ድንኳን አንቺ ነሽ» ይላል፡፡

ከላይ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ያመሰገነበት ይህ ቃል መሠረቱን የጣለው በመጻሕፍተ ብሉያት ላይ ቢሆንም በሐዲስ ኪዳንም በሊቃውንት መጻሕፍት ውስጥ በስፋት ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በሐዲስ ኪዳን ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን ሰዎች የጻፈውን መልእክት የቅዱስ ያሬድን አንቀጸ ብርሃን በተባለው የምሥጋና መጽሐፍ መመልከት ብቻ በቂ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን በላከው መልእክቱ «ከሁለተኛውም መጋረጃ ወዲያ ቅድስተ ቅዱሳን የምትባለው ድንኳን ነበረች፤ በዚያች ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ፤ ሁለንተናውም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት በእርስዋም ውስጥ መና ያለበት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ፡፡ በላይም ማስተሰሪያውን የሚጋርዱ የክብር ኪሩቤል ነበሩ፡፡ ስለ እነዚህም ስለ እያንዳንዳቸው ልንናገር አሁን አንችልም ይላል፡፡ ዕብ.9÷3–5፡፡ ወረድ ብሎም ቁጥር ዘጠኝ ላይ «ይህም ለአሁኑ ዘመን ምሳሌ ነው» ይላል፡፡

ቅዱስ ያሬድ ደግሞ የሐዋርያውን መልእክትና ውዳሴ ሲያጠናክር በድርሰቱ አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ ከተለዩ የተለየሽ የመለኮት ማደሪያ ነሽ፡፡ ከፍጥረት ሁሉ ይልቅ የተከበርሽ ሆይ አብ የወደደሽ፣ወልድ ያደረብሽ፣መንፈስ ቅዱስ ያረፈብሽ /የጸለለብሽ/ ተባልሽ …፡፡ ቅዱሳን ነቢያት፣ ካህናት፣ ነገሥታት ያንቺ ምሳሌ አድርገው በውስጧ የኪዳን የሕግ ጽላት ያለባት ቅድስተ ቅዱሳን ከተለዩ የተለየችውን ሠሩ ይላል፡፡

እንግዲህ ቅድስተ ቅዱሳን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከተመለከን በኋላ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ያሉትን ንዋየ ቅድሳት ምሳሌና ትርጉም በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

## ቅድስተ ቅዱሳን

በአንዳንድ ቋንቋዎች ውስጥ አንድ ግሥ ወይም ቃል ከአንድ በላይ ትርጉም /ፍቺ/ ይዞ ይገኛል፡፡ ግዕዝ የቤተ ክርስቲያንና የጥንታዊት ኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በግዕዝ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ ግሶች ከአንድ በላይ ትርጉም አላቸው፡፡ ለምሳሌ «ቀደሰ» የሚለውን ግሥ ብንወስድ «አከበረ፣ አነፃ፣ ለየ፣አመሰገነ» የሚል ትርጉም አለው፡፡ እነዚህን መሠረታዊ ፍችዎች ይዘን «ቅድስተ ቅዱሳን» የሚለውን ኃይለ ቃል ስንተረጉም ከተለዩ የተለየች ከከበሩ የከበረች ከነፁ የነፃች፣ ከተመሰገኑ የተመሰገነች የሚሉ ትርጉሞችን እናገኛለን፡፡

በዘመነ ብሉይ እስራኤል በምድረ በዳ ሲጓዙ ሃይማኖታዊ ሥርዓትን ሁሉ በመካከላቸው ባለው በእግዚአብሔር ድንኳን ይፈጽሙ ነበር፡፡ ይህ ድንኳን በሌላ አነጋገር «የመገናኛ ድንኳን፤ የእግዚአብሔር ፊት» ይባላል፡፡ ዘጸ. 16÷33፣ሉቃ.1÷9፡፡ እስራኤል ወደ ምድረ ርስት ከገቡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ቅዱስ ዳዊት «እኔ በዝግባ በተሠራ ቤት እየኖርኩ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት በድንኳን ለምን ትኖራለች?» ብሎ ቤተ መቅደስን ለመሥራት ሲፈልግ እግዚአብሔር



www.eotcmk.org

ከለከለው፤ 1ዜና.22÷8:: ነገር ግን የሚያስፈልገውን ድንጋይ እንጨት ወርቅና የከበረ ድንጋይና ሌላውንም ሰብስቦ ለልጁ ለሰሎሞንም እንዲሠራው አደራ ሰጠው:: 1ዜና.22÷3-5:: ሰሎሞን እንደ አባቱ ትዕዛዝ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አብርሃም ይስሐቅን ለመሥዋዕት ባቀረበበትና ዳዊት በገዛው ሥፍራ እጅግ ውብ አድርጐ ሠርቷል:: በቤተ መቅደሱ ግራና ቀኝ ሁለት አዕማድ ቆመው ነበር:: 2ዜና.3÷4-15:: ውስጡም ለሦስት የተከፈለ ሲሆን ውስጠኛው ክፍል ቅድስተ ቅዱሳን ይባል ነበር:: 1ነገ.8÷6-10::

የመጀመሪያው ክፍል የሕዝብ መጸለያ ተብሎ ይጠራል:: ይህም ክፍል የወንዶች አደባባይና የሴቶች አደባባይ ተብሎ በሁለት ይከፈላል:: በሁለተኛው ክፍል ካህናት የዕለት አገልግሎት ይፈጽሙበታል:: ካህናቱ አገልግሎት ከሚፈጽሙበት ከሁለተኛው መጋረጃ ወዲያ ሦስተኛ ክፍል አለ:: ሦስተኛዋ ክፍል ቅድስተ ቅዱሳን ተብላ ትጠራለች:: ዘጸ. 25÷8:: ዘሌዋ.24÷5-6:: ዕብ.9÷3:: እግዚአብሔር ባሪያውን ሙሴን በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ፤ እኔ እንደማሳይህ ሁሉ እንደማደሪያው ምሳሌ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ እንዲሁ ሥሩት በማለት ያዘዋል:: ዘጸ.25÷8-9:: ይኸውም ሕዝቡ ጸሎት የሚጸልዩበት ካህናቱ የዕለት አገልግሎት የሚፈጸሙበት ሊቀ ካህናቱ ከዓመቱ አንድ ቀን በመግባት መሥዋዕት የሚያቀርቡበትና እግዚአብሔርን የሚጠይቁበት ሥፍራን ያጠቃልላል::

የብሉይ ኪዳን የካህናት አገልግሎት ዕለታዊ፣ሳምንታዊና ዓመታዊ ተብሎ በሦስት ይከፈላል:: ዘጸ.29÷38፤ 30÷8፤ ዘሌ.24÷5-9፤ዘሌ.16÷1::

የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት በማስተሥረያ ቀን ዓመታዊ አገልግሎቱን ለመፈጸም በዓመት አንድ ቀን የከበረውን መሥዋዕት በመያዝ ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ሥርየት እግዚአብሔርን ለመጠየቅ /ለመማጸን/ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባ ነበር:: ይህ ሥርዓት እግዚአብሔር ለሙሴ ከገለጸለት በኋላ በወንድሙ አሮን ሊቀ ካህናትነት ሲፈጸም ኖሯል::

በሐዲስ ኪዳን ግን ከላይ የተሠሩት ሥርዓቶች ምሳሌዎች ወይም ምሥጢራት ተብለው ይጠራሉ:: በብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን ከሌሎቹ ከሕዝቡ መቆሚያ ከካህናት ዕለታዊ አገልግሎት መፈጸሚያ የተለዩች የተከበረች የነፃች በመሆኗ ቅድስተ ቅዱሳን ተብላለች:: በውስጧም የሊቀ ካህናቱ መገልገያ የወርቅ ማዕጠንት፣ ሁለንተናዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት፣መና ያለበት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳን ጽላትና ማስተሥሪያውን የሚጋርድ የክብር ኪሩቤል ይገኛል:: ከእነዚህ ንዋየ ቅድሳት ሊቀ ካህናቱ የወርቅ ማዕጠንት ይዞ ዕጣን ጨምሮ በመግባት የመንበሩን ዙሪያ በማጠን ዕጣንንም ያሳርጋል:: ሌላው ሁለንተናዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት ስትገኝ ይህችም ሊቀ ካህናቱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገርባትና ድምፅ የሚሰማባት ነች:: «ኪዳን» መዋዋል፣መስማማት፣መማል ተብሎ ይተረጐማል:: «ታቦት» ማደሪያ ማለት ሲሆን ይኸውም እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን የሚፈጽምበት፣ሕዝቡን የሚያገዝበት ከሊቀ ካህናት ጋር የሚገናኝበት የሚያድርበት ስለሆነ የቃል ኪዳን ማደሪያ ያሰኛል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት በታቦቱ ስለሚያድር ነው:: በሦስተኛ ቅደም ተከተል የምናገኘው «መና ያለባት የወርቅ መሶብ» ሲሆን ይህም እስራኤል በቃዲስ በረሃ መና ከሰማይ እየወረደላቸው ተመግበዋል:: ዘጸ. 16÷16::

ይህን መና ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ ልጆች በጠየቁ ጊዜ እግዚአብሔር በበረሃ መና እንደመገባቸው ለመታሰቢያ በወርቅ መሶብ እንዲያስቀምጠው የታዘዘ ነው:: ዘጸ. 16÷33:: ሳይተክሏት የበቀለች የአሮን በትርም ተከታይ ነች:: ይህች በትር ውኃ ሳያጠጧት ሳይኰተኩቷት አብባ አፍርታ ተገኝታለች:: በዚያን ዘመን የቆሮ ልጆችና የአቤሮን ልጆች ሙሴንና አሮንን ይቃወሟቸው ነበር:: ደቂቀ ቆሬ የአሮንን ክህነት ለመንጠቅ በድፍረት ማዕጠንተ ወርቅ ይዘው ባጠኑ ጊዜ ይቀስፋሉ:: ስለዚህ እግዚአብሔር የአሮንን ክህነት ለዘላለም መታሰቢያ እንዲሆን አሥራ ሁለቱም ነገድ በትራቸውን ይዘው እንዲመጡ ተደርጓል:: እግዚአብሔር የአሮንን ክህነት መምረጡን ለመግለጽ የአሮን በትር ውኃ ሳያጠጧት እንድታብብ እንድታፈራ አድርጓል:: የኪዳኑ ጽላት ሕጉ የተጻፈበት ሰሌዳ ሲሆን ብዛቱም ሁለት ነው:: ይኸውም በታቦቱ ውስጥ ይቀመጣል:: ሕጉ በደብረ ሲና እሥራኤላውያን እንዲጠብቁት የታዘዘ ነው:: የክብር ኪሩቤል የሚባለው እግዚአብሔር ሙሴን ታቦት ከቀረጸ በኋላ «አራቱን ኪሩቤል ክንፋቸውን ዘርግተው የአንዱ ክንፍ ካአንዱ ክንፍ ጋር እንዲገናኝ አድርገህ ቅረጻቸው» ብሎታል:: ይህ እንግዲህ በብሉይ ኪዳን የነበረውን የአገልግሎት ሥርዓት የሚያመላክት ነው::

## ከተለዩ የተለች

ከሁለተኛ መጋረጃ ወዲያ የምትገኘው ክፍል ከሕዝቡ መቆሚያና ከካህናት መገልገያ ልዩ በመሆኗ ቅድስተ ቅዱሳን እንደተባለች እመቤታችንም በንጽሕናቸው በቅድስናቸውና በድንግልናቸው ቅዱሳንና ቅዱሳት ተብለው ከተጠሩት ትለያለች:: ምክንያቱም እነዚያ ከገቢር ቅዱስ ቢባሉ በሐልዮ ቅዱስ ሊባሉ አይችሉም:: ከተግባር /ከመፈጸም/ እንጂ ከማሰብ ንጹሕ /ቅዱስ/ መሆን አይቻላቸውም::

በዚህ ዓለም ንጽሕ ጠብቀው ከሴት ርቀው፣ግርማ ሌሊቱን፣ድምፀ አራዊቱን ታግሰው በመጸለይ ዓለምን ዙረው በማስተማር፣ገንዘባቸውን በመመጽወት እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ብዙ ቅዱሳን አሉ:: ከእነዚህ አንፃር የተለየች ተብላለች:: ይኸውም አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልዳ በመገኘቷ ነው:: ቅዱሳን የተባሉት ሁሉ የፈጣሪያቸውን ፊት ለማየት ስለእርሱ አመሥጥረውና አራቀው ለመናገር ባሕሪያቸው አይፈቅዳላቸውም ነበር:: አባ ሕርያቆስ «ወሶበ እሔሊ ዘንተ ይፈቅድ ሕሊናየ ይጽብት ዕመቀ አብሕርቲ ለወልድኪ ወያመዓ ብሎ መዋግደ ምስዋሪቲሁ ለፍቁርኪ፤ ኅሊናዬ ወደ ሰማይ መጥቆ የመላእክትን አኗኗር ወደ ጥልቁ ወርዶ የአጋንንቶችን ወደ ምድር ዙሪያ ተጉዞ የምድርን ወሰን ድንበር፣ስፋት ወደ ሰማይ ወጥቶ ጽርሐ አርያምን መንበረ ጸባኦትን ለመመርመር ይፈልጋል:: የልጅሽ ባሕርይ አልመረመር ይለውና ከዚያ ካለበት ሥፍራ አይነሳም» ይላል:: /ቅዳሴ ማርያም/ እመቤታችን ግን ሰማይና ምድር ሊወስኑት የማይቻላቸውን ወስና በመገኘቷ ሊቁ ቅዱስ አፍሬም ቅድስተ ቅዱሳን፤ ከተለዩ የተለየች ይላታል::

## ከከበሩ የከበረች

ሌሎችን ቅዱሳን የምናከብራቸው ታላላቅ ቅዱሳን በመውለዳቸው እንዲሁም የሃይማኖት ሰዎች ሆነው በመገኘታቸው በመልካም ሥራቸው እግዚአብሔር ቃል ስለገባላቸው በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር ሕይወታቸውን ለዓለም አርአያቸውን መልካም ሥራቸውን መሥዋዕት አድርገው በማቅረባቸው ክቡራን ተብለው ይጠራሉ:: እመቤታችን «ከከበሩ የከበረች» ብሉ ሊቁ የሚያመሰግናት የአምላክ እናት ስለሆነች ነው:: ሊቃውንት «መትህተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን፣ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች» ይሏታል:: ስለዚህ ከከበሩ የከበረች ተብላ ትጠራለች::

*ይቀጥላል*



www.eotcmk.org

# የጥምቀት ንባብ በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ

⇒ መጽሐፈ ምሥጢር

*በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከተነሡት ሊቃውንት ውስጥ ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ ስሙ የሚጠራ ሊቅ ነው። ፀዊ ዳዊት ኢትዮጵያው ቄርሎስ ብሉ ጠርቶታል። የተወለደው በወሎ በረና ልዩ ስሟ ሽግላ በተባለች ቦታ በ1358 ዓ.ም. ሲሆን ያረፈው ሐምሌ 7 ቀን 1458 ዓ.ም ነው።*

*በሕይወት ዘመኑ ከ40 በላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን የደረሰ ሲሆን ከነዚህም መካከል የታወቁት ሰዓታት፣ አርጋኖንና መጽሐፈ ምሥጢር ናቸው።*

*መጽሐፈ ምሥጢርን የጻፈው በዕድሜው መጨረሻ መሆኑን ገድሉ ይገልጣል። በዚያ ጊዜ ተጻክሞ ስለነበር አራት ጸሐፊዎች ተመድበውለት ለአራቱም እየነገረ አስፍቶታል። በመጨረሻም የሁሉንም ጸሐፍት አገጣጥሞ መጽሐፈ ምሥጢር ብሎታል። በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ላይ አባ ጊዮርጊስ መጽሐፈ ምሥጢርን የጻፈው ብራንካሌዎን የተባለ ፈረንጅ /ካቶሊክ/ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት በመጠየቁ መሆኑን ያስረዳና ዘመኑን በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ያደርገዋል። ገድሉ እንደሚለው ግን አባ ጊዮርጊስ ያረፈው በዐፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት ነው።*

*ይህ መጽሐፈ ምሥጢር በዚያው ዘመን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሻገር መብቃቱን ገድለ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ያስረዳል።*

እንደ ናዝራውያን ሥርዓት በምንሠልሰው፥ እንደ ሱራፌል በምንቀድሰው በጽርሐ አርያም አትሮንሱን ባስቀመጠ በእግዚአብሔር ስም የሚች ኀሊና የማይፈልገው፣ የሰው እጅ የማይዳስሰው፣ በተራሮች ጫፍ ላይ የጭጋግ ተንን የሚያጠፋው፥ ያለ ጨኸት የሚያሻሽለው፥ በአየሮች ውስጥ የሚያታግል ሰፌውና የሰማይን ፊት የደመና መጐናጸፊያ የሚያለብስ ለእርሱ ክብር ምስጋና ለዘላለም ይገባል። አሜን።

*«ወልድ አብን በእርሱ ላይ ስላለ ክብር ያየው ዘንድ አይችልም፤ መንፈስ ቅዱስ ወልድ በእርሱ ላይ ስላለ ክብር ያየው ዘንድ አይችልም፤ መላእክት መንፈስ ቅዱስን በእርሱ ላይ ስላለ ክብር ያዩት ዘንድ አይችሉም፥ የሰው ልጆች በእነርሱ ላይ ስላለ ክብር የሰማይ መላእክትን ይመለከቷቸው ዘንድ አይችሉም፤»* የሚልን የአርጌንስን ዘለፋ እንመለከታለን።

አምስት መዓርግ ሠርቶላቸው አልተመለከቱትም። በጠባዩ አዋኪ፣ በአንደበቱ ሸንጋይ፣ ዋዛ ፈዛዛ የሚወድ፣ በዐይኑ ትዕቢተኛና ልቡ የተነፋ አርጌንስ በእስክንድርያ አብያተ ክርስቲያናት ሁከትን ይዘራል። በግብዕ አውራጃዎች እሾኽን ዘራ። ከኤጺስ ቆጶሳት የተለየ ትምህርት ያስተምራል። ክፋትን ሳያደርግ አይተኛም። አመለካከቱ ግን ከመናፍቁ አርዮስና ሹመትን ከሚወድ ሚሊጢስ ጋር አንድ ነው። አርዮስ ስለ ክሕደቱ በንጉሥ ርዳታ ምእመናንን አሳድዶ ቤተ ክርስቲያንን በትኗል። ከዚህ በኋላ በርቱዓ ሃይማኖት በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመን 318ቱ ሊቃውንት በኒቂያ ጉባኤ በአደረጉ ጊዜ ጸንታ ቆመች። ሚሊጢስ የቅዱስ ጴጥሮስን ጵጵስና በመንጠቅ ቤተ ክርስቲያንን ጨቁኗል። ትችቱ ግን ስለ ሃይማኖት ፍቅር አይደለም። ሹመትን በመውደድ እንጂ። አርጌንስ ግን ሃይማኖትን በመለወጥ ሁከትን በማድረግ ነው፤ የወልድን ከአብ ማነስና የመንፈስ ቅዱስን ከወልድ ማነስ ያስተምራልና። አርጌንስ እንዴት ወልድ ከአብ ያንሳል አለ? ከወንጌል ቃል፡- «የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር» የሚለውን ምክንያት አደረገለት። አብ ወል ድን እንደ ንስር ክንፎች መምታትና እንደ ዐይን ጥቅሻ ያህል በሰዓትና በዕለት ሳይቀድመው እንዴት ይበልጠዋል? እንደ ገና /ዳግመኛ/ «ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፥ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ፥ ወደ ሰማይ አርጋለሁ» አለ። ከዕርገቱ አስቀድሞ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ ማለቱ ግን የትስብእትን ጉዳና ትሕትና ሲያሳይ ነው። ለእነርሱ የጸጋ አባታቸው ነው። ለእርሱ ግን የባሕርይ አባቱ ነው። ለእነርሱ አምላካቸው ነው። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ነው።... በኦሪት «አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» የሚለው የእግዚአብሐር ቃል ተፈጸመ። ስለ አብና ወልድ እኩልነት /ዕሪና/ ጌታችን በወንጌል «እኔና አብ አንድ ነን» አለ። ዳግመኛ ፊልጶስ ጌታችንን «አብን አሳየንና ይበቃናል» ያለውን ሰማ። «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እኔን ያየ አብን አይቷል።» /እኔን ያየ አባቴን አይቷል/ አለው። እንደ ገና «እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን?» አለ። ዳግመኛ «አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ አለ። ከሰማይም አከበርኩህ ዳግመኛ አከብርሃለሁ የሚል ቃል መጣ።» ዮሐ.12÷28።

አርጌንስ ሆይ! ወልድ በአባቱ ዘንድ እንደ ተከበረ ዕወቅ /አስተውል/፤ አባቱ ካከበረው እንዴት ያንሳል ትለዋለህ? አንተ ከክርስቲያን ክብር ትጐድላለህ እንጂ ወልድን ከአባቱ ዘንድ ጉድለት የሚያገኘው አይደለም። ስለ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ እንደሚያንስ ስትናገር አትታዘብምን? በወንጌል፡- «እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣው የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ» የሚለውን ሰማ። «ከአብ ዘንድ ይወጣል» ባለህ ጊዜ በእዚህ እንኳ አታስተውልምን? ከእርሱ የሚወጣ ከሆነ እንግዲህ እንዴት አይመለከተውም? በማስከተልም፡-«እናንተም ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ» ይላል። ከመጀመሪያ ከእርሱ ጋር ከነበረ እንዴት አይመለከተውም? እንዴትስ ከእርሱ ያንሳል? ቅዱስ ጳውሎስም «እንዲህ ከሆነ የእግዚአብሔርን ልቡን ማን ያውቃል? መካሩስ ማነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን። እኔም ወንድሞች ሆይ፥ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም» አለ። እነሆ ቅዱስ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን «የክርስቶስ ልብ» በማለት ሰየመው። እርሱ የክርስቶስ ኅሊና ከሆነ እንዴት አይመለከተውም? ኅሊና ፊትን ከመመልከት ይበልጣልና፤ ልብን መመርመር የውጭን ከመመልከት ይበልጣልና፤ ዳግመኛ ቅዱስ ጳውሎስ «መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ግን ኹሉን ይመረምራል። እርሱን ግን የሚመራመረው የለም፤ እኛ ግን የተሸሸገውን የሚገልጥና የተደበቀውን የሚመረምር የእግዚአብሔር ልብ አለን» አለ። ሰነፉ ሆይ፥ ወልድም አብን እንደ ሚመለከተው ዕወቅ /አስተውል/።

እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል። ስለ መንፈስ ቅዱስ አስቀድመን ነግረናችኋል። እናንተ ዝንጉዎች ከእንግዲህ «ወልድ ከአብ ያንሳል፤ አይመለከተውም» አትበሉ። «መንፈስ ቅዱስም ከወልድ ያንሳል፤ አይመለከተውም» አትበሉ።

እኛ ግን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ባሕርይ፥ አንድ መንግሥት፥ አንድ ምልክና፥ አንድ መለኮት፥ አንድ ሐሳብ፥ አንድ ፈቃድና ሥርዓት እንደ ሆኑ እናምናለን። ፈቃዳቸው፥ ሕግና ሥርዓታቸው ችሎታቸው አንድ ነው። እንደ አሕዛብ አማልክት በየሥርዓታቸው ሦስት አማልክት አይሏቸውም። በሦስትነት ያለ አንድ አምላክ ይሏቸዋል እንጂ እንደ አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ አንዱ ከአንዱ ቀድሞ እንደ ነበረ፥ አንዱ አንዱን ሁለተኛው ሦስተኛውን አይከተለውም። የዐይን ቅንድቦች አገላለጥና የመብረቅ ብልጭታ ያህል አብ ከወልድ፥ ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ የቀደመ ህልውና የለውም። እናታችሁ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ



www.eotcmk.org

ትታመናለች:: «አቤቱ÷ በድንኳንህ
ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰ ውም
ተራራህ ማን ይኖራል?» ተብሎ እንደ
ተጻፈ በሙሽራዋ ተደስታ በወልድ
ክንድ ላይ ታርፋለች:: «ግራው ከራሴ
በታች ናት፤ ቀኙም ታቅፈኛለች»
ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ «ቅዱስ መንፈስህ
በጽድቅ ምድር ይመራኛል» ተብሎ
እንደ ተጻፈ በመንፈስ ቅዱስ ብርሃን
መብራትነት ወደ ገነት ድንኳኖች ትመ
ራለች:: ከዚህ በኋላ በአብ በወልድ
በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅ ፈልጋ
ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ትጓዛለች:: ወደ
ዮርዳኖስ ወንዝ ወርዳ መጀመሪያ ከዮር
ዳኖስ ወንዝ ከወጣች በኋላ የክርስቶስ
ባሪያ ትባል ዘንድ የቅብዐ በለሳን
ማኅተም ትቀበላለች:: ቅብዐ በለሳን
የሃይማኖት ኃይል ነውና:: ሐዋርያት
በዲድስቅልያ ትምህርት እንደ ተናገሩ
ት በጥምቀት መወለድ ግን /ክርስቶስ/
ከድ ንግል የተወለደውን ልደት
ይመስላል:: ክርስቶስ ከድንግል ማርያም
እንደ ተወ ለደ ከእርሷ ከተወለደ በኋላ
ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይፈታ በድን
ግልና ማኅተም ተገኘ:: እንደዚሁም
ከጥምቀት ሆድ ወጥተን የምንወለደው
ይህ ልደት ከጥምቀት ሆድ ከውኃ
ወጥተን በመጠመቂያ ውስጥ የመግቢ
ያና የመውጫ ፍለጋው አይገኝም::
በመዝሙር «መንገድህ በባሕር ውስጥ
ነው፤ ፍለጋህም በውኃ ውስጥ ብዙ
ነው፤ፍለጋህም አይታወቅም» ተብሎ
እንደ ተነገረ ::

እንግዲህ ወደ ተውነው ወደ
ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነገር እንመ
ለስ:: ከዚህ በኋላ ከቅዱስ ጳውሎስ
ቃል:- «በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት
እግ ሮቻችሁ ተጫምተው» የሚለውን
ሰምታ አካሄዷን አሣምራ ወደ ቤተ
እግዚአብሔ ር ትወጣለች:: ዳግመኛ
ቅዱስ ጳውሎስ «በራሳችሁ፤ በእጃችሁም
የመንፈስ ቅዱ ስን ሰይፍ ያዙ» ብሎ
እንደ ተናገረ በራሷ ላይ የዕንቁ ጌራ
ትደፋለች:: ይኸውም የሃይማኖት አክሊ
ል ነው:: በእጇቿም የክብር ቀለበት
ታጠልቃለች:: ይኸውም የድኅነት ምል
ክት÷ የጸጋ ማኅተብ ነው:: ከዚህ በኋላ
አብርሃም ወደ ሚቀመጥበት ይስሐቅም
በተሠዋው በግ ወደ ተቤዠበት ወደ
ሰርግ ቤት ዐጸድ ትገባለች:: አባታችን
ያዕቆብ:- «የወርቅ መሰላል ከምድር
እስከ ሰማይ ተተክላ የእግዚአብሔር
መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ወደ
ተመለከ ተበት÷ ሙሴ ስለ እስራኤል
ልጆች ዘለፋ ምስክር ይሆኑ ዘንድ
የትእዛዝና የሕግ ጽላትን ወደ ተሸከ
መበት ቦታ÷ መልከ ጼዴቅ ኅብስትና
ወይን ለቤተ ክርስቲያን ምሥጢር
ሥርዓት ወዳ ወጣበት ቦታ÷ ዳዊት
በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት
ፊት:- «አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ÷
አንተና የመቅደስህ ታቦት» እያለ ወደ
ሚዘምርበት ቦታ÷ አሳፍ ወደ ሚቃ
ኝበት÷ የቆሬ ልጆች በመሰንቆ ወደ
ሚያመሰግኑበት ቦታ÷ ነቢዩ ኢሳይያስ
ለወዳጁ ምስጋና እያለ ወደ
ሚዘምርበት ቦታ፣ ኤርምያስ ደጋ
ሰንጥቆ ወደ ውስጧ የአዳራሽ ድንኳን
መሥሪያ ዕቃ አስቀምጦ የደጋዩን ስባሪ
አተማት:: እንደ ብረት መሸፈኛ
ሆነችው፤ መከፈቻዋንም ለዐሐይ ሰጠ፤
ኤልያስ የእግዚአብሔር መልአክ የሰጠ
ውን የተዘጋጀ እንጀራ በልቶ በዚያም
ምግብ ኃይል አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
ወደ ተጓዘበት ቦታ÷ ዕዝራ ሱቱኤል
ከዑራኤል እጅ የምስጋና ጽዋን ጠጣ::
የትእዛዝና የሕግ መጻሕፍትን የምታ
ስተውለው ልቡናው በደረቱ ውስጥ
ከብዶ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት አፉ
ሳይዘጋ ወደ ተቀመጠበት÷ ዘካርያስ
ነጫጭና ዝንጉርጉራን ፈረሶችን ወደ
ተመለከተበት÷ ሕዝቅኤል የእሳት ሠረ
ገላ ወደ ተመለከተበት÷ ዳንኤል በዘመ
ናት የሸመገለ ሽማግሌ ከሰው ልጅ
ጋር በላዩ ላይ ተቀምጦ መንበሮችን
ወደ ተመለከተበት÷ እንባቆም በሁለ
ት እንስሳት መካከል እግዚአብሔርን
ወደ ተመለከተበት÷ ሁሉም ነቢያት
በትንቢት አርጋኖን ስብከት ወደ ሚያ
ሰሙበት÷ የገሊላ ሕፃናት አጥንትን
በሚያለመልም÷ ልቡናን ሰውሮ ኅሊናን
በሚመስጥ በቃለ ማኅሌት ወደ
ሚያመሰግኑበት÷ ቅዱስ ጴጥሮስ የመን
ግሥተ ሰማያት መክፈቻን ወደ
ተቀበለበት÷ ቅዱስ ጳውሎስ የቤተ
ክርስ ቲያን ብርሃን ይሆን ዘንድ ወደ
ተጠራበት÷ ዮሐንስ ምሥጢረ መለኮ
ትን እየሰበከ እንደ ነበር ቃል ወደ
ሚጮኽበት÷ ሁሉም ሐዋርያ በመንፈስ
ቅዱስ መውረድ መክፈቻን ወደ
ተቀበለበት ÷ ዮሐንስ ምሥጢረ መለ
ኮትን እየሰበከ እንደ ከበሮ ቃል ወደ
ሚጮኽበት÷ ሁሉም ሐዋርያ በመንፈስ
ቅዱስ መውረድ የእሳት ፍሳሽ ወደ ጠ
ጡበት÷ የመላእክት ማኅበር የእግዚ
አብሔርን መሠዊያ ለማየት ወደ
ሚጨነቁበት÷ የሰማዕታት ማኅበር
የመከራቸውንና የድካማቸውን ዋጋ
አክሊል የተቀዳጁበት÷ የደናግልና
የመነኮሳት ማኅበር የድካማቸውን ዋጋ
አክሊል ይቀዳጃሉ:: ከዚህ በኋላ በሙሽ
ራዋ ደጃፍ ውስጥ ለምእመናን ምሳ
ሙሽራው ይታረዳል:: በመሠዊያው
ቀንድ ውስጥ ደሙ ሲንጠባጠብ
በተመለከተች ጊዜ አንጀቷ ታወከ::
ጉልበቶቿ ራዱ:: ሥጋውን በፍርሃት
ትበላለች፤ ደሙንም በመንቀጥቀጥ
ትጠጣለች:: ...

እነሆ በቅድስት ሥላሴ መለኮት
ላይ ስድብን የሚናገር የአርጌንስን
ዘለፋ ፈጸምን:: ፍጥረትን ሁሉ ለሚገዛ
ለአብ ምስጋና ይገባል:: ለመንግሥትና
ለነገሥ ታት ጌታ ለወልድ ምስጋና
ይገባል:: ልብንና ኩላሊትን ለሚመ
ረምር ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና
ይገባል:: ለዘላለሙ አሜን::

*ይቀጥላል::*

## ዘመነ መርዓዊ... /ከገጽ ፰ የዞረ/

ከሀብታም፣ እናትን ከልጅ፣ሠራተ
ኛን ከአሠሪ፣ባልን ከሚስት አስተሳ
ስሮ አንዲትን ሀገር እንዲገነቡ የሚ
ያስችል ኃይል ነው::

«ይስሐቅም ርብቃን ወደዳት÷
ሚስትም ሆነችው» የሚለው ኃይለ
ቃል ለተጋቢዎች ፍቅር ቀዳማዊ
ጉዳይ መሆኑን ያመለክተናል::
ርብቃ ሚስት የሆነችው ከወደዳት
በኋላ ነው:: እርሷን የመወደዱን
ዋጋ ከእርሷ አግኝቷል:: ቢያንስ በእ
ናቱ ሞት የተጽናናው በእርሷ ነው::
ይህ እንግዲህ ርብቃን በመ ውደዱ
ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘው የፍቅር
ዋጋ ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳው
ሎስ በባልና ሚስት መካከል ሊኖር
የሚገባውን ፍቅር ክርስቶስ ቤተ
ክርስቲያንን ከወደደበት ዓይነት
ፍቅር ጋር ያነጻጽረዋል:: «ባሎች
ሆይ÷ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስ
ቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶ
ቻችሁን ውደዱ::» ይላል:: ኤፌ.
5÷26:: ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን
ራሱን አሳልፎ ሰጥቷል:: ለቤተ
ክርስቲያን ሞቷል:: ባል ለሚስቱ
ይህን የመሰለ ፍቅር ሊያሳያት
ይገባል:: ሐዋርያው በመጨረሻ
የባልንና የሚስትን የጋራ ሓላፊነትን
ሲገልጽ «ከእናንተ ደግሞ እያን
ዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ
ራሱ አድርጎ ይውደዳት፤ ሚስትም
ባልዋን ትፍራ /ታክብር/» ይላል::
ኤፌ.5÷ 33:: ፍቅርን ለለገሠ
የትዳር ጓደኛ አክብሮትንና ፍቅርን
መቸር ከሚስት ይጠበቃል::

እንግዲህ ዘመነ መርዓዊንም ሆነ
ከጾም ውጪ የሆኑትን ወራት ተን
ተርሰን ጋብቻን የምንመሠርት ወገ
ኖች ከላይ ከተመለከትናቸው የት
ዳር ሰዎች ለትዳራቸው ሥምረት
የተከተሉትን የሕይወት አቅጣጫ
ከተከተልን በትዳራችን ውጤታማ
ልንሆን እንችላለን:: እንደ ኢዮብ
ሚስት በፈተና ወቅት ከሚመጣ
ስንፍና ተጠብቀን እንደ ይስሐቅና
ርብቃ በጸሎት፣ በድንግልናና በፍ
ቅር ላይ የተመሠረተን የጋብቻ ሕ
ይወት ለመኖር የሠራዊት አምላክ
እግዚአብሔር ይርዳን:: አሜን::



www.eotcmk.org

# ተአምረ ማርያም

## ታሪኩ ✱ ምንጩ ✱ ይዘቱ ✱ተአማኒነቱ

*ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ በተአምረ ማርያም የጸሎት መጽሐፍ ዙሪያ ሰፋ ያለ ትምህርት እንድንሰጣቸው በርካታ አንባብያን በልዩ ልዩ መንገዶች ሲጠይቁን ቆይተዋል:: እኛም ከዚህ እትም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያናችን ሰፊ አገልግሎት ስላለው ስለዚህ መጽሐፍ ማስተማር እንጀምራለን:: መልካም ንባብ::*

በቤተ ክርስቲያናችን ከሚታወቁት ቅዱሳት መጻሕፍት አንዱ ተአምረ ማርያም ነው:: ተአምረ ማርያም በቤተ ክርስቲያን የንባብና የጸሎት ሥርዓት ውስጥ ሁነኛ ቦታ ካላቸው መጻሕፍት /Liturgical Books/ መካከል አንዱ ሲሆን ከሰዓታት፣ከቅዳሴ በኋላና በልዩ ልዩ የጉባኤ ጸሎቶች ጊዜ ይነበባል:: በሌላ በኩል በቤተ ክርስቲያናችን ተአምራትን ብቻ በማካተታቸው የተአምር መጻሕፍት የሚባሉት ሁለት መጻሕፍት ብቻ ሲሆኑ እነርሱም ተአምረ ማርያምና ተአምረ ኢየሱስ ናቸው:: የሌሎቹ ቅዱሳን ተአምራት በየገድላቸው ተካትቶ ወይም ለብቻ ቦታ ተሰጥቶት ይገኛል::

ተአምረ ማርያምን በተመለከተ ሊነሣ የሚገባው ሌላው ነጥብ በብራና ከተጻፉት /በተለይ በማይክሮ ፊልም ከተቀረፁት/ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት መካከል ከመዝሙረ ዳዊት ቀጥሎ በብዛት ሁለተኛውን ቁጥር የያዘ መሆኑ ነው:: ይህም በቤተ ክርስቲያን ጸሎት መጽሐፉ ያለውን ቦታ ያመለክታል::

የተአምረ ማርያምን አስፈላጊነት /Authenticity/ እና ተአማኒነት /Validity/ ለመቀበልና ለመተንተን እንዲቻል «ተአምር» የሚለውን ቃል ጽንሰ ሐሳብ መተንተንና ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት አንጻር መመልከቱ የግድ ይላል:: ስለሆነም ከሁሉ አስቀድመን ይህን እንመለከታለን::

### ተአምር ምንድን ነው?

ይህን ጥያቄ ለመመለስ የተለያዩ ሊቃውንት ሰፋ ያለ ትንታኔ ሰጥተዋል:: ተአምራት በነገሮች አካላዊም ሆነ ኅሊናዊ ሥርዓት የሚፈጠሩ ክስተቶች ወይም ሁነቶች ሲሆኑ እነርሱም ለሰው ድኅነት የሚረዱ ሁኔታዎች ናቸው:: እነዚህ ነገሮች በተለመደው የተፈጥሮ ሕግና ሥርዓት መሠረት ሊተነተኑ ወይም ሊነገሩ አይችሉም፤ ሁሉም የእግዚአብሔር ሥራዎች ናቸውና:: /Enyclopedia of Catholic Devotions and Practices: 356/.

«ተአምር የተፈጥሮን ሕግ ባልጠበቀ ሁኔታ ወይም ከተለመደው ነገር ውጭ የሚከሰት ሁኔታ ነው:: ይህም የእግዚአብሔር ወይም የሌላ ከዚህ ዓለም ውጭ የሆነ ኃይል ውጤት ነው:: ስለዚህም የመልእክቱ ወይም የመልእክተኛው ምንጭ መለኮታዊ ኃይል ነው::» /Eerdmans: 722/ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም «ተአምር» የሚለውን ቃል ሲገልጡ:- «ድንቅ ምልክት፤ እንደ ነቢያት እንደ ሐዋርያት በእግዚአብሔር ኃይል በክርስቶስ ስም ካልኾነ በቀር ማንም ሰው ሊሠራው የማይችል ልዩ ድንቅ ጉድ ብርቅ የኾነ አምላካዊ ሥራ» ብለዋል:: /መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ÷ ገጽ፣ 428/::

አንድን ክስተት «ተአምር ነው» የሚያሰኙት የሚከተሉት ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች ናቸው:: የመጀመሪያው የሚፈጠረው ክስተት ከተለመደው የተፈጥሮ ሕግና ሥርዓት ውጭ መሆኑ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ክስተቱ የሚፈጸመው ከመለኮት በሚሆን ኃይል መሆኑ ነው:: ሦስተኛው ለሰው ልጅ ድኅነት ሲባል የሚፈጸም መሆኑ ነው::

ይህን ጉዳይ በምሳሌ እንመልከተው:: የኤርትራ ባሕር ከሁለት ተከፍሎ ሕዝበ እስራኤል በደረቅ መሬት ተሻግረዋል:: ዘጸ.14÷30:: የውኃው በበትር መከፈልና እንደ ግድግዳ መቆም ከተፈጥሮ የስበት ሕግ ውጭ ነው:: ይህንን ተአምር የፈጸመው ሊቀ ነቢያት ሙሴ ቢሆንም ለሊቀ ነቢያት ሙሴ ይህንን ኃይልና ሥልጣን የሰጠው እግዚአብሔር ነው:: ዘጸ.14÷15፤21:: ይህ ተአምር የተፈጸመውም እሥራኤልን ከፈርዖን ግዞት፣ ከግብፅ ባርነት ለማዳን ነው::

ሌላ ምሳሌ እናክል:: በዮሐንስ ወንጌል 11÷1–44 አልዓዛር ከሞት መነሣቱ ተጽፏል:: የሰው ከሞተ ከአራተኛ ቀን በኋላ መነሣት ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ ነው:: የተለመደው የተፈጥሮ ሂደት ከሞት በኋላ የሥጋ መፍረስ መበስበስ ነው:: እኅቱ ማርታም:- «ጌታ ሆይ÷ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል፤» ዮሐ.11÷39 በማለት የተናገረችውም ለዚህ ነው:: አልዓዛርን ከሞት ያስነሣው ምድራዊ ጥበብና ኃይል ሳይሆን መለኮታዊ ኃይል ነው:: ይህም የተፈጸመው አይሁድ ይህን ተመልክተው እንዲድኑ ነው:: «ስለዚህ ወደ ማርታም ከመጡት አይሁድ ብዙዎቹ ኢየሱስም ያደረገውን ካዩት ከአይሁድ ብዙዎቹ በእርሱ አመኑ::» ዮሐ.11÷45::

### የተአምር መገለጫዎች

አንዳንድ ሊቃውንት «ተአምር» የሚለውን ቃል ከመተንተን ይልቅ መገለጫዎቹን መመልከቱ የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል ይላሉ:: ከዚህ በመቀጠል የተዘረዘሩት ነጥቦችም ይህን ይመለከታሉ::

ሀ. መደጋገም:- ይህ ሲባል «ተአምር» በተፈለገበት ጊዜና ቦታ ደግሞ ደጋግሞ መታየቱ በአጋጣሚ የተገኘ ያለመሆኑንና መለኮታዊ መንሥኤ እንዳለው ያመለክታል:: ለምሳሌ በዘኁ.21÷4–9 ላይ እንደ ተገለጠው እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ባጉረመረሙ ጊዜ እባቦች ነደፏቸው:: በኋላም በሙሴ አማላጅነት የሚፈወሱበት መንገድ ተነገራቸው:: ይኸውም ሙሴ የናስ እባብ በዓላማ ላይ እንዲሰቅል ተነገረው:: በዚያ ጊዜ ወደ ተሰቀለው የናስ እባብ የተመለከተው ሁሉ ዳነ:: ዘኁ.21÷9:: ይህ ተአምር በሁሉም እስራኤላዊ ላይ በየተራ መፈጸሙ የአጋጣሚ አለመሆኑን ያመለክታል:: ታቦተ ጽዮን በፍልስጤማውያን ተማርካ ወደ ጋዛ በወረደች ጊዜ ዳጎን ባለበት በቤተ ጣዖት አስቀመጧት:: በነጋው ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ወድቆ ተገኘ:: «ካህናተ ጣዖትም» ወደ ቦታው መለሱት:: በሁለተኛው ቀን ማለዳ ደግሞ ዳጎን በታቦቱ ፊት ወድቆ ተሰባብሮ ተገኘ:: /1ሳሙ. 5÷1–5/:: ይህ ሁኔታ በአጋጣሚ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቅጣት መሆኑን እንዲያውቁ አደረጋቸው::

ለ/ ወደ ጥንት ማንነቱ መመለስ:- ተአምሩ ከተፈጸመ በኋላ ሁኔታዎች እንደ ቀድሞው የሚሆኑበት ጊዜ አለ:: ይህም የዚያ ተአምር መፈጸም በሌላ ምክንያት ሳይሆን ልዑል እግዚአብሔር ለጥሪ፣ለምልክት፣ለቅጣት ያደረገው መሆኑን ለማመልከት ነው:: ለምሳሌ:- ንጉሥ ኢዮርብዓም የእግዚአብሔርን ሰው በተቃወመ ጊዜ እጁ ደረቀች:: በእግዚአብሔር ሰው ልመና ግን ወደ ጥንት ጤናይዋ ተመለሰች:: /1ነገሥት.13÷1–7/:: የሙሴ በትርም እባብ ከሆነች በኋላ ተመልሳ በትር ሆናለች:: /ዘጸ. 4÷2–4/::

ሐ/ ቀድሞ የሚሰጥ ትእዛዝ ወይም ቃል:- አንድ ተአምር ከመፈጸሙ በፊት ለሕዝቡ ቀድሞ የሚሰጠው ትምህርት፣ ትእዛዝ ወይም ቃል የሚፈጸመው ተአምር



www.eotcmk.org

ከእግዚአብሔር መሆኑን ይገልጣል:: «ኢያሱም ሕዝቡን:– ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ አለ::» ይህ የመስፍኑ እስራኤል ኢያሱ ቃል በኋላ የዮርዳኖስ ወንዝ ያለ ግድብ ሲቆም ተኣምሩን የሠራው እግዚአብሔር መሆኑን እንድናውቅ ነው::

መ/ **ጸሎት:–** ከጸሎት በኋላ የሚፈጸመው ተኣምር እግዚአብሔር ጸሎትን ሰምቶ ድንቅ ሥራውን መፈጸሙን ያመለክታል:: የማራ ውኃ ከመራራነት ወደ ጣፋጭነት የተለወጠው የሙሴን ጸሎት እግዚአብሔር ስለ ሰማው ነው:: /ዘጸ. 15÷22–26/:: መስፍኑ ሶምሶን በሌሒ እያለ በተጠማ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ:- «እግዚአብሔርንም በሌሒ ያለውን አዘቅት ሰነጠቀ፤ ከእርሱም ውኃ ወጣ፣ እርሱም ጠጣ::» /መሳ. 15÷18–19/::

ሠ/ **ተቃርኖ /ተጻሮ/** /Paradox/:- ጠርጡ ለስ የተባለው የሰሜን አፍሪካ ሊቅ:- «ወለፈንዲ በመሆኑ ፍጹም የሚታመን ነው:: ... የማይቻል በመሆኑ እውነት ነው::» [«It is to be believed absolutely because it is absurd... It is certain because it is impossible»] /On the Body of Christ, p.75 / በማለት እንደ ተናገረው ሁለት የሚቃረኑ /የሚጻረሩ/ ነገሮች መከናወናቸው ጉዳዩ በአጋጣሚ ወይም የተፈጥሮአዊ ሂደቶች ውጤት አለመሆኑን ያመለክታል:: ለምሳሌ:- እስራኤል የዮርዳኖስን ወንዝ ሲሻገር: - «እንደ መከር ወራት ሁሉ ዮርዳኖስ እጅግ ሞልቶ ነበር» /ኢያሱ. 3÷14/:: ይህም ማለት የዮርዳኖስ ቆሬ ሁሉ በውኃ ተሸፍኖ ነበር:: በዚያው ሰዓት «ታቦት ተሸካሚዎቹ ወደ ዮርዳኖስ ሲደርሱ፣ታቦቱንም የተሸከሙት የካህናቱ እግሮች በውኃው ዳር ሲጠልቁ ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመ::» /ኢያሱ. 3÷15/:: እነዚህ ሁለቱ ነገሮች የሚቃረኑ ነገሮች ናቸው:: ውኃው በጣም ሞልቷል፣ተትረፍርፏል - ውኃው ቆመ:: ነቢዩ ሳሙኤል ዝናም ከማውረዱ በፊት «የስንዴ መከር ዛሬ አይደለምን?» ብሎ ነበር:: ይህም ወቅቱ ደረቅ የበጋ ወቅት መሆኑን ያሳያል::: በኋላ ግን በነቢዩ ጸሎት «እግዚአብሔርም በዚያ ቀን ነጐድጓድና ዝናም ላከ::» /1ሳሙ. 12÷17–18/:: የበጋ ወቅትና የዝናም መምጣት የሚቃረኑ ነገሮች ናቸው:: አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ከእግዚአብሔር ሲያገኝም ይኼው ሁኔታ ተከስቷል:: «ልጅ ትወልዳለህ» ሲባል « የመቶ ዓመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሣራ ትወልዳለችን?» ብሎ ነበር:: ከዚህ ሁኔታ በኋላ ግን ይስሐቅ እንደ ሚወልድ በርግጥ ተነገረው:: /ዘፍ.17÷17–20/:: ለዚህ ነው አንድ ሊቅ እግዚአብሔርን «*የማይቻሉ ነገሮች አምላክ*» ብሎ የጠራው::

ረ/ሊሆን የማይችልበትን መንገድ ማለፍ:- አንዳንድ ጊዜ ነገሮች ሊሆኑ የማይችሉበት ሁኔታ ይበልጥ የተጠናከረና ተኣምሩን ላለማመን አንዳችም ዕድል ወይም ምክንያት በማይሰጥ ሁኔታ ይፈጸማሉ:: ለምሳሌ ኤልያስ የበኣልን ነቢያት ሲያሳፍር በሚቃጠለው እንጨት ላይ አራት ጋን ውኃ አስጨምሯል:: ይህ ደግሞ በሰውሰውኛው አስተሳሰብ ያለመሆንን ዕድል ያሰፋዋል:: በኋላም:- «የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፤ የሚቃጠለውን መሥዋዕቱንም፣ እንጨቱንም፣ ድንጋዩንም አፈሩንም በላች::» /1ነገሥ.18÷36–38/::

ሰ/ **በተፈቀደበት ቦታ ብቻ ተፈጻሚ መሆኑ:–** በሙሴ እጅ በግብፃውያን ላይ ይፈጸሙ የነበሩ ተኣምራት እስራኤልን ከግብፃውያን የለዩ ነበሩ:: «በዚያ የገዛንብ መንጋ እንዳይሆን ሕዝቤ የሚቀመጥበትን የጌሤምን ምድር እለያለሁ::» /ዘጸ.8÷22/ እንዳለ ይህም ተፈጥሯዊ ክስተት ሳይሆን ለትምህርት ወይም ለቅጣት የመጣ መሆኑ ይታወቅ ዘንድ ነው::

ሸ/ **የአረማውያን ምስክርነት:–** ተኣምራት ከሚገለጡባቸው መንገዶች አንዱ አረማውያን የሚሰጡት ምስክርነት ነው:: ይኼም የዚያ ተኣምር መገለጥ ዓላማ የሁሉ ጌታ፣የሁሉ ንጉሥ፣ የሁሉ ፈጣሪ የሆነ የልዑል እግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ መግለጥና ማሳመን በመሆኑ ነው:: ለምሳሌ የፈርዖን ጠንቋዮች ሙሴ የሚያደርገውን ተኣምር ማድረግ ባልቻሉ ጊዜ የሙሴን ተኣምር «ይኼስ የእግዚአብሔር ጣት ነው» በማለት ምስክርነት ሰጥተዋል:: /ዘጸ.8÷12/:: ሠለስቱ ደቂቅ ወደ ዕቶኑ እሳት በተጣሉ ጊዜ:- «እነሆ እኔ የተፈቱ በእሳትም መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለሁ:: ምንም አላቆሰላቸውም፤ የአራተኛውም መልክ የአማልክትን ልጅ ይመስላል» በማለት የመሰከረው ንጉሡ ናቡከደነፆር ነበር:: /ዳን.3÷25/:: ነቢዩ ዳንኤል ከአፈ አናብስት በዳነ ጊዜ ንጉሡ ዳርዮስ: - «በመንግሥቴ ሁሉ ያሉ ሰዎች በዳንኤል አምላክ ፊት እንዲፈሩና እንዲንቀጠቀጡ አዝዣለሁ:: እርሱ ሕያው አምላክ ለዘላለም የሚኖር ነውና::» ብሎ መስክሯል:: /ዳን. 6÷26–27::

ቀ/ ከላይ የዘረዘርናቸው በየራሳቸው እንደ ሚገኙት ሁሉ በቅንጅት ወይም ሁሉም በአንድ ላይ ሊገኙም ይችላሉ:: ለምሳሌ በዐሥራ አንዱ በግብፅ በተፈጸሙት ተኣምራት ተከታታይነት /መደጋገም/÷ ጸሎት፣ ቀድሞ መንገር በአንድነት ይገኛሉ::

በሐዲስ ኪዳን ተኣምር የሚለው ቃል /በግሪኩ ዳይናሚስ - ኃይል፣ ሥልጣን፣ ወይም ኤርጉን ሥራ/ ለጌታችንም ለቅዱሳን ሐዋርያትም ተሰጥቷል:: በሐዲስ ኪዳን የተፈጸሙ ተአምራትን መተርጉማን በሦስት ከፍለዋቸዋል:: ፈውስ፣አጋንንትን ማውጣት እና ተፈጥሮን መለወጥ ወይም በተፈጥሮ ላይ ሥልጣን ማሳየት ናቸው::

ፈውስ:- ፈውስ የሚባለው የጴጥሮስ አማት መፈወስ (ማቴ.8÷14)፣ 12 ዓመት ደም የፈሰሳት ሴት መፈወስ፣ (ማቴ.9÷20)፣ የሹሙን ልጅ ከሞት ማንሣት፤ /ዮሐ.4÷46/፤ የጴጥሮስና የዮሐንስ ሽባውን ማርታት (የሐዋ. 3÷1–10) የመሳሰሉት ናቸው::

አጋንንትን ማውጣት:- በጌርጌሴኖም ከሰው ወጥተው ወደ እሪያዎች እንደ ገቡት አጋንንት፣ (በማቴ.8÷28)፤ ዕውርና ዲዳ ከነበረው ሰው እንደ ወጣው ጋኔን፤ (በማቴ.12÷22) በምኩራብ ይኖር ከነበረው ሕሙም እንደ ወጣው ጋኔን፤ (በማር.1÷23) በፊልጵስዮስ ከተማ ከአንዲት አገልጋይ እንደ ወጣው ጋኔን (በሐዋ.16÷16) ያለው ነው::

ተፈጥሮን መለወጥ ወይም በተፈጥሮ ላይ ሥልጣን የሚባለው ደግሞ የውኃው ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ በዮሐ.2÷1–11፣ የጌታችን በባሕር ላይ መራመድ፣ የጌታችን ባሕሩን ጸጥ ማሰኘት በማቴ.14÷25፣ በማቴ. 14÷13–21፤ ሁለቱን ዓሣና አምስቱን እንጀራ ማበርከት (ማቴ.17÷24)፣ ለግብር የሚከፈለውን ገንዘብ ከዓሣ ሆድ ማስገበር በማቴ.17÷24፣ ጌታችን በለሷን በረገማት ጊዜ ወዲያው መድረቅ በዮሐ.21÷5–8፣ ያ የሐዋርያት አስደናቂ ሁኔታ- ሌሊቱን ሙሉ ደክመው ዓሣ ካጡበት የጥብርያዶስ ባሕር 153 ዓሣ ማግኘት:: በማቴ.21÷18 /Eerdmans: 722/

## ተኣምራት በምን በምን ይፈጸማሉ ?

እግዚአብሔር ተኣምራትን በልዩ ልዩ ነገሮች ይፈጽማል:: ብዙ ጊዜም «ለኀሊና ቀላል፣ተራና ከሚፈጸመው ተኣምር ጋር ባሕርያዊ ግንኙት· በሌላቸው ነገሮች ነው:: ባሕርያዊ ግንኙነት ማለት ለምሳሌ መድኃኒት ሲዋጥ የመድኃኒቱ ቅመማ የበሽታውን አምጪ ተሐዋስያን እንዲገድል ተደርጐ እንደ ሚሠራው ተኣምራቱ የሚፈጸምበት ነገር በዚህ መልክ የተዘጋጀ አይደለም ማለት ነው:: በተኣምራቱና በመፈጸሚያው ነገር መካከል ያለው ግንኙነት በመፈጸሚያው ነገር ላይ የእግዚአብሔር ኃይል፣ጸጋና ፈቃድ መኖሩ ነው::

ሀ/ በቃል:– ተኣምራት በቃል ይፈጸማሉ፤ ለምሳሌ ወደ ቤቴል የተላከው ነቢይ:- «እነሆ እግዚአብሔር የተናገረው ምልክት ይህ ነው:: መሠዊያው ይሰነጠቃል፤ በላዩም ያለው አመድ ይፈሳል» ብሎ በተናገረው



www.eotcmk.org

ቃል መሠዊያው ተሰንጥቋል፥ አመዱም ፈስሷል:: 1ነገሥት 13÷1–6:: ነቢዩ ኤልያስም ለሰራፕታዋ መበለት:- «በምድር ላይ እግዚአብሔር ዝናም እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ ዱቄቱ ከማድጋ አይጨረስም፥ ዘይቱም ከማሰሮው አይጐድልም» በማለት በተናገረው መሠረት:- «በኤልያስ እጅ እንደ ተናገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል ዱቄት ከማድጋው አልተጨረሰም፤ ዘይቱም ከማሰሮው አልጐደለም::» 1ነገሥት 17÷14–16:: በሐዋርያት ሥራም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቃሉ ትእዛዝ አጋንንትን አውጥቷል:: /የሐዋ.16÷18/:: ስልማና በተባለው ከተማ ጠንቋዩን ኤልማስን:- «የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት፥ ዕውርም ትሆናለህ ፥ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም» ባለው ቃል «ያን ጊዜ ጭጋግና ጨለማ ወደቀበት ፥ በእጁም የሚመራውን እየዞረ ፈለገ::» የሐዋ.13÷5–12::

ለ/ በልዩ ልዩ መሣሪያዎች: - «እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ» በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረ /1ቆሮ.1÷27/ የተኣምራት መገለጫ መሣሪያዎች ምድራዊ ኃይል የሌላቸው ናቸው:: በትረ ሙሴ /ዘጸ. 4÷20/፣ የዮርዳኖስ ውኃ ለምጻሙ ንዕማንን መፈወሱ 2ነገ.5፣የኢያሪኮ ውኃ በማሰሮ ጨው መጣፈጡ 1ነገ. 3፣ የመጻጉዕ በቤተ ሳይዳ ጠበል መዳን ዮሐ5÷1–17፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ጥላ ድውያንን መፈወስ የሐዋ.5÷15፣የቅዱስ ጳውሎስ ልብስ አጋንንትን ማስለቀቅ የሐዋ.19÷11 የሚጠቀሱ ናቸው::

ሐ/ የቅዱሳን ሰውነት:– «የሱነማዊቷ ልጅ በሞተ ጊዜ ኤልሳዕ ወደ ሠገነቱ ወጥቶ ገብቶ በሩን ከሁለቱ በኋላ ዘጋ:: ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ:: መጥቶም በሕፃኑ ላይ ተኛ:: አፉንም በአፉ፣ዐይኑንም በዐይኑ፣ እጁንም በእጁ አድርጐ ተጋደመበት:: የሕፃኑም ገላ ሞቀ::» በዚህ መልኩ ሰባት ጊዜ አድርጐ ሕፃኑን ከሞት አስነሥቶታል:: 2ነገሥት 4÷32–37:: ኤልሳዕ ከሞተ በኋላ ዐፅሙ ሙት አስነሥቷል:: 2ነገሥት 13÷20::

መ/ ያለ ምክንያት:– እግዚአብሔር ለሕዝቡ መግለጥ የሚፈልገውን ድንቅ ሥራ ያለ ምንም መሣሪያ የሚገልጥበት ጊዜም አለ:: ለምሳሌ:- የጥፋት ውኃ፣ የሰዶምና ገሞራ መቃጠል፣ በዮርዳኖስ የቅድስት ሥላሴ መገለጥ ማቴ.3÷1-17፣ በደብረ ታቦር የብርሃን መለኮቱ ለሐዋርያት መገለጥ / ማቴ.17÷1-5 / ወዘተ ይጠቀሳሉ::

## ተኣምራት ለምን ይፈጸማሉ?

ሀ/ ለፈተና:– እግዚአብሔር ለእርሱ ያለንን ፍቅርና በእርሱ ያለንን የሃይማኖት ጽናት ለማወቅ ተኣምራትን ያደርጋል:: የማራ ውኃ በተኣምራት በጣፈጠ ጊዜ:- «በዚያም ሥርዓትንና ፍርድን አደረገላቸው፤ በዚያም ፈተናቸው::» ይላል:: ዘጸ.15÷25:: መና ከሰማይ ከመውረዱ በፊትም «በሕጌ ይሄዱ ወይም አይሄዱ እንደ ሆነ እኔ እንድፈትናቸው እነሆ ከሰማይ እንጀራን አዘንብላችኋለሁ::» ተብሏል:: ዘጸ.16÷4::

ለ/እምነትን ለማጽናት:- መስፍኑ ጌዴዎን ሕዝቡን ነጻ ለማውጣት ሲጠራ እግዚአብሔር ጥሪውንና ተልእኮውን በተኣምራት እንዲያጸናለት ጠይቋል:: የጠሉና የጸምሩ ታሪክ የተፈጸመው በዚያ ምክንያት ነው:: /1ሳሙ.6÷36 –40/:: ንጉሥ ሕዝቅያስ እግዚአብሔር እንደሚፈውሰው ነቢዩ ኢሳይያስ ሲነግረው ምልክት ጠይቆ ነበር:: በዚህም መሠረት ጥላውን በአካዝ የጥላ ስፍረ ሰዓት ላይ በወረደበት መንገድ ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ መለሰው:: 2ነገ. 20÷8–11::

ሐ/ ለሽልማት/ለቅጣት :– የጻድቁ ሰው የሔኖክ ከነሕይወቱ መሰወር ተኣምር ነው:: ይህም ለመልካም ሕይወቱ ዋጋ የተሰጠው ነው:: ዘፍ. 5÷23–24:: ባልዋ የሞተባት ሴት ኤልሳዕን በተማፀነችው ጊዜ ቤትዋን በዘይት የሞላበትን ተኣምር የፈጸመው እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት በመሆ ንዋ የተደረገላት ቸርነት ነው:: 2ነገ. 4÷4:: የንጉሡ ሕዝቅያስ መፈወስ የጸሎቱ ምላሽ ነው 2ነገ. 20÷3፤ የሠለስቱ ደቂቅ ከዕቶነ እሳት መዳን የእምነታቸው ውጤት ነው:: ዳን.3::

በሌላ በኩል ደግሞ አብዮድና ናዳብ ያልተገባቸውን የክህነት ሥራ በመሥራታቸው ከእግዚአብሔር ፊት እሳት ወጥቶ በላቸው:: ዘሌ.10÷1–2፤ የዳታንና አቤሮን ከነሕይወታቸው አፏን በከፈተች ምድር መዋጥ ያልተገባቸውን በማድረጋቸው ቅጣት ነው:: ዘኁ. 16÷31–34:: ንጉሡ ያዝያን ያልተገባውን ዕጣን በማጠኑ በለምጽ ተመታ:: 2ዜና.26÷16–23:: የአሦር ንጉሥ በሰማርያ ያኖራቸው አሕዛብ እግዚአብሐርን አይፈሩትም ነበር::» ስለዚህም «አንበሶችን ሰደደባቸው፥ ይገድሏቸውም ነበር::» 2ነገ. 17÷25::

መ/ የእግዚአብሔር ቸርነት መገለጫ:– እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ፍቅር፣ ቸርነትና መግቦት ልዩ ልዩ ተኣምራትን በመሥራት ይገልጣል:: ለዚህም የሣራ መውለድ /ዘፍ.17/፣የሐና መውለድ /1ሳሙ.1/፣ የኢያሪኮ መራራ ውኃ መጣፈጥ /2ነገሥት. 2÷19/፣ የማኑሔና ሚስቱ ልጅ ማግኘት /መሳ.13÷5/፣ የኤልሳቤጥ መውለድ /ሉቃ.1/ እንደ አስረጅ ሊጠቀሱ ይችላሉ::

ሠ/ ለምስክርነት:– በማያምኑ ዘንድ የእግዚአብሔር ክብር እንዲታወቅ ተኣምራት ይደረጋል:: ነቢዩ ኤልያስ ከበኣል ነቢያት ጋር በተከራከረ ጊዜ:- « አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደ ሆንክ፣ እኔም ባሪያህ እንደ ሆንኩ ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግኹ ዛሬ ይገለጥ» በማለት እንደ ተናገረው እግዚአብሔር ከሃሊነቱ /ሁሉን ቻይነቱ/ የቅዱሳኑም ክብር እንዲገለጥ ተኣምራትን ያደርጋል:: 1ነገሥት 18÷37:: አሕዛብ እግዚአብሔርን እንዲፈሩ /ዘጸ.15÷14/፣ መስፍኑ እስራኤል ኢያሱ የዮርዳኖስን ወንዝ የመከፈሉን ምክንያት ሲገልጥ:- «የእግዚአብሔር እጅ ጠንካራ እንደ ሆነች የምድር አሕዛብ ሁሉ እንዲያውቁ አምላካችሁንም እግዚአብሔርን ለዘላለሙ እንድትፈሩ ነው» ብሏል:: /ኢያ.4÷24/:: የሙሴ አማት ዮቶር እግዚአብሔር በግብፅ ያደረገውን ተኣምር በሰማ ጊዜ:- «እግዚአብሔር ከአማልክት ሁሉ እንዲበልጥ አሁን ዐወቅሁ::» ብሏል /ዘጸ.18÷1/:: ሶርያዊው ንዕማንም ከለምጹ በተፈወሰ ጊዜ:- «እነሆ ከእስራኤል ዘንድ በቀር በምድር ሁሉ አምላክ እንደሌለ ዐወቅሁ::» ብሏል:: 2ነገሥት. 5÷15::

ረ/ የእግዚአብሔር ሰዎች ክብር እንዲገለጥ:– እግዚአብሔር የልጆቹን ክብር በተኣምራት ይገልጣል:: አሮንና ማርያም ሙሴን በተቃወሙት ጊዜ ማርያም በለምጽ ተመታች:: ዘኁ.12÷10:: ይህም የሙሴ ክብር እንዲገለጥ ነው:: የኤልያስ መንፈስ በኤልሳዕ ላይ ማረፉ ይታወቅ ዘንድ የዮርዳኖስ ወንዝ በነቢዩ ኤልያስ መጐናጸፊያ ለነቢዩ ኤልሳዕ ተከፈለለት:: 2ነገ. 4:: እግዚአብሔር አሮንን በክህነት መምረጡን ይበልጥ የገለጠው ያለ አፈርና ያለ ውኃ የአሮንን በትር በማለምለምና በማፍራት ነው:: ዘኁ. 17÷16 – 20:: በቅዱሳን ሐዋርያት እጅ ተኣምራት በመደረጋቸው ሕዝቡ እነርሱን ያከብሯቸው ነበር:: የሐዋ.5÷12–13::

ተኣምራትና ቅዱሳን እንዲሁም በተኣምረ ማርያም መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ታሪኮችንና ምንጮችን በተመለከተ በቀጣዩ እትም ላይ እንመለስበታለን::

ይቆየን

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

# አስቂኝ ማርያም

*ዘሪሁን ሲሳይ ጌታሁን*
*/ደብረ ብርሃን/*

የሰሞኑ ሙሉ ክብ ጨረቃ ዛሬ ማምሻዋን አልወጣችም:: ከዋክብት ዐይን ቢወጉ በማይታየው ድቅድቅ ጨለማ አሻግረው የውብ ዐይናማ ዓይነት ጥቅሻ ይጠቅሱኛል::

ንፋሱም የዛፎችን ቅጠል እያንቻቻ ሲያረግፋቸው "ምን መጣ?" ብዬ ልቤ እንደ ከበሮ ይደልቃል፤ የምረግጠውን በባትሪዬ ብርሃን እያየሁ፤ ከ<አስቂኝ ማርያም> ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ዙሪያ ከሚገኝ ካል ተዘጋው መቃብር ቤት ውስጥ ገባሁ:: ግድግዳውን ተደግፌ ዐረፍ አልኩ:: በባትሪው ብርሃን የግድግዳውን ዙሪያ ዐየሁ:: ሸረሪቶች በድራቸው ላይ ሲወጡና ሲወርዱ፤ ነፍሳት በግድግዳው ላይ በማን አለብኝነት ይንሸራሸራሉ:: ከተደረመሰው ግድግዳ ወዲያ ሌላ ክፍል አለ:: የባትሪዬን ብርሃን አጠፋሁ:: ክፍሉ በድቅድቅ ጨለማ ተዋጠ::

ኀሊናዬ ዕረፍት አግኝቶ ጐኔ አልተመቻቸም:: ብርሃን አልባው ጨለማ ውስጥ ለመግለጽ የሚያስቸግሩ፥ የተለያየ ቅርፅና መልክ ያላቸው ፍጥረቶች ወደ እኔ በአስደንጋጭ መልኩ ሲመጡ፤ የልቤ ትርታ ሲጨምር፣ ባትሪዬን ሳበራ፥ ያገጠጡ ድንጊያዎች ሆነው ሳያቸው "ተመስገን አምላኬ" በማለት በራሴ እስቃለሁ:: "እውነትም አስቂኝ፥ እመቤቴ ሆይ፥ ከክፉ ነገር ሁሉ ሰውረሽ ደስ አሰኚኝ" እላለሁ:: ምናልባት ለሚያየኝ አእምሮዬን ያጣሁ ሳልመስል አልቀርም::

ይህ የገና ጀንበር "ቀኑ አጭር፥ ሌቱ ረጅም" የሚባለው እውነትነት አለው:: የሚያልፈው ሌሊት አለቅጥ ረዝሞም እንደሁ እንጃ:: አልነጋ አለኝ::

የ <አስቂኝ ማርያም> ቤተ ክርስቲያን ጉልላት መርገፎች ሲንቻቹ የሚፈጠረውን የሚመስጥ ድምፅ እያደመጥኩ ትዝታ እንደ ደራሽ ውኃ ይዞኝ እልም ሲል፤ የፉጨት ዓይነት ቃና ያለው ቀጭን የሳል ድምፅ በጆሮዬ መሰስ ብሎ ገባ::

ደጋግሞ አሳሳት፤ ማንነቷን ለማወቅ ጓጓሁ::

"ማን ዐውቄስ?" ለራሴ ጥያቄ አቀረብኩ:: መላልሶ ሲያዛጋኝ በአወጣሁት ድምፅ ሳትሰማኝ አትቀርም:: መቼም ለራሴ እንድፈልጋት የሚያነሣሣኝ አንዳች ነገር በውስጤ ሆኖአል::

ረኀብ በሻከረ ምላሱ ይልሰኛል:: ድካምም ተጫጭኖኛል:: ግን የሚያስረሳኝ የው ይዞኝ ጥርግ የሚል ሐሳቤ ነበር:: አሁን ግን ሙሉ መንፈሴ የፉጨት ዓይነቱን የሳል ድምፅ ለማወቅ ባደረብኝ ጉጉት ምክንያት ድካሜ ሁሉ ጥሎኝ ጠፋ::

ባትሪዬን መኾረጥ አድርጌ በባትሪው ብርሃን እየተመራሁ ድምፅ ወደ ሰማሁበት አቅጣጫ አመራሁ:: በተደረመሰው ግድግዳ ላይ አልፌ ሌላ ክፍል ገባሁ፤ በክፍሉ ውስጥ በተዘጋው ሌላ ክፍል ሳትሆን እንደማትቀር ገመትኩ:: በባትሪዬ ብርሃን ጭላንጭል ፈልጌ በማብራት ወደ ውስጥ መመልከት ጀመርኩ:: ግድግዳውን ደገፍ ብላ ቁጭ ብላለች:: ፊት ለፊት ገጽዋ ላይ አበራሁት:: እንዳትደነግጥ እየሰጋሁ::

የቀይ ዳማ ነች፤ የደስ ደስ ከፊቷ ላይ ይነበባል፤ ልዩ ፈገግታዋ ልቤን ሰንጥቆ ገብቶ እኔንም ፈገግ አሰኘችኝ:: ሆኖም ግን ዐይናማ የኾነች ይመስል ዐይኖቿን የጨፈነች መሰለኝ::

"ከሚያስፈራት ነገር ለመሸሽ ይሆን?" አልኩ:: እውነትም <አስቂኝ ማርያም> አልኩ ለራሴ:: በሁኔታው ሁሉ ልገልጸው የማልችለው ደስታ በልቤ ውስጥ ይናኛል::

ይህን ሁሉ በሐሳቤ ካወጣሁና ካወረድሁ በኋላ ዐይኖቼ ባቶቿ ላይ ተወረወሩ፤ ጡቶቿ በደረቷ ላይ ወድቀዋል::

በሩን ገፋሁት:: በውብ ፊቷ ላይ የሚታየው ብሩህ ፈገግታ ደበዘዘና ግንባሯ ተቋጠረ:: የሰማችው የበር መከፈት ድምፅ ርግጥ መሆኑን በማንኳኳት ገለጽኩላት::

"ማነው?" አለች:: የፉጨት ዓይነት ቃና ያለው ድምፅዋ ልብ ይሰርቃል::

*«እኔ ነኝ »*

*«እኔ ማን? »*

*«ከከተማ ነው የመጣሁት...»*

*«ከየት ከተማ?»*

*"ግሼ ራቤል ከሚባል፥ ወደ ሀገረ ማርያም ከሰም ወረዳ በገጠር መምህርነት እንድሠራ ተዛውሬ ነው የመጣሁት:: ለሀገሩ እንግዳ ስለሆንኩ በመንገድ ላይም ስለ መሸብኝ እባክዎ ዛሬን እንዲያሳድሩኝ ነው እማማ::"*

ነገሬን በጥሞና ሰምታ ከጨረሰች በኋላ በስተ መጨረሻ "እማማ" ማለቴ ፈገግ አሰኛት:: ከቅምባ ተነሥታ እስከ በሩ ድረስ አወጣጡዋ ከታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ ያነበብኩትን "ዐይነ ስውሮችም ያያሉ" የሚለውን ጥቅስ አስታወሰኝ::

ንግግሬን በአንቲታ በመቀጠል ምሽቱን እንዴት እንዳሳለፉ ጠየኳት:: አምላካቸውን አመስግነው ወደ ውስጥ እንድዘልቅ ሲጋብዙኝ ሳልግደረደር ገባሁ::

ክፍሉ ነጭ ሣር ተጐዝጕዞበታል፤ በጭድ ተደልድሎ ስሌን ከተነጠፈችው አልጋ ብጤ ላይ ዐረፍ እንድል ነገሩኝ፤ ሆኖም ተስፈንጥሬ መደብ ላይ ተቀመጥኩ:: አጥብቀው እንድቀመጥ ጋበዙኝ፤ ግብዣቸውን ተቀበልኩ፤ ክብሪቱን በዳሰሳ ፈልገው ቁራጭ ሻማ ፈልገው ለኰሱ፤ ለጥቂት ጊዜ በመካከላችን ዝምታ ነገሠ::

"ደብሩ <አስቂኝ ማርያም> ነው፤ የሚባለው?"

"አዎ"

"አካባቢው እንዴት <አስቂኝ> ሊባል ቻለ?" የምበላውን ዳቦ እያቀረቡልኝ ሳለ ጠየቅኋቸው:: የደብሩ ዐቃቢት ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ገመትኩ::

"በቆዳ የተለጐሙ አገልግሎች በትከሻቸው ያነገቱ ዘጠኝ መንገደኞች ከሩቅ ሀገር መንገድ ተጉዘው፤ ለምሳ በተለምዶ <አስቂኝ> ከተባለው ቦታ ዐረፍ ይላሉ::..."

ነገራቸውን በማቋረጥ "ለመሆኑ አስቂኝ የሚባለው ስፍራ በትክክል የቱ ጋር ነው?" አልኳቸው::

*"... ስትመጣ በሁለት ተረተራማ ሸንተረሮች ደብድቤ ላይም አይደል፤ የመጣኸው?..."*

"ተረተር ማለት የቱ ጋር ነው?" አልኳቸው::

"... በሸንተረሮቹ ላይና ጥግ የኮሶ የዋንዛና ብሳና ወፍ ዘራሽ ቁጥቋጦዎች በጹር ጥድ መካከል ከበስተ ምሥራቅ አንድ ቀጭን መንገድ አልፈኸ የለም? ያ ነው" አሉ፤ በማስከተልም "ቆይ ይሄን ነገር ያነሣኸው ለምን ነበር?» ሲሉ ጠየቁኝ::

"አካባቢው ለምን <አስቂኝ> እንደ ተባለ ለማወቅ የጠየኩዎትን መነሻ በማድረግ ነው::"

"አዎ" አሉና ነገራቸውን ከአቆሙበት ይተርኩልኝ ገቡ::

"...ከስንቃቸው ለመመገብ አገልግሎቻቸውን እየፈቱ እያለ ከመካከላቸው አንዱ ከሚሄድበት መንገድ ርቀት አንጻር ከእያንዳንዳቸው አንዳንድ ጭብጦ አሰባስቦ የተሰበሰበውን የጭብጦ ብዛትና የመንገደኞቹን ቁጥር ሲያነጻጽር አንድ ጭብጦ ጐደለበት:: ግራ የመጋባት ስሜት ከዐይኑ ውኃው ላይ እየተነበበ አንዴ ጭብጠውን ደግሞ መንገደኞቹን ቆጥሮ መላ ስላጣ ለመንገደኞቹ ከማቅረቡ በፊት ግራ ያጋባውን ገለጸላቸው፤ በተመሳሳይ መልኩ ስምንቱ መንገደኞችም እንደ ጭብጦ ሰብሳቢው ግራ ገባቸውና መላ አጡ:: በሁኔታው እየተገረሙ እያለ ከርቀት ተጉዘው በዐረፉበት <አስቂኝ> ስፍራ የሚያልፈውን መንገደኛ ግራ ስለ ተጋቡበት




www.eotcmk.org

ሁኔታ ይነግሩታል::
"እርሱም፥ እናንተስ አስቂኞች ናችሁ፤ ጭብጦ ሰብሳቢው እኮ የራሱን ባለ ማዋጣቱ ነው» አላቸው:: በማስከተልም ስለ ፈጣን አእምሮው ለአስቸጋሪ ጉዳ ያቸው መላ ስለ መታ አንድ ጭብጥ

ተመርቄ በተለያየ አካባቢ እንዳንተ አስተምሬአለሁ:: ...
"... ይሁን እንጂ በልጅነቴ አመዛኙን ጊዜዬን በእግዚአብሔር ቤት ነው ያሳለፍሁት:: ስለዚህ የደብሩ ን ዕቃ ቤት በማጠናከር የቤተ ክር

ያልቻለው ወላጆቼ ፍጹም ጤነኛ እንድሆን ያላደረጉልኝ ክብካቤ፣ ያልደረ ስኩበት ጠበል፣ ዐማኑኤል ሆስፒታል አልቀረም ወስደውኛል::
ይሁን እንጂ በዚህ መሐል ዐይኔን አጣሁ::

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የተጠኑ ÷ የተተገበሩና በመተግበር ላይ የሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶች አጭር ዳሰሳ /ካለፈው የቀጠለ/

**ባለፈው እትማችን በከፋ ችግር ውስጥ የሚገኙ ገዳማት፣አድባራትና አብነት ት/ቤቶች ይረዱ ዘንድ ማኅበረ ቅዱሳን ያጠናቸውን 24 የልማት ፕሮጀክቶች ከሚገኙበት ሁኔታ ጋር ማስተዋወቅ ጀምረናል:: በዚህኛው እትም ደግሞ የቀሩትን እናቀርባለን:: የዚህ ዝግጅታችን ዓላማ ምእመናን ቅዱሳት መካናቱ የደረሰባቸውን ችግር ተገንዝበው ቤተ ክርስቲያን የጣለችባቸውን አደራ እንዲወጡ መሆኑን በድጋሚ እናስገነዝባለን:: መልካም ንባብ!**

በምዕራፈ ቅዱሳን በልበሊት ኢየሱስ ገዳም ያደረግነውን ቆይታ አጠናቀን ጉዞአችንን በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ስናደርግ በጎንደር ሀ/ስብከት በደባርቅ ወረዳ በአዳጋት ቀበሌ ገበሬ ማኀበር ከአራት ሰዓት የእግር መንገድ ጉዞ በኋላ በፕሮጀክቱ ጥናት ውስጥ የተካተተውን የዱር አንበሳ ኪዳነ ምሕረት ገዳም እናገኛለን :: ገዳሙ ከተመሠረተ ጥቂት ዓመታት ቢሆነውም ገደላማ በሆነ የመሬት አቀማመጥ ውስጥ ጥቅጥቅ ያለው የተፈጥሮ ደን፣ የገዳሙ መነኮሳት አኗኗር እና ሥርዓት ጥንታውያት ገዳማት ያላቸውን ገጽታ እንዲይዝ አድርጎታል::

ገዳሙ ካለው መሬት ውስጥ ለእርሻ የሚውለው አነስተኛ መጠን ያለው መሬት ብቻ ነው:: በየዓመቱም ያለማቋረጥ ስለሚታረስ የሚገኘው ምርት አጥጋቢ አይደለም:: ከዚህ የተነሣ መነኮሳቱ ከሰኔ ወር በኋላ ምርት እስከሚያገኙ ድረስ በየአርሶ አደሩ ቤት በመዘዋወር ይለምናሉ:: የገዳሙ አካባቢ ዙሪያውን በረጃጅም ተራራዎች የተከበበ ሆኖ ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ የተዋጠ በመሆኑ የፀሐይ ሙቀት ፈጽሞ አያገኘውም:: በዚህ የተነሣም ገዳሙ ከባድ ቅዝቃዜ አለው:: ገዳማውያኑ ይህንን ጠንካራ ብርድ ለመቋቋም የሚያስችሏቸው መኖሪያ ቤቶችና በቂ የቀንም ሆነ የሌሊት ልብሶች ስለሌሏቸው ዘወትር እንደ ተቸገሩ ይኖራሉ::

ይህንን መሠረታዊ የሆነ ችግር በዘላቂነት በማስወገድ ገዳሙ ራሱን እንዲችል ለማድረግ ግምቱ 25,000 ብር የሆነ የአነስተኛ መስኖ እና የአትክልት ልማት ፕሮጀክት፤ እንዲሁም ግምቱ 20,850 ብር የሆነ ዘመናዊ የንብ ርባታና የመስኖ ፕሮጀክት ተቀርጾለታል:: ከአዲስ አበባ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት የጎልማሶች ክፍል በተገኘ የ20 ሺ. ብር ድጋፍ ሥራውን ለመጀመር በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ ሲሆን የንብ ርባታው ፕሮጀክት የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠበቅ ላይ ይገኛል::

በዚሁ በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ እንዳለን ወደ አዊ ሀ/ስብከት ስናመራ የቅድስት ወለተ ጴጥሮስ አንድነት ገዳምን እናገኛለን:: የቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ገዳም በአዊ ዞን ሀ/ስብከት ከዳንግላ ወረዳ ከአራት ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ልዩ ስሙ ቱምሃ በተባላ ሥፍራ ይገኛል:: 400 ዓመት ገደማ እንደ ሆነው የሚነገርለት ይህ ገዳም እጅግ ማራኪና ውብ በሆኑ ተራራዎችና ሸንተረሮች በተከበበ ቦታ ላይ ይገኛል::

የቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ገዳም ቤተ ክርስቲያን በ1996 ዓ.ም በአካባቢው በተነሣ ሰደድ እሳት ሙሉ ለሙሉ ሲቃጠል፤ በውስጡ የነበሩና ሊተኩ የማይችሉ ቅርሶች አብረው ወድመዋል:: በአሁኑ ሰዓት ከበጎ አድራጊዎች በተገኘው ድጋፍ ግንባታው እንደ ገና እየተካሄደ ይገኛል:: በአሁኑ ወቅት በገዳሙ ውስጥ ወደ 70 የሚጠጉ መነኮሳትና መነኮሳዪያት ይኖራሉ:: በገዳሙ እስከ 1988 ዓ.ም ድረስ በሁለት የአብነት መምህራን አማካይነት ለሁለት መቶ ተማሪዎች የአብነት ትምህርት ይሰጥ የነበረ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ግን ለመምህራን የሚደረግ ድጋፍ ባለመኖሩ ትምህርቱ ሙሉ በሙሉ ተቋርጧል:: ተማሪዎቹም ወደ ሌሎች አጎራባች ገዳማት መምህራን ተበትነዋል:: ገዳሙ ያሉበትን ችግሮች ለማቃለል እና ራሱን በልማት እንዲችል ለማድረግ ግምቱ 17,105 ብር የሆነ የንብ ርባታና ግምቱ 34,623 ብር የሆነ የሽመናና የልብስ ስፌት ፕሮጀክቶች ተጠንተው የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል::

ወደ ምዕራብ ጐጃም ሀ/ስብከት ስናመራ የምናገኘው የማየ ሐጹራ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አንድነት ገዳምን ነው:: ገዳሙ በምዕራብ ጎጃም ሀ/ስብከት ከባህር ዳር በስተ ምሥራቅ ከ 30 ኪ.ሜ ርቀት በኋላ በቱሪዝም መስህብነቱ በሚታወቀው በጢስ ዓባይ መግቢያ ላይ ይገኛል::

በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በሀገራችን ተከስቶ በነበረው «የኅዳር በሽታ» በገዳሙ የነበሩ ወደ 30 የሚጠጉ መነኮሳት በሙሉ በማረፋቸውና ከገዳሙ 30 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው ይባብ ከሚባለው ሥፍራ በተነሣው ሰደድ እሳት ቤተ ክርስቲያኑ ሙሉ ለሙሉ በመቃጠሉ ለብዙ ጊዜ ጠፍ ሆኖ ቆይቷል::

በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ በርናባስ እና በሌሎች በጎ አድራጊ ምእመናን ጥረት ቅዳሴ ቤቱ ሰኔ 16 ቀን 1990 ዓ.ም ተከብሯል:: ገዳሙ ዙሪያውን በዓባይ ወንዝ የተከበበ በመሆኑም «ማየ ሐጹራ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የአንድነት ገዳም» የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል:: በአሁኑ ሰዓት በገዳሙ 14 መነኮሳት የሚገኙ ሲሆን እነዚህ መነኮሳት ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ተጠቅመው በኑሮ ራሳቸውን እንዲችሉና ገዳሙንም ወደ ፊት የብዙ መነኮሳት መኖሪያና መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለማድረግ የሚያስችሉ የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶች ተነድፈዋል:: ፕሮጀክቶቹም ግምታቸው 14,156 ብር የሆነ የንብ ርባታ፣ 60,156 የሆነ የዶሮ ርባታና የአትክልት ልማት አማራጭ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ ለተግባራዊነታቸው የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን::

ጉዞአችን በርካታ ቅዱሳት መካናት ወደ ሚገኙበት ምሥራቅ ጎጃም ሀ/ስብከት ስናደርግ ደግሞ ከተጠኑት ጥንታውያትና ታሪካውያት ገዳማት ውስጥ የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳምን እናገኛለን:: የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስን ገዳም በ1297 ዓ.ም. በዐፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት እንደ ተመሠረተ እና ከአንድ ሺህ በላይ መነኮሳት ይኖሩበት እንደ ነበረ ታሪክ ያስረዳል:: ለዘመናት በርካታ ሊቃውንትን ሲያፈራ የኖረው



www.eotcmk.org

የገዳሙ የአብነት ት/ቤት የቆየ ጥን ካሬውንና ክብሩን እንደ ያዘ ባይገኝም ዛሬም የቅኔ፣የዜማ፣የሐዲሳት መጻሕፍት ትርጓሜ እየተሰጠበት ይገኛል:: በተለ ይም የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜው ት/ቤት ብዙ ሊቃውንትን በማፍራት ከፍተኛ አስተዋፅዖ በማበርከት ላይ ይገኛል::

ጥንታዊው የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ብዛት ያላቸው ጥንታዊ እና ታሪካዊ ቅርሶች ባለቤት ነው:: ይሁን እንጂ ቅርሶቹ በአግባቡ ባለመያዛቸው ለብልሽትና ለዘረፋ በተጋለጠ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ:: ይህን ችግር ለመቅረፍ ግምቱ 768,000 ብር የሆነ ቤተ መዘክርና፣ መነኮሳቱን በምግብ ራሳቸ ውን ለማስቻል ግምቱ 25,000 ሺ ብር የሆነ የንብ ርባታና ግምቱ 52,000. ብር የሆነ የእርሻ ልማት ፕሮጀክቶች ተጠንተዋል:: የእርሻ ልማት ኘሮጀክቱ በገዳሙ መነኮሳት መተግበር የጀመረ ሲሆን የንብ ርባታው በከፊል ከግል በጎ አድራጊ በተገኘ የ15,000 ሺህ ብር ርዳታ በመካሄድ ላይ ይገኛል:: የቤተ መዘክሩ ፕሮጀክት ግን ሙሉ በሙሉ የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል::

በሀገራችን መሥዋዕተ ኦሪት ይ ሠዋባቸው ከነበሩት ጥቂት ጥንታ ውያት ቅዱሳት መካናት ውስጥ የርዕሰ ርዑሳን መርጡ ለማርያም ገዳም አንዷ ናት:: በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት የምትገኘው የመርጡ ለማርያም ገዳም አሁን ባለችበት ቦታ ላይ አብርሃ ወአ ጽብሐ በ330 ዓ.ም. ያሠሩት የእመቤ ታችን ቤተ መቅደስ እስከ 852 ዓ.ም ድረስ ሲያገለግል ቆይቶ በዮዲት ጉዲ ት የጥፋት ዘመን መቃጠሉ ይነገ ራል:: ይህ በ852 ዓ.ም. የፈረሰው ቤተ ክርስቲያን ቅሪቱ እስከ አሁን በቦታው ላይ ይገኛል:: በገዳሙ ውስጥ ጥንታው ያትና ታሪካውያት የሆኑ ከነገሥታቱ የተበረከቱ አልባሳት፣ የግራኝ አሕ መድ ካባ እና ብዛት ያላቸው የብራና መጻሕፍት ይገኛሉ:: ከዚህ በተጨማሪ ተተኪ ሊቃውንትን በማፍራት የሚታ ወቀው የአራቱ ጉባኤያት ትምህርት ቤት ከአንድ መቶ ኀምሳ በላይ የሚ ሆኑ የአብነት ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ይገኛል::

ቀደም ሲል ገዳሙ ይተዳደርበት የነበረው መሬት በመወረሱ ምክንያት የገዳሙ መነኮሳት በቂ መተዳደሪያ እንዲያጡ ሆነዋል:: የገዳሙን መነኮ ሳት መሠረታዊ ፍላጐት ለማሟላት እና ጥንታዊ ቅርሶች በአግባቡ እንዲ ያዙ ለማድረግ ግምታቸው 88ሺ 97 ብር የሆነ የእርሻ ልማት፣ የቅርሳ ቅርስ መደርደሪያ፣ የአትክልት ልማት እና የንብ ርባታ ኘሮጀክቶች ተጠንቶላ ቸዋል:: በአሁኑ ሰዓት የእርሻ ልማት ኘ ሮጀክቱን የገዳሙ መነኮሳት በከፊል በመተግበር ላይ የሚገኙ ሲሆኑ የአትክልት ልማት ኘሮጀክቱ ከሸራ ተን ሐዲስ ፈለገ አብርሃም ሠራተኛ ጉባኤ በተገኘ የ7,000 ብር ድጋፍ ተተግብሯል::

ከዚህም በተጨማሪ የቅርስ መደ ርደሪያው በበጎ አድራጊዎች ዕርዳታ ተ ሠርቶ ንዋያተ ቅድሳቱ በአግባቡ ለመቀመጥ ችሏል:: በምሥራቅ ጎጃም ሀ/ስብከት ያደረግነውን ቆይታ አጠና ቀን ወደ ደቡብ የሀገራችን ክፍል ስን ጓዝ በጅማ እና በከፋ ሻካ ቤንች ማጂ ዞን ሀ/ስብከት የተጠኑትን የጅማ መረዋ እና የአንድራቻ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያንን እንመለከታለን::

የጅማ ሀ/ስብከት ከአዲስ አበባ 318 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል:: በሀገ ረ ስብከቱ የሚገኙት ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት በካህናት እና በንዋየ ቅድ ሳት እጥረት ምክንያት አገልግሎት የ ማይሰጥባቸው ሆነዋል:: መረዋ በሚገ ኘው የሀገረ ስብከቱ የእርሻ መሬት ላይ አንድ ገዳም እና መንፈሳዊ ት/ቤት በመመሥረት፣ ከየወረዳው የሚውጣጡ የአካባቢውን ልጆች ለማስተማር ይቻል ዘንድ ግምቱ 55,825 ብር የሆነ የእርሻ ልማት ኘሮጀክቶች እና የፕሮጀክቶች ውስጥም ተጠንተዋል:: የእርሻ ልማቱ በሀ/ስብከቱ በከፊል በመተግበር ላይ ይገኛል:: የአብነት ት/ቤት ተማሪዎች መኖሪያ ግንባታ ፕሮጀክት የበጎ አድራጊ ዎችን ርዳታ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል:: በቦታው ለሚገኙ የአብነት መምህርም ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 300.00 ከበጎ አድራጊዎች በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እየተደጎመ ይገኛሉ::

በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ያደ ረግነውን ቆይታ አጠናቀን ዳግም ቅኝ ታችን ወደ ሰሜን ምሥራቅ የሀገራችን ክፍል ስናደርግ በቅድሚያ በደቡብ ወሎ ሀ/ስብከት የሚገኘውን የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ገዳም እናገኛለን:: የአባ ጊዮ ርጊስ ዘጋሥጫ ገዳም በደቡብ ውሎ ዞን፣በከለላ ወረዳ በጥራንጥር ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ዘጠና ኪ.ሜትር ቁመት ካለው አሰርጥ መንገድ አናት ላይ ይገኛል::

ገዳሙ በዐፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግ ሥት በአባ ጊዮርጊስ የተመሠረተ ሲሆን በወቅቱም ወደ 300 የሚጠጉ መነኮሳት እንደ ነበሩት ይነገራል:: ገዳሙም ታላቅ የቤተ ክርስቲያን የሥነ ጽሑፍ ሀብቱ የኾኑቱ እንደ መጽሐፈ ምሥጢር፣አር ጋኖን፣ ሰዓታትና የመሳሰሉት መጻሕ ፍት ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ በተባለው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ የተጻፉት በዚሁ ቦታ ነው::

*ገዳሙ ይተዳደርበት የነበረው እጅግ ሰፊ የመሬት ይዞታ በመሬት ላራሹ ዐ ዋጅ ተወርሷል:: በዚህም የተነሳ የገዳሙ መነኮሳት ካጋጠማቸው የቀለብ ችግር ፣ የውኃ ጥምና እርዛት የተነሣ* በቅርብ ጊዜ እንኳን ገዳሙን ሦስት መነኮሳት እስኪቀሩት ድረስ ለመፈታት አድርሶታል:: በሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በአቡነ አትናቴ ዎስ ጥረት በአሁኑ ወቅት በገዳሙ እንደ ገና በመሰባሰብ 19 ወንድ መነኮሳትና 11 ሴት መነኮ ሳት ይገኛሉ::

ይህ ታሪካዊ ገዳም ያለበትን ችግር ለመቅረፍ በደሴ ከተማ ላይ የዐፀደ ሕፃናት ኘሮጀክት እንዲሁም ግምቱ 61 ሺ የሆነ የመጠጥ ውኃ አገልግሎት ኘሮጀክት ተጠንቷል:: ለተግባራዊነቱም የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል:: ችግ ሩን በጊዜያዊነት ለመቅረፍ ከ1995 ዓ. ም ከደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ሰንበት ት/ቤት የጎልማሶች ክፍል በየዓመቱ በሚገኝ የ3000.00 ድጋፍ የዓመት ቀለብ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል::

ወደ ሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ስናመራ ሌላው በጥናቱ የተካተተው ንና ጥቅጥቅ ባለ ገደላማ ደን የተከበ በውን የደብረ ዘመዳ ቅድስት ማር ያም አቡነ በርተሎሜዎስ የአንድነት ገዳምን እና ገኛለን:: ገዳሙ በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት በቆቦ ወረዳ በጀ መዶ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ውስጥ ይገኛል:: በአሁኑ ሰዓት በገዳሙ 35 ወንድና 21 ሴት መነኮሳት ያሉ ሲ ሆን እነዚህ መነ ኮሳት የገዳሙ ብቸኛ መተዳደሪያ የሆነውን ከ2–2.5 ሄክታር የሚሆን መሬት በማረስ የሚ ተዳደሩ ቢሆንም የሚያገኙት ምርት ስድስት ወር እንኳን የሞላ ጊዜ ስለ ማይመግባቸው ቀሪውን ጊዜ በልመና ካልተገኘም በችግር እና በረኀብ ያሳልፉታል:: የመነኮሳቱን ዘርፈ ብዙ ችግር ለማ ቃለል ቦታው ለግብርና ሥራ አመቺ ባለመሆኑ ግምቱ 62,500/ ስድሳ ሁለት ሺ አምስት መቶ/ የሆነ የሚከራይ ሱቅ ግንባታ እና 200, 000/ሁለት መቶ ሺ/ ብር የሆነ ዘመናዊ ዳቦ ቤት ፕሮጀክት ሰነድ በቆቦ ከተማ ተግባራዊ ለ ማድረግ ተዘጋጅቶ የበጎ አድራጊ ዎችን ድጋፍ በመጠበቅ ላይ ይገኛል:: በሰሜን ምሥራቅ የሀገራችን ክፍል ያደረግነውን ቆይታ አጠናቀን ወደ መካከለኛው የሀገራችን ክፍል ስናመራ በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱት ገዳማት ክርስትና ወደ ኢት ዮጵያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የተመሠረተ እንደ ሆነ የሚታመንበትን በምዕራብ ሸዋ ሀገ ረ ስብከት የሚገኘውን የጋራ መናገሻ መድኃኔዓለም ገዳም እናገኛለን:: በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግራኝ አ



www.eotcmk.org

ሕመድ የጥፋት ወረራ የገዳሙ አግልግሎት ቢታጎልም በ1923 ዓ.ም ንግሥት ዘውዲቱ የእመቤታችንን፣ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ደግሞ የመድኃኔ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን በማሠራት እንደገና እንዲቋቋም አድርገዋል:: በአሁኑ ሰዓት በገዳሙ አንድ መቶ ዐሥር /110/ የሚደርሱ መነኮሳት ሰባ/70/ የሚሆኑ የቅኔ እና የድጓ የአብነት ትምህርት ተማሪዎች ይገኛሉ:: የገዳሙ ዋና መተዳደሪያ የነበረው የእርሻ መሬት በለውጥ ምክንያት በመወሰዱ በቀሪው መሬት የሚለማው የገዳሙን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት ባለመቻሉ ገዳማውያኑን ለተመጽዋችነት ዳርጓቸዋል:: በገዳሙ መሥራት የሚ ችል በቂ የሰው ኃይል በመኖሩ ግምታቸው 58 ሺ ብር የሚሆን የሽመና እና የወፍጮ ፕሮጀክቶች ተጠንተውላቸው ቀደም ብለው በኖርዌይ ይኖሩ ከነበሩ የግል በጎ አድራጊዎች በተገኘ የ 37 ሺ ብር ድጋፍ ሁለቱም ፕሮጀክቶች ተተግብረዋል::

ወደ ምዕራቡ አቅጣጫ ስናመራ በምሥራቅ ወለጋ ሀ/ስብከት ነቀምቴ ከተማ በ1992 ዓ.ም. በብፁዕ አቡነ ኤልያስ የተገደመውን የምስካበ ቅዱሳን ዑራኤል ወሳሙኤል ዘዋልድባ ገዳምን እናገኛለን:: በምዕራቡ የሀገራችን ክፍል ያለውን የካህናት ችግር ለማቃለል የተመሠረተው ይህ ገዳም በአሁኑ ሰዓት ከጠቅላይ ቤተ ክህነት በተመደበለት አነስተኛ በጀት ለተወሰኑ መነኮሳት እና ተማሪዎች የመኖሪያ እና የምግብ ማብሰያ ቤት ግንባታ ተጠናቆ ከሀገረ ስብከቱ የተውጣጡ ተማሪዎችን በማሰባሰብ የንባብ፣የቅዳሴ፣ እና የቅኔ ትምህርት በማስተማር ላይ ይገኛል:: ይህ ገዳም በአካባቢው የሚታዩትን ችግሮች ለማቃለል ተስፋ የተጣለበት በመሆኑ ተማሪዎች ከመንፈሳዊ ትምህርት በተጨማሪ ዘመናዊ ትምህርትም እንዲማሩ ለማድረግ ፣ በገቢውም ገዳሙንና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቱን ለመደጎም ግምቱ 900 ሺህ ብር የሆነ ዘመናዊ ት/ቤት ግንባታ እና ግምቱ 100 ሺህ ብር የሆነ የወተት ላም ርባታ ፕሮጀክት ተጠንተው የበጎ አድራጊዎችን ድጋፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል::

ይህን የምስካበ ቅዱሳን ዑራኤል ወሳሙኤል ዘዋልድባ ገዳምን ለቀን አቅጣጫችንን ወደ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ስናደርግ አሶሳ ከተማ ከመድረሳችን በፊት 120 ኪ.ሜ ሲቀር የቂልጡ ካራን ከተማ እናገኛለን:: በዚህ ከተማ ቀደም ሲል የምዕራብ ወለጋ እና የአሶሳ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ቀዳማዊ ታኅሳስ 30 ቀን 1991 ዓ.ም የመሠረት ድንጋይ ያኖሩበትን በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስም የተሰየመውን ቦታ እናገኛለን:: ብፁዕነ ታቸው እዚህ ቦታ ላይ የመሠረት ድንጋይ ያኖሩት ለምዕራብ ወለጋ ፣ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና ለአካባቢው የሰባክያነ ወንጌል እና የካህናት ማፍሪያ የሚሆን ገዳምና የአብነት ት/ቤት ለማቋቋም ካላቸው ጽኑ ፍላ ጐት ነበር:: የአካባቢው ምእመናንም በቦታው ላይ የመቃኞ ቤት በመሥራት በወር አንድ ጊዜ የምህላ ጸሎት እና የወንጌል ትምህርት እየተማሩበት ይገኛሉ::

የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ያየለበት ሥፍራ በመሆኑ ማኅበረ ቅዱሳንም የብፁዕነታቸውን ጅምር ከግብ ለማድረስ ግምቱ 500,000 /አምስት መቶ ሺ ብር/ የሆነ የተቀ ናጀ የልማት ፕሮጀክት ማለትም የመነኮሳት እና የተማሪዎች መኖሪያ ቤት ግንባታ፣የመጠጥ ውኃ፣ የንብ ርባታ እና የአትክልት ልማት ፕሮጀ ክቶች ተጠንተዋል:: ማኅበሩ ፕሮጀ ክቶቹን በምዕራፍ በመከፋፈል ከ19 94 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል:: ከኖርዌ ትሮን ድሂም እና ከግብፅ አባሲያ ከሚገኙ ምእመናን በተገኘ ድጋፍ አምስት ክፍል የተማሪዎች መኖሪያ ቤት ፣የመመገቢያ አዳራሽ እና የምግብ ማብሰያ ቤት ግንባታ ተጠናቆ ርክክብ ተፈጽሟል::

ጽሑፋችንን ስናጠቃልል በተከታታይ ካቀረብነው የፕሮጀክት ማስተዋወቂያ ጽሑፍ በአባቶቻችን እና እናቶቻችን ትጋት የቆዩልን ቅዱሳን መካናትና አብነት ት/ቤቶች ዛሬ በከፋ ችግር ላይ ይገኛሉ:: ካጋጠሟቸው ችግሮች የተነሣ ገዳማውያኑ ባዕታቸውንና በገዳማቸው የሚገኙ ቅርሶችን በመተው እየተሰደዱ ነው:: መምህራን ለእነሱም ሆነ ለተማሪዎቻቸው የሚቀመስ እያጡ በርካታ ጉባኤያት እየታጠፉ ነው:: ይህንን ችግር ለመቅረፍ ምእመናን በየግላቸሉ የሚችሉትን ሁሉ እያደረጉ ቢሆንም ችግሩ ሰፊና ለዘመናት ስር የሰደደ በመሆኑ የሚደረገው ድጋፍ ተፈላጊውን ያህል ውጤት አላመጣም:: ብዙው ርዳታ በጥናት ላይ ያልተመረኮዘና የተበታተነ በመሆኑም ድምር ውጤቱ በጉልህ አልታየም::

ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት በጥናት ላይ የተመሠረተና የሁሉንም አካላት ቅንጅትና ርብርብ የሚጠይቅ ነው:: ስለሆነም ማኅበረ ቅዱሳን ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ያለውን የተማረ የሰው ኃይል ሞያ ከምእመናንና ከጽዋ ማኅበራት የገንዘብ ድጎማና ከገዳማውያኑ ጸሎትና ጉልበት ጋር በማቀናጀት የልማት ሥራዎችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ነው:: ይህም ጅምር አበረታች ውጤት እያሳየ ነው::

ነገር ግን ይህንን ጅምር ማኅበሩ አጠናክሮ ለመቀጠልና ቅዱሳት መካናቱ ከችግር ተላቀው በልማት ራሳቸውን ለማስቻል ለዚህ የተቀደሰ ሠናይ ምግባር መሳካት ፍላጎት ያላቸውን አካላት ሁሉ ትብብር ይፈልጋል:: በመሆኑም በዚህ አጭር ዳሰሳ የተካተቱትንም ሆነ ሌሎች በማኅበሩ የተጠኑ በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ለማድረግ ማኅበሩ ሦስት የአፈጻጸም ስልቶችን ነድፏል::

የመጀመሪያው:-የፕሮጀክት ሰነድ ማኅበሩ ለበጎ አድራጊዎች ከሰጠ በኋላ ከበጎ አድራጊዎች ገንዘቡን ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ከገዳሙ፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ፣ከንዑስ ማዕከል እንዲሁም ከሀ/ስብከት የተውጣጣ አስፈጻሚ አካል በማ ዋቀር ተግባራዊ የሚያደርግበት፣ በጎ አድራጊዎች በፈለጉት መልኩ ክትትል እና ቁጥጥር የሚያደርጉበት ነው:: ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ማኅበሩ የፕሮጀክት ሰነዱን ለበጎ አድራጊዎቹ በመስጠት ገንዘቡን ሳይቀበል በፕሮጀክት ክትትልና ግምገማው ላይ የሚሳተፍበት ነው:: ሌላው የመጨረሻው አማራጭ ማኅበሩ ፕሮጀክት ሰነድ ሰጥቶ ገንዘብ ሳይቀበልም፣በክትትልና ግምገማ ውስጥ ሳይገባም በአማካሪነትና አስፈላጊውን ሪፖርት በማግኘት ደረጃ የሚሳተፍበት ነው:: ለእነዚህ አማራጮች ሀ/ስብከቱ፣ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ገዳም ፣ድጋፍ ሰጪውና ፕሮጀክቱን የሚከታተለው ማኅበረ ቅዱሳን በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ሰነድ ላይ የስምምነት ውል ይፈራረማሉ:: በእነዚህ አማራጭ የማስፈጸሚያ ስልቶች ከማኅበሩ ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚፈልጉ ማኅበረ ምዕመናን ወምዕመናት፣የጽዋ ማኅበራት፣መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ ተሳታፊ ቢሆኑ ቅዱሳት መካናቱ ወደ ቀድሞ ይዞታቸው እንደሚመለሱ ማኅበሩ እስከ አሁን ከሠራቸው ጅምር ሥራዎች መረዳት አያዳግትም:: ስለዚህ ሁሉም አካል በሚችለው መንገድ ሁሉ ከማኅበረ ቅዱሳንጎን ለጎን በመሆን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን እና ለትውልድ የሚጠቅም ተግባር እንዲሠራ ማኅበሩ ጥሪውን ያስተላልፋል::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.eotcmk.org

# አቡነ ዘዮሐንስ ዘክብራን ገብርኤል

ምትኩ ዘለቀ/

በጣና ሐይቅ ደሴቶች ውስጥ የሚገኙ ገዳማትን ከመሠረቱትና ሰባቱ ከዋክብት ተብለው ከሚጠሩት ቅዱሳን አባቶች አንዱ የሆኑት አቡነ ዘዮሐንስ ዘክብራን ገብርኤል ትውል ዳቸው በሰሜን ሸዋ መርሐ ቤቴ ሲሆን አባታቸው ዘካርያስ እናታቸው ደግሞ ሶፊያ ይባላሉ:: ወላጆቻቸው እግዚአብሔርን የሚፈሩ ጸዋሚ ተነራሚ ናቸው:: ሁል ጊዜ መንፈሳዊ ተግባራት ከማድረግ የማይቆጠቡ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ጻድቃን ነበሩ:: እግዚአብሔር ግን ሁልጊዜ የዐይን ማረፊያ የሚሆኑ ልጆችን እንዲሰጣቸው በጸሎት ይጠይቁ ነበር::

አንድ ቀንም ዘካርያስና ሚስቱ ሶፍያ በእመቤታችን ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተው ከሥዕሏ ፊት ሰገዱ:: በትሕትናና በፍቅርም «የሚያስደስተን /ደስ የሚያሰኘን/ ልጅ ስጪን» ብለው እመቤታችንን ጠየቁ::

ዘካርያስም በጸሎቱ «አቤቱ የሚያሰቃዩኝ ጠላቶቼስ ደከሙ፤ ወደቁ፤ ወርቅንና ብርን ልዩ ልዩ ልብሶችንም ሰጠኸኝ:: ለዐይኖቼ ደስ የሚያሰኝ በጎ ልጅ ስጠኝ፤» አለ:: «አንቺም የድኻ እናት እመቤቴ÷ ኀዘኔን አርቂልኝ÷ በሞቴ ጊዜም የጠላቴ መዘባበቻ አታድርጊኝ::» ከዚህ በኋላ ሌሊት «ዕንቊ ባሕርይ» የሚባሉ ሁለት መላእክት ታዩት:: ዕንቊዉንም አምጥተው ሰጡት:: ሶፍያ /የዘካርያስ ባለቤት/ በራእይ የሸዋ ሰዎች ሁላቸው የምድር ዳርቻዎች ሕዝብ ሁሉ የሚበሉት የቀፎ ማር አየች:: በነቁም ጊዜ ስለ አዩት ሕልም እርስ በርሳቸው ተነጋግረው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይኹን አሉ::

ከጥቂት ቀኖች በኋላም የከበረች ሶፍያ ጸነሰች:: ጽንሷም ታወቀ:: የአጥቢያ ኮከብ የሚመስል÷ ብርሃኑም እንደ ፀሐይ የሚያበራ ወንድ ልጅም ወለደች:::

አባትና እናቱም በተወለደው ልጅ ደስ ብሏቸው እስከ 40 ቀን ድረስ ታላቅ በዓል አደረጉ:: ይኸውም የተወለደበት ኅዳር 13 ቀን ነው:: በ40 ቀኑም እናቱ ከግዳጅዋ በምትነጻበት ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ወሰዱት:: ቄሱም ሕፃኑን ባየው ጊዜ ደስ ብሎት ትንቢት ተናገረለት:: ለዚህም እንደዚሁ በወገቡ የሚታጠቀው ጠፍር ነበረው:: በእውነት ከእናቱ ማኅፀን ተመርጧልና:: ዘዮሐንስ ዘክብራን ገብርኤል ከአደገ በኋላ አንድ ቀን ለጸሎት በመንፈቀ ሌሊት ከእመቤታችን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳለ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስና ነቢዩ ኤልያስ በእጆቻቸው ቆብንና አስኬማን ይዘው ታዩት:: ለአባታችን ዘዮሐንስም ሰጡት:: «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና እመ ቤታችን ማርያም ሁለቱ እሊህን መዓርጎች እንሰጥህ ዘንድ አዘዙን» አሉት:: እርሱም እጅ ነሳቸው፤ በደስታም ተቀበላቸው::

ከዚህ በኋላም ለስድስት ቀናት ለብቻው ተቀምጦ ሳለ ትንሽ ደመና መጥታ ተሸከመችው፤ ወደ ኢየሩሳሌምም አደረሰችው:: ይኸውም የጌታችን መቃብር ነው፤ መቃብሩንም ተሳለመ:: ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ በዚያ ተጠመቀ:: ዳግመኛም ወደ ጳጳስ ሄዶ በዚያ የዲቁና መዓርግ ተቀበለ:: ጳጳሱም አባታችን ዘዮሐንስ «ከሁሉም ቅዱሳን ይልቅ መንፈስ ቅዱስ አድሮብኻል» አለው:: ዳግመኛም ለብዙዎች መነኮሳት አባት እንደሚሆን÷ ሕዝቡንም እንደሚያስተምር÷ ወደ ሃይማኖትም እንደሚመልሳቸው ትንቢት ተናገረ:: ይህንም ብሎ ቡራኬ ሰጠውና ጸሎትን አደረጉ:: ከዚህ በኋላ ደመና መጣችና ተሸክማ አባቱና እናቱ ወደሚኖሩበት ወደ ሀገሩ ወደ ሸዋ አደረሰችው:: አባቱና እናቱም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ አላወቁም ነበር፤ «በፊቱ ላይ የሚከበው ብርሃን ምንድን ነው?» ይሉት ነበር እንጂ:: የሚወርድለት ብርሃን ይጨምርለት ነበር:: እርሱም ጾምንና ጸሎትን፣ ንጽሕናንና ቸርነትን ይጨምር ነበር::

ከዚህ በኋላ 25 ዓመት በሆነው ጊዜ ከዚያ ሀገር መኳንንት ልጆች መልከ መልካም ሴት አጬለት:: አባትና እናቱም:- «ልጃችን ሆይ÷ በሰርግህ ደስ ይለን ዘንድ ና እንሂድ» አሉት:: አባታችን ዘዮሐንስም «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ በነፍሱ ከተጐዳ ለሰው ምን ይጠቅመዋል? ተውኝ ከልቤ ጋር ልምከር» አላቸው:: ይህንም ብሎ አባትና እናቱ ከዚህ ከኃላፊው ዓለም ድካም ያርፉ ዘንድ ዳግመኛም እንዳያማክሩት÷ ሚስት አግብቶ ሰርግም አድርግ እንዳይሉት ሁልጊዜ ይጸልይ ጀመር:: ከጥቂት ቀኖች በኋላም አባትና እናቱ ዐረፉ::

አባታችን ዘዮሐንስም የአባትና እናቱን ተዝካር ካወጣ በኋላ ወላጆቹ የተውትን ወርቅና ብር÷ ልብሶችን÷ ከብቶችንና በጐችን ለችግረኞች ሰጠ:: ከዚህ በኋላ ወደ ገዳም ሄደ:: በዚያም በእመቤታችን ስም የተሠራች ቤተ ክርስቲያን አግኝቶ በዚያ ጸሎት አደረገ:: ሥዕሏም ተናገረችው:: «ከዛሬ ጀምሮም ወደ ደብረ ሊባኖስ ሂደህ በዚያ ቆብንና አስኬማን ተቀበል» አለችው:: እመቤታችን እንዳለችው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ውኃ እየቀዳ፣ እህልም እየፈጨ፣ ሣርም እየተሸከመ በየዕለቱም እንጨት እየለቀመ ኖረ:: በሥራውም ሁሉ ማኅበሩን ደስ አሰኛቸው:: «ሁሉም ዐዋቂና ደግ አገልጋይ አገኘን» አሉት:: በገዳሙ አገልግሎት ለሰባት ዓመት ያህል ኖረ:: ከዚህ በኋላም አባ ሕዝቅያስ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አደረጉት:: በቀን ሰባት ጊዜ በሌሊት ሰባት ጊዜ ያጥን ነበር:: በየጧቱም አራቱን ወንጌሎች ያደርስ ነበር:: የዳዊት መዝሙርንም ሰባት ጊዜ ያደርስ ነበር:: አብዝቶ ይሰግድ ነበር:: የሌሎች ጸሎቶቹ ግን ቁጥር የሌላቸው ናቸው:: እንዲህ እየተጋደለ በትዕግሥትና እግዚአብሔርን በመፍራት 27 ዓመት ኖረ:: ምግቡም የባሕር ጐመን ነበር:: እንደተላጠ የዱር እንጨትም መሰለ፤ ቀድሞ የነበረ ሰውነትና መልኩም ተለወጠ:: «ሰውነቱን የሚወድ ስለ እኔና ስለ ወንጌል በመከራ ይጣላት» ያለውን የወንጌል ቃል ፈጸመ:: አባታችን ዘዮሐንስ ጌታውን በእውነት ተከተለው፤ የፈጣሪው አገልጋይ ይሆን ዘንድም መስቀሉን ተሸከመ:: ይህንም ሁሉ ፈጽሞ ኖረ:: ጌታችንም ተገልጾ «ከእናትህ ማኅፀን ሳትወጣ እኔ ዐውቅሃለሁ» አለው:: ይህንም ብሎ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ያደረገለትን÷ ከመወለዱ አስቀድሞ የሆነውን÷ ከተወለደም በኋላ እስከዚያ ቀን ድረስ ያደረገለትን፣ አባቱንም ከዐመፀኛ በዶልያ እጅ ከመሞት እንዳዳነው እናቱንም ዐቁባት ሊያደርጋት እንደ ነበር ምሥጢሩን ሁሉ ነገረው::

ይህንንም ብሎ ዳግመኛ ተነጋገረው:: «ከዛሬ ጀምሮ ስምህ ዘዮሐንስ ይሁን፤ አንተ የዓለሙ ሁሉ ደስታ ነህና፤ የሚያለቅሱም በአንተ ደስ ይላቸዋል» አለው:: ዳግመኛም በዚያ ጸጋን÷ ክብርንና ባለሟልነትን ታገኛለህና:: ወደ ትግሬና ወደ ኢየሩሳሌም አውራጃዎች ሂድ!! እነሆ የኢየሩሳሌምን መክፈቻ ሰጥቼሃለሁ:: መክፈቻዋም በአንተ እጅ ይሁን፤ አንተም ከርሷ ለሚገባና ለሚወጣ ለልጆችህና ለልጅ ልጆችህ ክፈት::» አለው::

በዚያን ጊዜ አባታችን ዘዮሐንስ ጌታችን እንደ ሆነ ዐወቀ:: በጉልበቱም ተንበርክኮ ሰገደ:: «ቃል ለቃል ስለ ተነጋገርሁና ለእንግዳ ሰው ስለ መለስኩልህ አቤቱ ኃጢአተኛ ሰው እኔ መቀመጤና መነሣቴ ምንድን ነው? እንደ ጐስቋላም ሆንኩ÷ ይቅር በለኝ» አለው:: መድኃኒታችንም:- «ወዳጄ ዘዮሐንስ ሆይ÷ እንዲህ አትበል! ይህስ ነገር ለሰነፎች ነው፤ ለአንተ ግን ይህ አይገባህም» አለው:: ይህንም ብሎ ቡራኬ ሰጠው:: ወደ ቀደመ ቦታው ወደ ሰማይ ዐረገ:: አባታችን ዘዮሐንስም በዚያች ሌሊት ምንም ሳይቀምስ አደረ:: በማግሥቱ የሰኞ ቀን ጧት ሲሆን ብርሃን ያለባት ደመና ቅዱስ ቅዱስ ሚካኤል በቀኙ ገብርኤል በግራው ከርሱ ጋር ሳሉ ተሸክማው ወደ ትግራይ ምድር አደረሰችው:: ወደ ትግራይ ምድር በደረሰ ጊዜ በሽተኞችን በመፈወስ÷ አጋንንትን በማውጣት÷ የዐይነ ስውራን ዐይን በማብራት÷ አንካሳዎችንና ልምሾዎችን በማቅናት ብዙ ምልክቶችን አደረገ:: በአባታችን ዘዮሐንስም እግዚአብሔር የሆድ በሽታን





www.eotcmk.org

አመጣበት፤ በዚያ እንዲቆይ አልፈቀደ
ለትምና:: እጅግም ታሞ ሥጋው ሁሉ
አለቀ:: ከዚህ በኋላ ደመና መጣችና
ተሸክማ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ጌታችን
መቃብርም አደረሰችው:: ከዚያም ከጳጳ
ሳቱ አለቃ ከአባ ዮሐንስ ጋር ተገናኘ::
የጳጳሳቱ አለቃ አባ ዮሐንስም ባየው ጊዜ
እጅግ ደስ አለው:: «አባታችን ዘዮሐ
ንስም ከዚህ ምን አመጣህ! የምትፈልገ
ውስ ምንድን ነው? ሁሉ በእጅህ አለና::»
አለው:: አባታችን ዘዮሐንስም:- «የእግዚ
አብሔር ፈቃድ አመጣኝ» አለው:: ይህ
ንም ብለው የእግዚአብሔርን ገናንነቱን
ክብሩንም ሁሉ የእግዚአብሔር መልአክ
በደመና እንዳመጣውና ከዚህ ቦታም እንዳ
ደረሰው ሲጫወቱ አደሩ:: ከዚህ በኋላ
ጥቂት ቀናት እንደ ቆየ በደመና ላይ
ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ:: በፍጥ
ነትም ወደ ደራ ሀገር ደረሰ:: በዚያም
መንገዱን ቀጠለና ሮቢት ከምትባል ቦታ
ደረሰ:: በመሸም ጊዜ «ገብርኤል» ወደ
ሚሉት አንድ ዓሣ አጥማጅ ሰው÷ ሚስቱ
ም መስቀል ክብራ እያሉ ወደሚጠሯት
ቤት ደረሰ:: ስምን መክፈል ለሰው ልማ
ዱ ነውና ይኸችንም ከፍለው «ክብራ»
ብቻ ብለው ይጠሯት ነበር::

አባታችን ዘዮሐንስ በመስከል ክብራ
ቤት እንደ ደረሰ ከደጁ ተቀመጠ:: እጅ
ግም በር አንኳኳ:: መስቀል ክብራም
ስምታ ፈጥና ወጣች:: እንዲህም አለችው:
- « አንተ እንግዳ መነኩሴ ከወዴት ሀገር
መጣህ? ከማንስ ወገን ነህ?» አለችው::
አባታችን ዘዮሐንስም «ለመነኩሴ ሀገርና
ዘመድ የለውም፤ ሀገሬም ሩቅ ነው፤ ዘመ
ድም የለኝም» አላት:: ይህንም ብሎ «አሳ
ድሪኝ» አላት:: ያችም ሴት ይህን ነገር
በሰማች ጊዜ ወደ ውስጥ አስገባችው::
ለአባታችን መቀመጫ አነጠፈችለት::
«ባሌ ገብርኤል እስኪመጣ ተቀመጥ÷
ጥቂትም ዕረፍ» አለችው:: ገብርኤል
ግን ዓሣ ወደ ማጥመድ ከሄደ ጀምሮ አም
ስት ቀን ሆኖት ነበር:: እስከዚያች ቀን
ድረስም ዓሣ አልያዘም ነበር:: በዚያች
ቀን ግን አባታችን ዘዮሐንስ ከቤታቸው
ከገባ ጀምሮ ታንኳው እስከ ማይችለው
ድረስ ለመንገር የማይቻል ብዙ ዓሣ
ተያዘ፤ በጭንቅም ወደ ባሕሩ ዳር ደረሰ::
ክብራ ግን አባታችን ዘዮሐንስ ወደ ቤቷ
በገባ ጊዜ እህል ጎታው እስከ አፉ ድረስ
ሞልቶ አየችው:: የቅቤ ማሰሮውንም
የዘይት ዕቃውንም እንደዚሁ ሁሉም በየቦ
ታቸው እስከ አፋቸው ድረስ ሞልተው
አየቻቸው::

ይህንም ሁሉ ዐይታ አደነቀች:: በል
ቧም «በውኑ አምላክ ወደ እኔ ወረደ
ይሆን? ወይስ መልአክ ሰው መስሎ
ወረደ ይሆን?» አለች:: ከዚህ በኋላም
ባሏ ጠራት:: ወደ ባሕሩ ዳርም ወርዳ
ባሏን:- «ጌታዬ ያዘገየህ ምንድን ነው?»
አለችው:: «ከሄድኩ ጀምሮ እስከዚህች
ቀን ድረስ አልያዝኩም፤ ዛሬ ግን ታንኳ
ዬን ሲያስጥመው ታያለሽን» አላት:: ከዚ
ህ በኋላ ሚስቱ ክብራ:- «እኔንም ዛሬ
ያገኘኝ ነገር ያስደንቀኛል» አለችው::
ይህንም ብላ እንግዳ መነኩሴ እንዳለ÷
ከቤታቸው በረከት እንደ ወረደ
ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረ
ሻው ድረስ ነገረችው:: ከዚህ በኋላ
የክብራን ባለቤት ገብርኤልም አባታ
ችንን ተገናኘው:: ክብራና ባሏም እጅግ
ደስ አላቸው:: ደግና መንፈሳዊ÷ እንደ
ፈጣሪያቸውም ይቅር ባይ÷ አባታቸው
ወደ እነርሱ ወርዷልና:: ሰዓቱ በመሸ
ጊዜም ማዕድ አቀርበው ጠሩት÷ በመ
ካከላቸውም አስቀመጡት:: ቅዱሳን
በእግዚአብሔር ፈቃድ ተገናኝተዋልና
በዚያች ቀንና በዚያች ሰዓት የተ
ደረገውን ደስታ ማን ይናገራል? ሌሊ
ቱን ሁሉ በደስታና በፍቅር በእግዚ
አብሔር ትምህርት አደሩ:: አባታችን
ዘዮሐንስም እግዚአብሔር እስኪገለ
ጥለት ድረስ በዚያ ቦታ ሰባት ቀናት
ተቀመጠ:: ከዚህ አስቀድሞም የክብራ
ደሴት ክፍሉ እንደ ሆነች ኢየሩሳሌም
በነበረበት ጊዜ ከጳጳሱ ከአባ ዮሐንስ
ዘንድ ተነግሮት ነበር:: ነገር ግን አባ
ዘዮሐንስ እስከህዚች ቀን ድረስ አላ
ወቃትም ነበር:: በስድስተኛውም ቀን
ተኝቶ ሳለ በመንፈቀ ሌሊት የእግዚ
አብሔር መልአክ ታየው:- «ከዛሬ ጀም
ሮም በፊትህ ወደ አለች ወደዚያች
ደሴት ሂድ» አለው:: ይህንም ብሎ
በእጆቹ አመልክቶ የሚሄድበትን አሳ
የው:: «ለብዙዎችም መነኮሳት አባት
ትሆናለህና ዕረፍ» አለው:: ከዚህ በኋላ
ሌሊቱ በነጋ ጊዜ የክብራን ባለቤት
ገብርኤልን ጠርቶ:- «በዚያች በምና
ያት ተራራ በውኑ ሰው አለን ወይስ
የለም?» አለው:: ያም ዓሣ አጥማጅ
«ሰውስ የለም፤ ዓሣ ባጠመድን ጊዜ
ብዙዎች ዓሣ አጥማጆች እናድርበታለን
እንጅ» አለው:: እንዲህ ባለውም ጊዜ
የአባ ታችን የአባ ዘዮሐንስ ልቡን ደስ
አላት:: ራእዩን ግን አልገለጸለትም::
ከዚህ ነገር አስቀድሞ ያች ደሴት ለብ
ዙዎች መነኰሳት እንደምትሆን÷ ገዳ
ማው ያንም እንደሚሰበሰቡባት እስከ
ኋላም ዘመን ድረስ እንደማትጠፋ መስ
ቀል ክብራ ከአንድ መነኩሴ አፍ
ሰምታ ነበር:: ስለዚህም ነገር በየወሩ
መስቀል ክብራ ከግዳጇ በምትነጻበት
ሰሞን ትሄድ ነበር:: ባሏም ይወስዳትና
የዚያችን ደሴት ነገር ይገልጽላት ዘንድ
ጸሎት ታደርግ ነበር:: ስለዚህ ያች
ደሴት በደጊቱ ሴት በመስቀል ክብራ
ስም ተጠራች::

ከዚህ በኋላ አባታችን ስሙ ገብ
ርኤል የሚባል ዓሣ አጥማጅን «እጅግ
ወድጃታለሁና ያቺን ቦታ አያት ዘንድ
ውሰደኝ» አለው:: ገብርኤልም «በረ
ኀብ እንዳንሞት ራታችንን እንያዝ»
አለው:: አባታችን ዘዮሐንስም «እንደ
ዚህ ለምን ታስባለህ! የሚመግብ እግ
ዚአብሔር ስለሆነ የምንወደውን ሁሉ
ይሰጠናል÷ እንሂድ» አለው:: አባታች
ንም ይህን ካለው በኋላ ዓሣ አጥማጁም
ታንኳውን ጫነ:: አባታችን ዘዮሐንስም
በታንኳው አስቀመጠው:: ከዚህ በኋላ
በመሄድ ላይ እንዳሉ አባታችን ዘዮሐ
ንስ ተሰወረ:: ያም ዓሣ አጥማጅ በኋላ
አላየውም:: በእግዚአብሔር ፈቃድ
ወደዚያች ደሴት ደርሶ በባሕሩ ዳር
አገኘው:: አባታችን ዘዮሐንስ ይህንን
ተአምር አልገለጠም:: በጊዜው እስኪ
ገለጥ ድረስ:: «ይህንም ሁሉ አድር
ጋችሁ ሥራ ፈት ባሪያዎች ነን በሉ»
ብሎ መጽሐፍ እንደ ተናገረ:: ሉቃ.
17÷21:: ወደ ክብራ ደሴትም በደ
ረሰ ጊዜ እጅግ ደስ አለው፤ ፈጽሞም
ወደዳት:: ከዚህ በኋላ ያን ዓሣ አጥ
ማጅ አሰናበተው:: «ከዛሬ ጀም ሮስ
ወደ ቦታህ ሂድ! በሕይወትና በሰላ
ምም ያድርስህ! እኔ ግን እስከ ሁለት
ሱባዔ /14 ቀን/ ድረስ ፈጽሜ እመጣ
ለሁ» አለው:: ይህንም ብሎ ዓሣ አጥ
ማጁን በፍቅር ሸኘው:: አባታችን ግን
ያን ጊዜ ስሙ ገብርኤል የሚባል
መልአክ እየመራው ቦታውን ተመ
ለከተ:: በዚያች ደሴትም በምሥራቅ
በኩል ተቀመጠ:: «እግዚአብሔር ብር
ሃን ረድኤቱን ያበራልኛል÷ ከመከራም
ያድነኛል÷ እስከ መጨረሻው ድረስ»
ምን ያስፈራኛል? እያለ ይጸልይ
ጀመር:: እስከ 14 ቀን ድረስ ተቀ
መጠ:: ከዚህ በኋላ በ15ኛው ቀን ክብ
ራ ባሏን ገብርኤልን «ያንን እንግዳ
መነኩሴ ፈጽመን የማንጠይቀው በምን
ምክንያት ነው? ወደ ርሱም የማን
ደርስ ለምንድን ነው? ሞቶም እንደ
ሆነ ሞተ ብለን ያልቀበርነው ወይም
አለ ብለን ያላየነው እግዚአብሔር
እንዴት ይፈርድብን ይሆን! አለችው::
ባሏም «እሺ በጄ!» አላት:: ከዚህ
በኋላ ገብርኤልና ሚስቱ ክብራን ወደ
ዚያች ደሴት ገብተው ይፈልጉት
ጀመር:: ይሁን እንጂ ያለበትን ሥፍ
ራው አጡት:: በጊዜውም ጸሎትን እየ
ጸለየ ከደሴቲቱ በስተምሥራቅ በኩል
በጭንቅ አገኙት:: እጆቹም ጌታው
በመስቀል ላይ እጆቹን እንደ ዘረጋ
ተዘርግተው ከአንድ እንጨት በታች
ተጠግቶ ነበር:: ቃሉን ከመስማት የተ
ነሣ ሰውነት የምትደነግጥለት እርሱም
እንደ ደረቅ እንጨት ከእግሩ ጀምሮ
እስከ ራሱ ድረስ ትሎች እስኪፈጠሩ
እግሮቹ ያለመንቀሳቀስ እንደ ምሰሶ
ተተክለው ነበር:: ትሎችም በላዩ
እየተመላለሱ ነበር:: ከዚህ በኋላ ተገና
ኙትና እጅ ነሱ፤ አልቅሰውም:
"ትሎቹን አታራግፏቸው" አሏቸው::
"እግዚአብሔር የመረጠህ ሆይ! ይቅር
በለን!» አሉት::

አባታችን ዘዮሐንስም "በሥራ
ችሁ ሁሉ የተመረጣችሁስ እናንተ
ናችሁ" አላቸው:: ከዚህ በኋላ ያን
ያመጡለትን ሰጡት:: እርሱም ባረከላ
ቸውና የእግዚአብሔርን ሕግ እያስተ
ማራቸው በደስታ አሳደራቸው:: ከዚህ
በኋላ በማግሥቱ ቡራኬ ሰጣቸውና:
- «እንጦንስ ከሚባል ከሌላ ደሴት
ተቀመጡ» አላቸው፤ ከሴት ጋር
መኖር ለመነኩሴ አይገባውምና::
እነርሱም እስኪሞቱ ድረስ አባታችን
ዘዮሐንስ ባዘዛቸው ቦታ ተቀመጡ::
ከዚያ ቀን ጀምሮም ሴት ወደ ደሴቱ

/ወደ ገጽ ፳፬ ይዞራል/



www.eotcmk.org

# ጋብቻ እና የሰርግ ወጪ

ዲ/ን ፋሲል አስረስ

ስለ ትዳር ሲነሣ እንደ ዋናነት ጐልቶ የሚታሰበው የሰርግ ወጭ ነው። በተለይ በሀገራችን የማይነቀፈው የአብሮ መብላትና መጠጣት ባሕል የተለመደ በመሆኑ በሰርግ ወቅት የሚዘጋጀው ድግስ ብዙ ጊዜ ዐቅምን ያገናዘበ አይደለም።

በገጠርም ይሁን በከተማ ያለውን የጋብቻ ሁኔታ ስንመለከት የገጠሩ ኅብረተሰብ ለመኪና፣ ለመናፈሻ፣ ለአዳራሽ የሚያወጣው ወጭ ባይኖርም ከቅርብም ከሩቅም ‥የሚገኘ ወዳጅ ዘመድ ተጠርቶ ያለ የሌለ ጥሪት ወጭ ተደርጐ ድል ያለ መስተንግዶ በማዘጋጀት ለረዥም ጊዜ እድምተኞች ሰርጉ ቤት ቁጭ ብለው ሲስተናገዱ ይሰነብቱና ይመለሳሉ። በዚህ ወቅት ደጋሽ የዘር እህል እንኳን እስከ ማጣት ደርሶ በዓመቱ ችግር ውስጥ ሲወድቅ ይስተዋላል።

ከተማ ውስጥም የሚኖረው የኑሮ ውድነት እየጨመረ በመጣበት በአሁኑ ወቅት ዐቅምን ያላገናዘበ ድግስ ሲደግስ ይታያል። ለአዳራሽ ኪራይ÷ ለመኪና እንዲሁም ለመናፈሻ የሚከፈለው ወጪ የሙሽሮችን የወደፊት ሕይወት የሚያናጋ ሆኖ ይገኛል።

ብዙዎች የጋብቻ ወጭን ከዐቅም ጋር በማገናዘብ መደገስ ተገቢና ትክክለኛ እንደ ሆነ ሲናገሩ ይደመጣሉ። ዳሩ ግን እነርሱም ቢሆኑ ጉዳዩ ወደ እነርሱ ሲመጣ ከሌላው ምንም ያል ተለየ ተመሳሳይ ችግር ውስጥ ራሳቸውን ያስገባሉ። ለዚህ እንደ ምክንያት የሚቀርቡ የተለያዩ ነገሮች ቢኖሩም ጥቂቶቹን እንመለከታለን፦

1ኛ. <u>ከማን አንሳለሁ ማለት</u>፦ ሌሎች ስላደረጉት ብቻ እኔም ማድረግ አለብኝ የሚል አመለካከት ውድቀት ውስጥ ይጥላል። ሰው መሆን የሚችለውና የሚገባው ራሱን ነው። የገቢ ምንጫችንና መጠን የተለያየ እንደ መሆኑ የመደ ገስ ዐቅማችንም እንዲሁ ይለያያል እንጂ በባዶ ከማን አንሳለሁ በማለት የማይወጡት ችግር ውስጥ መግባት ራስን ለአደጋ ማጋለጥ ነው።

2ኛ. <u>የጎጂ ልማድ ችግር</u>፦ በኅብረተሰቡ ዘንድ የተለመደው የሰርግ ሂደት ከከፍተኛ ወጭ ጋር የተያያዘና ድግስ እንደ ወሳኝ የጋብቻ አካል ስለሚቆጠር ይህን ባላደርግ ሰው ምን ይለኛል? የሚለው ምክንያት ከቤተሰብ ተጽዕኖ ጋር ተጨምሮ የግድ የሰርግ ወጭ እንዲበዛ ያደርገዋል። ጥቂት የማይባሉ ወላጆች፦ «እኔ ቁሜ እየሄድኩ÷ ክንዴን ሳልንተራስ÷ ልጄን ደግሸ ሳልድር ከቀረሁማ ምኑን ወላጅ ሆንኩት» እያሉ ተቸግረው ሙሽሮችንም አስቸግረው ከገቢያቸው ጋር ያልተመጣጠነ ድግስ ይደግሳሉ።

3ኛ. <u>መንፈሳዊ ብስለት አለመኖር</u>

መንፈሳዊነት በመጠን መኖርን ያስተምራል። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያልበሰለ ሰው የሚበጅና የማይበጀውን ለመለየት ከመቸገሩም ሌላ ሥጋዊ ክብርንና ጊዜያዊ ደስታን ስለሚያስቀድም ነገን ሳይሆን ዛሬን በመምረጥ የሚጓዝ ይሆናል። ከላይ በተዘረዘሩትና በሌሎች መሰል ምክንያቶች የሰርግ ወጪ ከዐቅም በላይ ይሆንና ጋብቻን ሲሸሹት ሲፈሩት ይታያል።

ጋብቻ በእግዚአብሔር ተባርኮ የተጀመረ÷ ሰው ተረዳድቶ ተደጋግፎ መኖር እንዲችል በፈጣሪው የተለገሠው ልዩ ስጦታ ሲሆን የማንኛውም ሀገር ትውልድ የሚገኘው ከጋብቻ በሚገኝ ፍሬ ነው። ይልቁንም ለሀገር የሚጠቅም ታማኝ የሆ ነና የተቀደሰ ልጅ የሚገኘው ከተቀደሰ ትዳር ነው። ዕድሜን ጠብቆ የሚመጣ ውን የፍትወተ ሥጋ ፈተናም በጋብቻ መፍትሔ በመስጠት ከእግዚአብሔር ጋር ሳይጣሉ ከተለያዩ በሽታዎችም ተጠብቆ መኖር ይቻላል።

የጋብቻ ጥቅሙና ዓላማው ይህ ሆኖ እያለ ለሰርግ ቀን ድግስ ብቻ ትኩረት ሰጥተው ያለ የሌለ ንብረታቸውን አውጥተው ከዚህም አልፎ ከወዳጅ ዘመድና ከባንክ በመበደር በከፍተኛ ዝግጅት ተጋብተው በጋብቻቸው ማግሥት ዕዳቸውን መክፈል ሲያቅታቸውና ያወጡት ወጭ ደግሞ ማንሰራራት እንዳይችሉ ሲያደርጋቸው ትዳራቸው ሰላም አጥቶ እንደሬት መሯቸው ለፍች ሲደርሱ ይስተዋላል።

በዓለም ይኖራሉ ወይም ዓለማውያን ናቸው የሚባሉት ብቻ ሳይሆኑ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም ጭምር የዚህ ችግር ተጠቂዎች ናቸው። ግን ለምን? ክርስቲያን ተቸግሮ የሚያስቸግር ሳይሆን በዓላማ የሚኖር ነው። በዚህ እትም አርአያነት ያለው ጋብቻ ፈጽመዋል ያልናቸውን ወጣት ተጋቢዎች የጋብቻ ወጪ አስመልክተን ጥቂት ለማለት እንሞክራለን። መልካም ንባብ።

አስካለ ማርያም እና ወልደ ጊዮርጊስ ይባላሉ። ነሐሴ 16 ቀን 1996 ዓ.ም ነው ጋብቻቸውን የፈጸሙት። ወልደ ጊዮርጊስ ከዐሥር ዓመት በፊት በእንግሊዝኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ከኰተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል። አሁንም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በማታው መርሐ ግብር የ4ኛ ዓመት የኢኮኖሚክስ ተማሪ ነው። የመጀመሪያ ዲግሪውን ካገኘ በኋላ በተለያዩ ቦታዎች አገልግሏል። በአሁኑ ሰዓት በአንድ ግብረ ሠናይ ድርጅት የሕዝብ ግንኙነት ባለሞያ ኾኖ ይሠራል። አስካለ ማርያም በአንድ ት/ቤት ውስጥ በመምህርነት ትሠራለች።

*«ጋብቻችሁ ለየት ያለ ነው። እና ንተስ ልዩ እንደሆነ ታስባላችሁ?»* ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ወልደ ጊዮርጊስ ሲመልስ፦ «ጋብቻችን ምናልባት አዳራሽ ውስጥ ብዙ ሕዝብ ተጠርቶ÷ ሌላው እንደሚያደርገው መኪና ተደርድሮ÷ አደባባይ እየተዞረ አለመከና ወኑ ልዩ አድርጎት ይሆናል። ነገር ግን እንደ ማንኛውም ክርስቲያን በሥርዓተ ተክሊል በቅዱስ ቁርባን የተመሠረተ በመሆኑ ልዩ ነው አያሰኘውም።» ነበር ያለው።

*«ከሥርዓተ ተክሊሉ በኋላ ምንም ዓይነት መርሐ ግብር አልነበራችሁም?»*

አልነበረንም።

*የሰርጋችሁን ወጪ ምን አደረጋችሁበት? ምንም አላወጣንም። ለምን ?*

«በልጅነቴ እመለከተው የነበረው የሰርግ ሂደት አሁን ድረስ አይረሳኝም። ተወልጄ ያደግኩት በገጠሪቱ የሀገራችን ክፍል ሲሆን ገበሬው ምንም ሳይኖረው ለሰርግ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ነበር። ትልቅ ድግስ ተደግሶ ሰው ይጠራል። ለአራት ለአምስት ቀን ቁጭ ተብሎ እየተበላ እየተጠጣ ይሰነብታል። ከዓመት በኋላ ደጋሹ ሊወጣው የማይችለው ችግር ውስጥ ሲዘፈቅ እመለከት ነበር።

ወደ ከተማም ከመጣሁ በኋላ ተማርኩ የሚለውን ትውልድ ጨምሮ ያለ የሌለ ጥሪቱን በማውጣት÷ ከዚህም አልፎ ተበድሮም ቢሆን ለሰርግ ዝግጅት ከፍተኛ ወጪ ያወጣል። ነገር ግን ከወር ከሁለት ወር በኋላ የተበደሩትን ለመክ ፈል ሲቸገሩ ፍርድ ቤት ሲጓተቱ ትዳራቸው ሰላሙን ሲያጣ ይታያል። ለምን ይህ ይሆናል የሚል ቁጭት ነበረኝ። በመጨረሻም ከባለቤቴ ጋር ተመካክረን እንዲህ ዓይነት ነገሮችን ማስቀረት አለብን አልን። ይህን ደግሞ በኛ መጀመር አለበት ብለን ወስነን፤ አደረግነው።

አንዳንድ ሰዎች ጋብቻ መፈጸም ይፈልጋሉ። ነገር ግን ገንዘቡ የለም። ለምን? መደገስ ስለሚፈልጉ። ምክንያቱም ካልደገስኩ ኅብረተሰቡ ምን ይለኛል? በሚል ድግሱን መደገስ ካልቻሉ ደግሞ መጋባት የማይችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል። በእጮኝነት ለረዥም ጊዜ በቆዩ ቁጥር በመካከላቸው ነፋስ ይገባል። እንዲሁ ሳይጋቡ ይፋታሉ። ዕድሜ እየገፋ ይመጣል። ከዚያ በኋላም የሚፈጠረው ችግር የከፋ ይሆናል። ይህን ደግሞ መለወጥ አይቻልም ወይ? በሚል ጀም ረነዋል።

ወልደ ጊዮርጊስ የሰርግ ወጪያቸውን ለገዳማትና በገዳም ለሚኖሩ አባቶች እንዴት እንዳዋሉት ጠይቀናቸው ሲመ ልሱ፦ «እኛ የሰርግ ወጪያችንን በሙሉ አይደለም ለገዳማት ያዋልነው፤ በሥራ ዓለም ከተሠማራሁበት አንሥቶ በአራት የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ሠርቻለሁ። በእነዚህ የሥራ ቦታዎች የተለያዩ ሰዎች ጋር ተዋውቄአለሁ። ባለቤቴም እንዲሁ ቤተሰቦቻችንን ጨምሮ የምናውቃቸውን



www.eotcmk.org

ሰዎች ጠርተን ደግሰን ለመጋበዝ ብንሞክር ልናወጣ የምንችለው ገንዘብ እንግዲህ አስቡት:: ያውም በአዲስ አበባ ከተማ የአዳራሽ÷ የመኪና÷ የመስተንግዶ ሲባል ወልደን ልጆችን አድጉ ሥራ እስከሚይዝ ድረስ የማን ወጣው ዕዳ ውስጥ መግባት ግድ ይለናል:: እናም ለገዳማትና ለአባቶች ያደረግነው እንደ ዐቅማችን ነው::

በቅድሚያ ሥርዓተ ተክሊሉ እንደ ተፈጸመ ሥርዓቱን በፈጸምንበት ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ከሚኖሩት ጠያቂ ከሌላቸው ወገኖቻችን ጋር አንድ በሬ በማረድ የቁርስ ግብዣ አድርገናል:: ከሰርጋችን በኋላም በሰሜን ገዳማት ጻድቃኔ ማርያም፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ፣ ቅዱስ ላሊበላ፣ ጎንደር፦ ምንዳባ መድኃኔዓለም፣ ደብረ ሲና ማርያም፣ ዛራ ሚካኤል፣ ጣና ገዳማት፣ ደብረ ሊባኖስ በመዘዋወር ለገዳማቱ ጧፍ፣ ዕጣን፣ ዘቢብ የሰጠን ሲሆን ለአባቶች ደግሞ አቡ ጀዲ አስቆርጠን በመያዝ አድለናል:: እንዲሁም ጋዝ በጀሪካን እንደ አስፈላጊነቱ ደግሞ በጥሬ ገንዘብ ሰጥተናል» በማለት አብራርቶልናል::

በድግሱና በተለያዩ ዝግጅቶች ልታወጡ የነበረውን ወጪ ለገዳማቱና ለአባቶች ካደረጋችሁት ወጪ ከመቆጠብ አንጻር ልዩነቱ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ ወልደ ጊዮርጊስ ሲመልስ «እንዴ ቅድም ገልጫለሁ እኮ፤ እኛ አልተበደርንም÷ አልተቸገርንም÷ ለኑሮአችን የሚያስፈልገንን ለራሳችን እንደ ዐቅማችን አሟልተናል:: ይህችን ትንሽ ነገር ማድረጋችን ደግሞ በጊዜያችን ካለው የሰርግ ወጪ ጋር በፍጹም አይነጻጸርም» ነበር ያለው::

ጋብቻችሁን በዚህ ሁኔታ ስትፈጽሙ አንተ በወሰንከው ሁኔታ ባለቤትህ ለመቀበል አልተቸገረችም ወይ? የሚል ጥያቄ ጠይቀነው ሲመልስ፦

«በነገራችን ላይ በአብዛኛው ሴቶች ላይ ጐልቶ ይታይ እንጂ እንዲህ ዓይነት ነገር በወንዶች ላይም አለ:: ሙቼ ነው ሳልሞት እንዲህ ሁኜ የማገባው ብለው የሚናገሩ ወንዶች አሉ:: ዳንኪራውን÷ ሽብ ረቡን የሚፈልጉ ወንዶችም ሴቶችም አሉ:: ባለቤቴን በተ መለከተ ቅድም ገልጨዋለሁ:: ተመካ ክረን ነው ሁሉንም ያደረግነው:: አሳቡን በደስታ ነው የተቀበለችው:: በርግጥ በእኔም በእርሷም ወገን ቤተሰቦቻችንን ጨምሮ ወዳጅ ጓደኞቻችን እጅግ ከፍተኛ ጫና ያደርጉብን ነበር:: አንተን የሚያክል ሰው... እርሷን የመሰለች ልጅ... እንዴት እንዲህ ይሆናል? ይሉን ነበር::» በማለት ከባለቤቱ ጋር በአሳብ አንድ ሁነው የጋብቻቸውን መርሐ ግብር እንዳከናወኑ አስረድቷል::

«ይህ የኢትዮጵያውያን ባሕል ነው:: ዘመድ ወዳጅ ተሰባስቦ የሚደሰትበት ነውና ባሕሉ ሊጠበቅ ይገባዋል:: በተቻለ መጠን ይህን ማጥፋት አይገባም» የሚሉ አሉና ይህን እንዴት ትመለከቱ ታላችሁ? በማለት ላቀረብነው ጥያቄ መልስ ሲሰጥ እጅግ በመገረም እንዲህ ነበር ያለው:: «ይህ እንደ ሰው አመለካከት ይወሰናል:: ዜጐች በረኀብ በሚያልቁባት ሀገር ውስጥ እያለን ከዐቅም በላይ ወጪ እያወጡ ድግስ መደገስ አይዋጥልኝም:: በሀገራችን ከሦስት ሚሊዮን በላይ ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡ ሕፃናት እያሉ÷ ጧሪ የሌላቸው አረጋውያን ያለ ደጋፊ እየተንገላቱ ለአንድ ቀን ደስታ ተብሎ /ደስታ ከተባለ/ የማይወጡት ዕዳ ውስጥ መግባት ለኅሊናም ይከብዳል:: ይህ ለኔ የአመለካከት ጉድለት ነው::

እያልኩ ያለሁት የሰርግ ሥነ ሥርዓት ይቅር÷ ባሕሉ አይጠቅምም አይደ ለም:: አብሮ መብላት መጠጣት የኢትዮጵያውያን ባሕላችን ነው:: ኾኖም አይብዛ፤ ከማን አንሼ፤ በማለት ኑሯቸውን እያናጉ ዘላቂነት ያለው ሥራ እንሥራበት ነው:: ሰው ተበድሮ÷ ሥራ ሠርቶ÷ አትርፎ ብድሩን መልሶ ትርፉን ይጠቀምበት ይሆናል እንጂ በገዛ እጁ የሰው ገንዘብ አምጥቶ እንዴት በችግር ይወድቃል? መተው እየተቻለ::» ብሏል::

ከጋብቻ በኋላ ትዳርን እንዴት እንዳገኙት ሲያስረዳ፦ «ቅዱስ ጳውሎስ ቢቻል እንደ እኔ ብትሆኑ እወዳለሁ እንዳለው መኖር ቢቻል ጥሩ ነው:: ነገር ግን እኔ እንደማልችል ሳውቀው ነው ወደዚህ ሕይወት የገባሁት:: ብቸኝነት ከባድ ነው፤ በጣም ብዙ ፈተናዎች ይበዙበታል:: ከዐይን ጀምሮ እስከ ተግባር ድረስ በተለይ ከጾታ ጋር በተገናኘ ፈተናው ብዙ ነው:: ከዚህ ለመጠበቅ ትዳር ውስጥ ገባሁ:: ልምድ ላካፍል የምችልበት ጊዜ ባይኖረኝም በዚህ አጭር ጊዜ ያለው ሁኔታ ጥሩ ነው ማለት እችላለሁ:: ወደ ፊትም መልካም ኑሮ እንመራለን ብለን እናስባለን:: መጀመር ቀላል ነው፤ ፍጻሜው ነው ዋናው:: ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ነው እላለሁ::» በማለት ገልጾልናል:: እኛም እግዚአብሔር ጋብቻቸውን ይባርክላችሁ እንላለን:: ረድኤተ እግዚአብሔር አይለይን::

*ከአዘጋጁ* ፦ ውድ አንባብያን የጽሑፉ አቅራቢ በተነሣው ርእሰ ጉዳይ ለመነሻ የሚሆን ዝግጅት አቅርበውልናል:: በሰርጋችሁ ያለ አግባብ ወጪ አውጥታችሁ ከሠርግ ማግስት ጀምሮ የተጸጸታችሁ፣ የሰርግ ወጪያችሁን በአግባቡ አድርጋችሁ ለኑሮ የሚያስፈልጋችሁን በማሟላት ሰላማዊ ኑሮ የምትገፉ፣ በሰርግ ወጪያችሁ ሥራ ለሌላቸው ቋሚ መተዳደሪያ የሚሆን የሥራ እድል የፈጠራችሁና ጧሪ ለሌላቸው አረጋውያንና አሳዳጊ ለሌላ ቸው ሕፃናትን የረዳችሁ...

በጠቅላላው በሰርግ ወጭ ዙሪያ ያላችሁን ትምህርታዊ ተሞክሮና ገጠመኛ ጻፉልን:: እንወያይበት::

# አቡነ ዘዮሐንስ ...

/ከገጽ ፳፪ የዞረ/

/ከገጽ ፳፪ የዞረ/

እንዳትገባ አወገዘ:: እስከ ዛሬ ድረስም እንደ ቃሉ ሆነ:: ያችንም ደሴት ወረታዋ እንዳ ይጠፋ በዓሣ አጥማጅ በገብርኤል ሚስት በመስቀል ክብራ ስም ጠራት:: ከዚህችም ቀን ጀምሮ እስከዚህ ቀን ድረስ በክብራ ስም ተጠራች:: ከዚህ በኋላ አባታችን ዘዮሐንስ ለአንዲት ቀንም የዚያችን ደሴት ርዝመቷን፣ ወርዷን፣ ቁመቷን ያዩ ዘንድ ሲመላ ለስ ከዚያች ተራራ በስተ ደቡብ ብዙዎችን ሰዎች አይቶ፦ «ከዚህ ምን ታደርጋላችሁ?» አላቸው:: «ለአምላካችን ለዘንዶው ምግብን እንሰጠው ዘንድ ጌቶቻችን አዘውናልና የዘንዶውን መምጣት እንጠብቃለን» አሉት:: የሀገሩ ሰዎች ግን በየተራቸው ይህን ያደርጉ ነበር:: ጃንቹሐይ የተባለ ጌታቸውም እንዳዘዛቸው አንድ ከብት፣ አንድ ማድጋ ወተትና አንድ በግ በየቀኑ ይሰጡት ነበር:: እንዲህም ሲባባሉ ያዘንዶ ምድርን እያናወጣት መጣ:: እርሱ ግን በስመ ሥላሴ በትእምርተ መስቀል ሲያማትብ መርዙ ተሻረ:: እነዚያ የመጡ ሰዎችም «አባታችን ሆይ! በከንቱ አታጥፋን» አሉት:: «በፈጣሪዬ ስም እገድለዋለሁ! ጊዮርጊስንም ከድራጎን አፍ ያዳን ከው አንተ በተኩላና በዘንዶ ላይ ትቀመጣለህና÷ አንበሳንና ዘንዶንም ትገዛለህና አድነኝ!» አለ:: ይህንም ብሎ ዳግመኛ ባረከ:: ያን ጊዜም ዘንዶው ሞተ:: ዘንዶውንም በለኩት ጊዜም ርዝመቱ 60 ክንድ÷ ወርዱ ስምንት ክንድ ሆነ::


እነዚያም በታንኳቸው ሂደው ስለሚያመልኩት ስለዚያ ዘንዶ ሞት ለሕዝቡ ሁሉ ነገሯቸው:: ከዚህም በኋላ ዘዮሐንስ በዚያ ወራት ወደ ዘጌ ገዳም ሂዶ ከዚያ ሀገር ሰዎች ጋር ተገናኘ፤ በመምጣቱም ሁሉም በጠቅላላ ደስ ብሏቸው መንፈሳዊ አባታቸው አደረጉት:: ከዚህ በኋላ የአገውሹም ጃንቹ ሐይ የዘንዶውን ሞት ሰማ:: በየበዓሉ ሁልጊዜ እየመጣ ለዘንዶም ይሰግድ ነበርና:: ጭፍሮቹን «ዘንዶውን የገደለውን ያንን መነኩሴ ይዛችሁ ወደኔ አምጡት!» አላቸው:: አባታ ችን ዘዮሐንስም ስለ ዘንዶው ሞት ጃንቹሐይ እንደ ተቆጣ በሰማ ጊዜ ከዘጌ ገዳም ወጣ:: ጭፍ ሮችንም ሲፈልጉት አገኛቸው:: አባታችን ዘዮሐንስ ግን ሳይደበቅ ይህን ሁሉ ዐውቆ ሊቀበላቸው ከመንደር ወጣ:: ከዚህ በኋላ ይዘው በችኮላ ወደ ጌታቸው ወሰዱት::

/ወደ ገጽ ፳፮ ዞሯል/





www.eotcmk.org



*ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የጀመረው ሰፊ ሥራ አካል ሆኖ ከዚህ እትም ጀምሮ የተከፈተ ነው:: ማኅበራችን ይህንን ሥራ ሲጀምር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ባገኘው መልካም ፈቃድና መመሪያ መሠረት ሲሆን፣ አጠቃላይ የሥራ ሂደቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ክትትል እንዲደረግበት ሆኖ ነው::*

# የጠባይ ለውጥ እንዴት?

*መ/ር ኃ/ ማርያም ላቀው እና ዲ/ን ፋሲል አስረስ*

በዓለም ላይ ከ35 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር አብሮ የሚኖር መሆኑን የተለያዩ ዘገባዎች ሲያስረዱ በተለይም ከሰሀራ በታች ያሉ ሀገሮች ከፍተኛውን ቁጥር አስመዝግበዋል:: ሀገራችን ኢትዮጵያም በቫይረሱ ከተጎዱት ሀገሮች ግንባር ቀደም መሆኗ ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል::

ዛሬ በየትኛውም ቦታ ብንሆን ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስማት የግድ ሁኗል:: ጋዜጦችና መጽሔቶች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በተመለከተ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ይጽፋሉ፤ ሬድዮና ቴሌቪዥንም በልዩ ልዩ ዘዴዎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሲጥሩ ይታያሉ::

በሀገራችን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከሰቱ ከታወቀ ሁለት ዐሠርት ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ከማስፈራራት ጀምሮ እስከ ማቆላመጥ ድረስ በተለያየ መንገድ ኅብረተሰቡ የጠባይ ለውጥ እንዲያመጣ ሙከራ ተደርጓል::

እንደ ዋነኛ የቫይረሱ መተላለፊያ መንገድ ተደርጎ ከሚታወቀው ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመታቀብ በቫይረሱ ከመያዝ ማምለጥ እንደ ሚቻል ተነግሯል፤ ተዘክሯል:: የሚፈለገውን ያህል የጠባይ ለውጥ ግን የለም:: እንዲያውም በተቃራኒው ይመስላል ሁሉም ነገር ብሶበታል:: ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮግራም በ2000 /UNAIDS 2000/ ባቀረበው ሪፖርት በ1993 እ.ኤ.አ የቫይረሱ ሥርጭት ከ15-49 ዓመት ባለው ዕድሜ ክልል 3.2% የነበረ ሲሆን በ1999 እ.ኤ.አ መጨረሻ ወደ 10.63% ከፍ ብሏል::

የሞትና የሕይወት የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ የሆነውን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጉዳይ ትኩረት መንፈግ አደገኛነቱ አጠያያቂ አይደለም:: ዘር፣ ቀለም፣ ሃይማኖትና ጐሳ ባለመለየት የዘመተብንን ጠላት በዝምታ ማሸነፍ አይቻልም:: ይህ የሚታወቅ ጉዳይ ቢሆንም ኅብረተሰቡ ግን የሚፈለገውን የጠባይ ለውጥ ማምጣት አልቻለም:: ለምን?

የጠባይ ለውጥ እንዳይመጣ እንደ ምክንያት የሚቆጠሩ የተለያዩ ሁኔታዎች ሊኖሩ ቢችሉም ጥቂቶቹን እንመለከታለን::

## 1ኛ. የአመለካከት ችግር

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ሥርጭቱ እየከፋና እየተባባሰ ቢመጣም በራሳቸው ደርሶ ካላዩ በስተቀር ለማመን የሚቸገሩ ሰዎች አሉ:: ትውልድ ለማዳን ራሳቸውን አጋልጠው በአንድ በኩል የቫይረሱ ተጠቂዎች በመሆናቸው በተለያዩ በሽታዎች እየተጠቁ በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ፊት እየገረፋቸው የኤች.አይ.ቪን አስከፊነት በማስተማር አምራች ዜጋ እንዳይጠፋ ለማድረግ ደፋ ቀና የሚሉ ወገኖች ሲኖሩ ሓላፊነታቸውን የማይወጡት የበጐ ነገር ተቃራኒ የሆኑት ደግሞ በአመለካከት መዛባት ጠቃሚ የሆነው ሁሉ አይዋጥላቸውም::

በቫይረሱ ተይዘው ራሳቸውን አውቀው የጠባይ ለውጥ ያላመጡትም «በኔ ይብቃ» በማለት ፈንታ በበቀል ተነሳስተው «እኔ ብቻ ለምን? ከሌላው የተለየ ኃጢአት ሠርቼ አይደለም የተያዝኩት» በሚል አጉል አመለካከት ሥርጭቱ እንዲባባስና እንዲጨምር ያደርጋሉ::

## 2. ተስፋ መቁረጥ

ጠቢባን የተቸገሩበትና መፍትሔ ያጡለት ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ብዙዎችን በቀቢጸ ተስፋ እንዲኖሩ እያደረገ ነው:: ከዚህም አንጻር የቀደመ ሕይወታቸውን በማሰብ ይኑርባቸው አይኑርባቸው እንኳን ሳያረጋግጡ ተስፋ በመቁረጥ ወደ መከላከል ለማምራት የሚቸገሩ አያሌ ናቸው::

የሕክምና ባለሞያዎች ቫይረሱን ከሚያባብሱ ድርጊቶች ተቆጥቦ ከቫይረሱ ጋር ለረዥም ጊዜ አብሮ መኖር እንደሚቻልና እንደማንኛ ውም ሰው መሥራት እንደሚቻል ቢናገሩም በተስፋ መቁረጥ ተሸንፈው ከመሞታቸው በፊት የሚሞቱ ሕይወታቸውን ጥንቃቄ በጐደለው መንገድ የሚመሩ አያሌ ናቸው::

ተስፋ የሌለው ሰው ምንጊዜም ሕይወቱ በጨለማ ውስጥ ነው:: በጨለማ የሚኖር ደግሞ እንዴትና ወዴት እንደሚሔድ አያውቅም:: ምንም ቢነገረው ለመቀበል የተዘጋጀ ልቡና ስለማይኖረው የጠባይ ለውጥ ለማምጣት ይቸገራል::

## 3. ችግሩን መፍታት የሚወሰዱት መፍትሔዎች

አንዳንድ ጊዜ ለችግሩ መፍትሔ ይሆናሉ ተብሎ የሚነገሩ ቃላት በተቃራኒው ራሳቸው ችግር የሚሆኑበትና የሚያባብሱ ሆነው ይገኛሉ:: ኅብረተሰቡ የሚሰማውንና የሚያየውን በሕይወቱ ውስጥ ስለሚያስገባው በተለይ በመገናኛ ብዙኀን የሚሰጡ ትምህርቶች ከፍተኛ ጥንቃቄን የተሞሉ መሆን አለባቸው::

## 4. *የባሕል ተጽዕኖ*

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከል የጠባይ ለውጥ ለማምጣት አካባቢያዊ ተጽዕኖ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል:: ጠባይ በክፋም ሆነ በደግ ሊለወጥ ይችላል:: ለምሳሌ የአንድ አገር ባህል በማኅበረሰቡ ያሉትን የቋንቋ አጠቃቀምን፣ የልብስ አለባበስን፣ የምግብ አመጋገብንና ሌሎችንም ቁሳዊና መንፈሳዊ ነገሮች ሊወስን ይችላል:: «ገመና መሸፈን» ከኢትዮጵያውን የባህል እሴቶች አንዱ ነው:: ይህ ገመና ሸፋኝነት የቀደመ አባቶች ተጉዘውበት ተጠቅመውበታል:: አባቶቻችን የአንዱን ገበና ሸፍነው ያለፉበት መንገድ ሙሉ በሙሉ ዛሬ ላይ ላይሠራ ይችላል:: ምክንያቱም አበው ባለፉበት ዘመን የተከተሉት አሠራር አሁን ካለንበት ሁኔታ አንፃር ሲቃኝ ብዙ መንገድ አያስጉዘንም:: ዛሬ ሸፋፍነን የደበቅነው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጉዳይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰብን ይገኛል::




www.eotcmk.org

## 5. የምርጫ አለመስተካከል

ቅዱስ ጳውሎስ «ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን ዓመል ያጠፋል» /1ኛቆሮ. 15÷33::/ ይላል:: ጠባያችን ሊከፋም ሊለማም የሚችለው በዕለታዊ እንቅስቃሴያችን ውስጥ ነው:: ከምን የዋለ ምን ተምሮ ይመጣል እንዲሉ ለወዳጅነት የምንመርጠው ባልንጀራ፣ ለጊዜ ማሳለፊያ የምንመርጠው የመዝናኛ ሥፍራ አንዳንድ ጊዜ በጠባያችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል:: ለጠባይ ለውጥ መከሰቻ «ምርጫ» አንዱ ነው:: ጠባያችን ሊበላሽ የሚችለው ምርጫችን ሲበላሽ ነው:: አንድ ሰው የምርጫ መበላሸት ከገጠመው ሕይወቱ ሊበላሽ ይችላል:: ስለዚህ በሕይወት ለመኖር እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስደስት ሥራ ሠርቶ ስምን ከመቃብር በላይ ለማዋል ከእኔ ጋር ሊጓዝ የሚችለው ማነው? እኔስ ማነኝ? ጉዞዬስ ወዴት ነው? ብሎ ራስን አለመጠየቅም ተጠቃሽ ችግር ነው::

## 6. የአስተሳሰብ ችግር

ከምንም በላይ ዛሬ ሊለወጥ የሚገባው አስተሳሰባችን ነው:: የአጠስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት እስካልተቻለ ድረስ የጠባይ ለውጥ ማምጣት አይቻልም:: ለቫይረሱ የምንሰጠውን ግምት ከፍና ዝቅ የሚያደርገው አስተሳሰባችን ነው:: ልቅ ከሆነ ከፋካቤ ሥጋ በኋላ ለሥጋችን የሚሰማንን ፍስሓና ነፍሳችን የምትከፍንበው የጸጸት ካባ ማነጻጸር አለመቻል በእጅጉ ችግሩን ሊያባብሰው ችሏል:: ሥጋችን የሚሰማትን ፍስሐ ነፍሳችን ላታገኘው ትችላለች:: ስለዚህ ቫይረሱ አሳሳቢ የሚሆነው ለሥጋ ብቻ ሳይሆን ለነፍስም መሆኑን በውል አለመረዳት ነው:: ለዚህም ተጠቃሹ ከሥርዓት የወጣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው::

ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለኤች.አይ.ቪ መተላለፍ ዋነኛ መንገድ መሆኑን ተናግሮ እንዴትና ለምን መታቀብ እንደሚገባ አጠንክሮ ማስረዳት ሲቻል እንዲሁም የመተላለፊያ መንገዶቹን በግልጽና በማያሻማ መንገድ ሊነገር ሲገባ ስለ ቫይረሱ አስከፊነት ብቻ ከተነገረ ለውጥ ሊመጣ አይቻልም:: ስለሆነም የቫይረሱን ሥርጭት ለመቀነስም ሆነ የጠባይ ለውጥ ለማምጣት የሚ ወሰዱ ርምጃዎች ጥበብ የተሞሉ ሊሆኑ ይገባል::

## 7. የቤተሰብ አለመወያየት

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገራዊ ጉዳይ መሆኑን ከገንዘቤ በማስገባትና በሽታውን በመከላከል ረገድ በቤታቸው ውይይት በማድረግ ለቤተሰቦቻቸው ጥሩ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ወላጆች አሉ:: ቫይረሱን ለመከላከል ሊደረግ የሚገባውን ክትትል በአካባቢ መረዳትን ማስረዳት የጠባይ ለውጥ ለማምጣት የራሱ የሆነ ሚና ይኖረዋል:: ነገር ግን ይህ ባሕል በብዙዎች ዘንድ ገና አልዳበረም:: የፆታ ትምህርት፣ ኤች.አይ.ቪን አንስቶ መወያየት በአንዳንድ ቤተሰቦች እንደ ነውር ይቆጠራል:: ቤተሰብን አሰባስቦ ማወያየት እንደነውር በሚቆጠርበት ሁኔታ የተፈለገውን ዓይነተኛ ለውጥ ለማምጣት ያዳግታል::

## 8. መድልዎና መገለል

ለበሽታው ተጋላጭ የሆኑትን ወገኖች ማግለል የተፈለገው የጠባይ ለውጥ እንዳይመጣ እንቅፋት ነው:: ብዙዎች ለኤች.አይ.ቪ ተጠቂ የሆኑትን ባገለሉ ቁጥር በሽታውን በተዘዋዋሪ እያስፋፉት መሆኑን በውል አልተገነዘቡትም:: አንዳንድ ሕመምተኞች መገለል ሲደርስባቸው ወዳልተፈለገ ርምጃ ሊያመሩ ይችላሉ:: መገለልና መድልዎ በቀላን ይወልዳል:: በዚህ የተነሳ ብዙዎች ራሳቸውን ገልጸው በማስተማር ሓላፊነታቸውን እንዳይወጡ መገለልና መድልዎ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል::

## 9. ከቫይረሱ ጋር አብረው የሚኖሩ ሰዎችን መብት የሚያስጠብቅ አካል አለመኖር

በተለያዩ አካባቢዎች ከተከራዩት ቤት እንዲወጡ የሚደረጉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጠቂዎች በርካታ ናቸው:: ለምሳሌ አዋሳ ከተማ ውስጥ በአካራዮቿ የተፈጸመባትን በደል ለሕዝብ ይፋ ያደረገችውን አንዲት ሕመምተኛ መመልከት ይቻላል:: ይህ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ የተፈለገውን የጠባይ ለውጥ ለማምጣት አዳጋች ይሆናል:: ለማንኛው ሰብአዊ ዜጋ ሊደረግ የሚገባውን ክብካቤ የኤች.አይ.ቪ ሕመምተኞች አለማግኘታቸው የቫይረሱ ሥርጭት እንዳይገታ አሉታዊ ተፅዕኖ ለማሳደር ችሏል:: የኤች.አይ.ቪ ሕመምተኛ ቤት ስለተከራዩ በአንድ ግቢ ውስጥ አብረው መኖራቸው፣ በአንድ መጸዳጃ መጠቀማቸው በሽታውን እንደ ማያስፋፋ በሕክምና ባለሞያዎች ዘወትር እየተነገረ ይህን ነገ ጥለነው የምንሄደውን ቤት ለሕመምተኛ አላከራይም፣ በግቢያችን መኖር የለባቸውም በማለት የምን ከተለው ኢ-ሥነ ምግባራዊ ውሳኔ በተዘዋዋሪ ለበሽታው መንገድ እየጠረግን መሆኑን አለማጤን አንዱ ችግር ነው::

ውድ አንባብያን፤ በሚቀጥለው እትም ኅብረተሰቡ የጠባይ ለውጥ እንዲያመጣ ምን ይደረግ በሚለው ነጥብ ላይ እንወያያለን:: የመጽሔታችን አንባቢዎች በዚሁ ቫይረስና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ አስተማሪ የሆኑ ገጠመኞች፣ ታሪኮችና ልምዶች ያሏችሁ ብትልኩልን እንደ ምናስተናግድ እንገልጻለን::

# አቡነ ዘዮሐንስ ...

/ከገጽ ፳፬ የዞረ/

ወደ እርሱ በደረሰም ጊዜ ጃንቹሐይ አባታችን ዘዮሐንስን፡ - «እኔ የማመልከውን ዘንዶ ለምን ገደልከው? ትገድል ዘንድስ ማን ግድ አለህ?» አለው:: አባታችን ዘዮሐንስም፡ - «ከጌታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር አምላክ የለም» አለው:: ጃንቹሐይም በብረት ዘንግ ይመቱት ዘንድ በዚያም ይሞት ዘንድ አዘዘ:: ከዚህ በኋላ ደሙ በምድር ላይ እስኪፈስ ድረስ በጠንካራ ሰንሰለት ታስሮም ሰነበተ:: ከዚህ በኋላ አባታችን እንደ ታሰረ ንጉሥ ዐምደ ጽዮን በሰማ ጊዜ፡- «ያን መነኩሴ ካልፈታኸው በእኔና በአንተ መካከል ፍቅር አንድነት አይደረግም /አይሆንም/» ብሎ ብዙ ጭፍሮችን ሰደደ:: እንቢ ባለም ጊዜያን ከሐዲ ይገድሉት ዘንድ አዘዘ:: ከሐዲውንም ገደሉት:: አባታችን ዘዮሐንስን ግን ከእስራቱ ፈቱት:: ንጉሥ ዐምደ ጽዮንም ከአባታችን ዘዮሐንስ ዘንድ ለመባረክ በታላቅ ደስታ ወደ እርሱ መጣ::: ንጉሥ ዐምደ ጽዮንም ተባረከ:: ንጉሡም ዘዮሐንስ «የምሰጥህን ለምን» አለው:: አባታችን ዘዮሐንስም «ወደ ቀድሞው መኖሪያዬ /ቦታዬ/ መልሰኝ» አለው:: ንጉሡም «ፈቅጄልሃለሁ» አለው:: ከአዳማ ምድር ጀምሮ እስከ ባሕር ድረስና እስከ ዐባይ ወንዝ ድንበር እስከ ቱምሐና እስከ አገው ድረስ ብዙ ጉልትን ሰጠው:: ከዚህ በኋላ ወደ ክብራን ደሴት ተመልሶ በቅዱስ ገብርኤል ስም ቤተ ክርስቲያንን ሠራ::

አባታችን ሐምሌ ስምንት ቀን ለዓርብ አጥቢያ ሲጸልይና በግንባሩ ወደ ምድር ሲሰግድ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል ተከትለውት መጥቶ፡- «ወዳጄ አባ ዘዮሐንስ ሆይ! ከድካም ወደ ዕረፍት÷ ከበሽታ ወደ ሕይወት÷ ከዚህ ዓለም ዐይን ወደ አላየውና ጆሮ ወዳልሰማው ተድላ ደስታ ወደ አለበት ገነት አሳርፍህ ዘንድ ወደ አንተ መጣሁ::» አለው:: ይህንም ብሎ ስሙን ለሚጠራና መታሰቢያውን ለሚያደርግ ከእርሱ በረከት እንደማይጠፋ ቃል ኪዳንን ሰጠው::

ከዚህ በኋላም በሦስተኛው ቀን ልጆቹን አንድ ላይ ሰብስቦ ስለ መንፈሳዊ ጥንካሬያቸው ልዩ ልዩ ምክሮችን ከመከራቸው በኋላ ሐምሌ 24 ቀን ዐረፈ:: የአባታችን ቅዱስ ዘዮሐንስ ልመናው ይደረግልን፤ በረከቱ ይደርብን:: አሜን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር





www.eotcmk.org

# «እነዚህ ድርጅቶች ሕዝቡን ለመሳብ ልዩ ልዩ ማታለያዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ይጠቀማሉ:: እኛ ግን ምንም ሳንጠቀም ምእመናኑ በራሳቸው ጊዜ ወደ እኛ ይመጣሉ:: መንፈስ እግዚአብሔር ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ይጠራቸዋል::»

*/ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በትሪኒዳድና ካሪቢያን ሀገራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ/*

ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸውን ሓላፊነት ይዘው፣ ተወልደው ያደጉባትን፣ ተምረው ለመዓርግ የበቁባትን ሀገራቸውን ለቀው ወደ ባዕድ ሀገር ከሄዱ 32ኛ ዓመታቸውን ይዘዋል:: በ1965 ዓ.ም በወቅቱ በነበሩት አባቶች በትሪኒዳድና ካሪቢያን ሀገራት ተጉዘው እንዲያገለግሉ ሲታዘዙ ይዘውት የሄዱት ለዓመታት ከካበተ የቤተ ክርስቲያን ዕውቀታቸው ጋር ከአባቶቻቸው የተቀበሉትን መዓርገ ቅስና ነበር:: ከሃያ ዓመታት ሰፊ አገልግሎት በኋላ ግን በ1985 ዓ.ም «ይገባሃል» ተብለው መዓርገ ጵጵስናን ተቀብለዋል:: ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በትሪኒዳድና ካሪቢያን ሀገራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ::

በቀድሞው ወሎ ጠቅላይ ግዛት ዋግ አውራጃ «ዘለቃ ጊዮርጊስ» በተባለው ቦታ የተወለዱት ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ በአካባቢያቸው ፊደል ከቆጠሩ በኋላ ወደ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት ተሻግረው «ቀረጻ ማርያም» ተብላ በምትታወቀው ገዳም ትምህርታቸውን ቀጠሉ:: ለዓመታት እስከ መጻሕፍት ትርጓሜ ያለውን ትምህርት በሚገባ ከተማሩ በኋላ ንጽሕ ጠብቀው በድንግልና ጸንተው ሊኖሩ ወስነው በ1951 ዓ.ም በወቅቱ የገዳሙ አበ ምኔት ከነበሩት መ/ር ኃይለ ማርያም ወረታ አርዑተ ምንኩስናን ተቀበሉ:: በገዳሙ ለአራት ዓመታት ከቆዩ በኋላ በእግዚአብሔር አነሣሽነት በወቅቱ በማኅበሯ ድምቀት፤ በውስጧ በሚሰጠው ትምህርት ስፋትና ጥራት ስመ ጥር ወደ ነበረችው መናገሻ ማርያም መጡ:: በዚያም ከ1956–1960 ዓ.ም በትምህርትና በአገልግሎት ቆዩ:: በ1960 ዓ.ም ወደ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መጥተው እስከ 1965 ዓ.ም በክህነት አገልግሎትና በትምህርት ቆዩ:: በአለፈው ዘመናቸው ያደረጉትን የመማር ጥረትና የአገልግሎት ትጋት የተመለከተው የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በ1965 ዓ.ም ለበለጠው አገልግሎት አሁን 32ኛ ዓመታቸውን ወደያዙበት ቦታ ላካቸው:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሕዝቡን ቋንቋና ባሕል ቋንቋቸውና ባሕላቸው አድርገው፤ ሕዝቡም አባታቸው፣ እርሳቸውም ሕዝቡን ልጃቸው አድርገው በመኖር ላይ ይገኛሉ::

ብፁዕነታቸው ለ22ኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለቀናት በቆዩበት ጊዜ የዝግጅት ክፍላችን አነጋግሯቸው ነበር::

**ሐመር:–** *በትሪኒዳድና ካሪቢያን ሀገራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአመሠራረት ታሪክ ምን ይመስላል?*

**ብፁዕነታቸው:–** ቤተ ክርስቲያናችን በዚያ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመችው የዛሬ 52 ዓመት ነው:: የአካባቢው ተወላጆች የእኛን ቤተ ክርስቲያን እንደ ማንነታቸው መገለጫ፤ እንደ ድኅነት መንገዳቸውም በመቁጠራቸው «ቤተ ክርስቲያን ትቋቋምልን» በማለት በወቅቱ ለነበሩት አባቶችና ንጉሠ ነገሥት ጥያቄ አቀረቡ:: ጥያቄያቸው ተቀባይነት አገኝና በኋላ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ተብለው በአካባቢው ረዘም ላለ ጊዜ ያገለገሉት አባ ገብረ ኢየሱስ መሸሻና በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት አቶ አበራ ጀንበሬ /በአስተርጓሚነት/ ወደ ቦታው ተላኩ:: እነርሱም የተሰጣቸውን ተልእኮ በሚገባ በመወጣት በትሪኒዳድ ጉያና በመድኃኔ ዓለም ስም የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን አቋቋሙ:: እንግዲህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት እ.አ.አ በ1952 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ተቋቁማ ዛሬ ባለችበት ደረጃ ላይ ደርሳለች::

**ሐመር:–** *ስለሆኑ በትሪኒዳድና ካሪቢያን አገሮች ቤተ ክርስቲያናችን ዛሬ በምን ደረጃ ላይ ትገኛለች?*

**ብፁዕነታቸው:–** ምንም እንኳ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሰናል ብለን ባንመካም ዛሬ በደኅና ሁኔታ ላይ ደርሰናል ብለን መናገር የምንችል ይመስለኛል:: በአሁኑ ወቅት በአካባቢው የተቋቋሙ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ዐሥራ ስድስት ደርሷል:: በምእመናንም ቁጥር በኩል መልካም ዕድገት አለ:: ምናልባት ከእኛ ዐቅም ማነስ የተነሣ ነው እንጂ ዛሬም የአካባቢው ሕዝብ «ተጨማሪ አብያተ ክርስቲያናትን አቋቁሙልን» እያለ ነው::

**ሐመር:–** *ምናልባት ያሉት የምእመናን ብዛት ይታወቅ ይሆን?*

**ብፁዕነታቸው:–** ስማቸው በመዝገብ ያሉ ምእመናን ከ30,000 በላይ ናቸው:: ነገር ግን አሁንም ቤተ ክርስቲያናችን በመለፈግ በርካታ ምእመናን እየመጡልን ነው:: የአገልጋይ እጥረትና የቦታ መራራቅ ችግሮች ስላሉብን በሦስት ወር አንድ ጊዜ ቢያንስ 50 አፍሪካ አሜሪካውያንን እናጠምቃለን:: በዚያ ሀገር ይኸን ያህል ምእመን



መያዝ በጣም ትልቅ ነገር ነው:: በእውነቱ የቤተ ክርስቲያናችንን ማኅደረ መለኮት መሆን የሚያሳይ ነው:: በአካባቢው የሌለ የእምነት ድርጅት የለም ለማለት ይቻላል:: ለምሳሌ 1.3 ሚልዮን ሕዝብ በሚኖርበት ትሪኒዳድ ከ120 በላይ የእምነት ድርጅቶች አሉ:: እነዚህ ድርጅቶች ሕዝቡን ለመሳብ ልዩ ልዩ ማታለያዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ይጠቀማሉ:: እኛ ግን ማታለያም ሆነ ቴክኖሎጂ ሳንጠቀም ምእመናኑ በራሳቸው ጊዜ ወደ እኛ ይመጣሉ:: መንፈስ እግዚአብሔር ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ይጠራቸዋል:: በዚህም እግዚአብሔርን እናመሰግናለን::

**ሐመር:–** *እነዚህን ምእመናን የምታቀፉበትና የምታገለግሉበት አስተዳደራዊ መዋቅር ምን ይመስላል?*

**ብፁዕነታቸው:–** በተቻለ መጠን የቤተ ክርስቲያናችንን አገልግሎት የሚያፋጥን አስተዳደራዊ መዋቅር ዘርግተናል:: እያንዳንዱ ደብር የራሱ የሆነ አለቃ አለው:: አስተዳዳሪው በአጥቢያው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አቋቁሞ ምእመናኑን ያስተዳድራል:: በአንድ ክፍለ ሀገር /ለምሳሌ:– በትሪኒዳድ/ ለሚኖሩ አብያተ ክርስቲያናት ከአለቆቹ በላይ ሆኖ አመራር የሚሰጥ አንድ አስተዳዳሪ አለ:: ከየክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪዎች በላይ ደግሞ ሊቀ ጳጳሱ አለ:: በዚህ ዓይነት ነው የምናስተዳድረው:: በነገራችን ላይ በየአስተዳደር መዋቅሩ ያሉ ሓላፊዎች በሙሉ /ከሊቀ ጳጳሱ በስተቀር/ የዚያው ሀገር ተወላጆች ናቸው::

**ሐመር:–** *የሚሰጠውን መንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ በሚገባቸው ቋንቋ በመስጠቱ በኩል የምታደርጉት እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?*



www.eotcmk.org

ብፁዕነታቸው:- በተቻለ መጠን በሚገባቸው ቋንቋ ነው የምናገለግላቸው:: ለምሳሌ ቅዳሴውን ብንመለከት እንደ «ኦሐዱ..»፣ «እግዚኦታ» እና «ሀበነ» ያሉትን ካልሆነ የቀረውን ሁሉ በእንግሊዘኛ ነው የምንቀድሰው:: ቅዳሴያችን ሁሉ ቀደም ባሉት ምሁራን ወደ እንግሊዘኛ ስለ ተተረጐመ ችግር የለብንም:: በተረፈ ስብከቱንና የቀረውን ሁሉ በእንግሊዘኛ ነው የምንሰጠው::

ሐመር:- *አገልጋይ ካህናቱን በማስተማርና አገልግሎት በማስፋፋ ረገድስ?*

ብፁዕነታቸው:- በተቻለን መጠን ያሉት ካህናት /አፍሪካ - አሜሪካው ያኑን/ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ዐውቀው ምእመኑን በትጋት እንዲያገለግሉ እናስተምራለን:: ለዚህም የምንጠቀምበት ጊዜ የጾመ ፍልሰታን ወቅት ነው:: በዚህ ወቅት በየዓመቱ ካህናቱ ሁሉ ተሰብስበው በሱባኤና በመማማር እናሳልፋለን::

ሐመር:- *ቤተ ክርስቲያናችን በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ እንዲሁም በሌሎች አህጉር ተገኛለች:: ነገር ግን በብዛት እንደ ምንመለከተው በእነዚያ አካባቢዎች የቤተ ክርስቲያናችን እንቅስቃሴ በአካባቢው በስደት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ከመያዝና ከማገልገል ያለፈ አይደለም:: በእርስዎ ሀገረ ስብከት ግን ሙሉ በሙሉ ቤተ ክርስቲያናችን በዚያ የሚኖሩ አፍሪካ አሜሪካውያንን ወቅ ፈለች:: እያገለገለችም ነው:: ስለሆኑ የዚህ ምሥጢሩ ምን ይመስለዎታል?*

ብፁዕነታቸው:- እኔ እንደ ገባኝ በዚያ የሚኖሩ ጥቁሮች ቀደም ሲል በግዞት ከአፍሪካ የተወሰዱ፣ አፍሪካዊ ደም ያላቸው ናቸው:: በመሆኑም የሀገር ናፍቆት፣ የታሪክ ፍለጋ ጥማት አላቸው:: በመሆኑም ቤተ ክርስቲያናችንን እንደ ማንነታቸው መገለጫ ይቆጥሯትና ወደ ዕቅፏ ይገባሉ:: በነገራችን ላይ ከጥቁሮቹ በተጨማሪ በዚያ የሚኖሩ ሕንዶችም በእምነት ይመስሉናል፣ ይተባበሩናል:: በክህነትም የሚያገለግል አንድ ሕንዳዊ ዜጋ አለን:: እነዚህ ወገኖቻችን ቤተ ክርስቲያናችንን ከማንነት ጥያቄያቸው መልስነቷ በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያን ቀዳሚነት፣ የትምህርቷን ጥልቀት ተረድተው የመጡ ናቸው:: ብዙዎች «ዓለም ዐቀፋዊት ቤተ ክር ስቲያን ናት» [It is the Universal Church] ይላሉ:: ለሁሉም እግዚአብሔር ይመስገን::

ሐመር:- *አሜን÷ አባታችን:: ከዚያ አካባቢ የሚመጡ አንዳንድ ሰዎች የሚከተሉት አንድ እምነት አለ:: ይኸውም የቀድሞውን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን «እንደ አምላክ» ቆጥሮ «ማምለክ» ነው:: እነዚህ ሰዎች «ራስ ተፈሪያውያን» ይባላሉ:: ስለሆኑ ይህ እምነት በቤተ ክርስቲያናችን እንቅስቃሴ ላይ ያመጣው ችግር ይኖር ይሆን?*

ብፁዕነታቸው:- የለም:: እነዚህ ሰዎች ባለማወቅ ነው ወደ እንደዚህ ዓይነቱ እምነት የተሰማሩት:: ኢትዮጵያን ስለ ወደዱ፣ የእርሷንም መታወቂያ በመፈለግ ነው:: አሁን እየተረዱት ሲሄዱ ግን በዚያ ፈንታ ቤተ ክርስቲያንን መታወቂያቸው እያደረጉ ነው:: ያ የሆነው ከእኛ የማስተማር ጉድለት ሊሆን ይችላል:: ተምረው ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጡ በርካታ ናቸው:: አሁን ለምሳሌ በዚሁ ጉባኤ ለመካፈል ከእኔ ጋር የመጣው ይህ ካህን /ቃለ መጠይቁን ስናደርግ አብረውን የነበሩትን/ እንደዚሁ «ፀጉሩን ያስረዘመ» ነበር:: አስተምረነው ተጠምቋል:: በእውነቱ በመጀመሪያ እነዚህ ሰዎች ወደ እኛ መጥተው አጥ ምቁን ሲሉ ፀጉራችሁን ካልተላጫችሁ እንላቸው ነበር:: ነገር ግን በቅዱስ ሲኖዶስ ስለ ተወሰነልን አሁን ከነፀጉራቸው እያጠመቅናቸው ነው::

ሐመር:- *ከማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያ አስተዳደር ጋር ያላችሁ ግንኙነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ በውጭ ከሚገኙ ሌሎች አህጉረ ስብከት ጋር ያላችሁ የጉንዮሽ ግንኙነት እንዴት ነው?*

ብፁዕነታቸው:- እንገናኛለን:: ያው በሰሜን አሜሪካ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ማትያስ አሉ፣ ከእርሳቸው ጋር ምንም እንኳን የቦታ ርቀት ቢኖርም በስልክና በመሳሰሉት መንገዶች እንገናኛለን:: በዚያው አካባቢ ከሚገኙ ሌሎች አባቶች ጋር ግን ያው ምንም እንኳን ባንፈልገውም አስተዳደራዊ ልዩነት ስላለ በኢትዮጵያዊነታችን ከመገናኘት ያለፈ የሥራ ግን ኙነት የለንም::

ሐመር:-*በሰሜን አሜሪካ ስላለው የቤተ ክርስቲያናችን መከፋፈልና ስለ ምእመናን መደናገር የሚሰጡት አስተያየት ካለ?*

ብፁዕነታቸው:- በእውነቱ በዚህ ጉዳይ ከልቤ ከማዘን በስተቀር የምሰጠው አስተያየት የለም:: ቤተ ክርስቲያን «አሐቲ» /አንዲት/ ናት:: አሐቲ /አንዲት/ አድርጎ አምላክ በደሙ የመሠረተ ልንን እናት ቤተ ክርስቲያናችንን የእኛ ድካምና ሥጋዊ ሐሳብ ሊከፋፍላት አይገባም ነበር:: ያሳዝናል:: /ረጅም ዝምታ/:: ከምንም በላይ ደግሞ ምእመኑ ያሳዝነኛል:: ልናጽናናው፣ ልንመክረውና አንድነቱን ልናጠናክርለት ሲገባ እኛ እየተለያየን ልንከፋፍለው አይገባም ነበር:: የሆነው ሆኖ አሁንም ልንጸልይና አምላክን በልቅሶም ጭምር ልንጠይቀው ይገባል::

ሐመር:- *ምናልባት ይህ ችግር የእርስዎን ሀገረ ስብከትም ፈብሾ ይሆን?*

ብፁዕነታቸው:- አዎ÷ በጃማይካ አካ ባቢ ከቀድሞው የክፍሉ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ጋር በተያይዘ ችግር አለ:: ሁሉም ያሳዝናል::

ሐመር:-*ብፁዕ አባታችን እግዚአብሔር ይስጥልን::*

ብፁዕነታቸው:- አሜን ልጆቼ፤ እናንተንም እግዚአብሔር ያበርታችሁ:: በተቻለ መጠን በአካልም መጥታችሁ የሕዝቡን ሁኔታ ብትመለከቱ፣ ትምህርትም ብትሰጡ መልካም ነው::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



# ቸልተኛነት...

*/ከገጽ ፴ የዞረ/*

አይችልም፤ ብለው ይደ መድማሉ:: ትዳራቸውና ልጆቻቸው ወደ ባሰ ጥፋት ሲያመሩ ቢያዩም ስሜት አይሰጣቸውም:: ከዚህ ይልቅ አምሽቶ÷በመጠጥ ናውዞ እንደ ሰው በሁለት እግር፣ እንደ እንስሳ በአራት እግር፣ እንደ በርሜል÷ እየተንከባለሉ በውድቀት ሌሊት መግባትን ይመርጣሉ:: ተስፋ ሲቆርጡ ደግሞ አስቀድሞ ይፈጽሟቸው የነበሩትን መልካም ምግባራት ይተዋሉ:: ተስፋ የመቁረጣቸውም ምልክት ቸልተኝነታቸው ነው:: ተስፋ የቆረጠ ሰው ቢጸልይ ባይጸልዩ፣ ቢቆርብ ባይቆርብ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ቢታጎል ባይታጎል ቁም ነገሩ አይደለም:: ይሁዳ ጌታን በመሳም ለአይሁድ አሳልፎ ከሰጠ በኋላ እንደ ተፈረደበት ሲሰማ ተስፋ ቆረጠ:: ራሱን ሊያጠፋ ሄደ:: ጌታችንን አሳልፎ ከመስጠቱ በፊት ንስሐ እንዲገባ ጌታ ቢነግረውም፣ ዛፍ አንደበት አውጥታ ለንስሐ ብትጠራውም ሁሉንም በቸልታ ተመለከተ:: ተስፋ ቆርጧልና:: ማቴ.27÷3-9::

7. **በጥቂቱ መርካት**:- አንዳንድ ሰዎች ካሉበት ደረጃ እስኪ ደርሱ ድረስ በጣሙን ይተጋሉ:: ለመማር ማስተማር፣ ለመሥራት፣ ለመጾም ለመጸለይ፣ ንስሐ ለመግባት፣ ለመቁረብ፣ በቅዱስ ቁርባን ለማግባት ይተጋሉ:: ጊዜው ሁሉ ያንሳቸዋል:: ይሁን እንጂ ፍላጎታቸው ተፈጽሞላቸው ልቡናቸው ሲረካ ሁሉን ነገር ችላ ማለት ይጀምራሉ:: መማራቸውን የትምህርት፣ መጾም መጸለያቸውን የምግባር፣ ንስሐ መግባታቸውንና መቁረባቸውን የጽድቅ፣ ማግባታቸውንም የመጽደቅ ፍጻሜ አድርገው ይመለከታሉ:: ከዚህን በኋላ ስለ ራሳቸው ሲናገሩ «ነበርኩ» በማለት በትዝታ ይቀራሉ:: ለዚህ ነው በዘመናችን ጋብቻቸውን በተክሊል የፈጸሙት ሰዎች ከጋብቻቸው ዕለት በኋላ እግሮቻቸው ከቤተ ክርስቲያን ማጠር የሚጀ ምሩት:: ለእነርሱም ሩጫቸውን የጨረሱ÷ ተጋድሎአቸውን የፈጸሙ ያህል ይሰማቻ ዋል:: ጊዜው ቢርቅም፣ ንስሐው ቢተዳ ደፍም አንዴ ረክተዋልና ችላ ይላሉ:: ሰው ባለው ነገር÷ በሠራው ሥራ መርካት ከጀመረ ቸልተኛና ሰነፍ ስለሚሆን ነው ሐዋርያው:- «...በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረ ጋለሁ» ያለው:: ፊልጵ.3÷13::

እግዚአብሔር ጊዜንና ዐቅምን */ወደ ገጽ ፴፫ ዞሯል/*





www.eotcmk.org

# ቸልተኝነት

ቀሲስ ስንታየሁ አባተ ቅ/ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ

*ቸልተኝነት ማንኛውም ሰው በሕይወት ዘመኑ በተሠማራበት ሞያ፣ በተሰጠው ሓላፊነት በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊው ኑሮ የሚጠበቅበትን አገልግሎት ከመፈጸም መቆጠብ፥ መቀዝቀዝ፥ ተነሣሽነትና ትጋት ማጣት ነው። የጊዜ፣ የገንዘብ፣ የሥልጣን፣ የአእምሮ ብቃቱና ዐቅሙ እያለ ባለን ስጦታ አንድን በጎ ነገር ከመፈጸም መደንዘዝና ማንኛውንም ልማትም ሆነ ጥፋት፥ ጽድቅም ሆነ ኃጢአት ዝም ብሎ መመልከት ቸልተኝነት ይባላል።*

አንድ ሰው ቸልተኛ ሲሆን መንፈሳዊውንም ሆነ ሥጋዊውን ሓላፊነት ከመወጣት ይቀዘቅዛል። ኃጥአንና ወንጀለኞችን ከማስተማር፥ ከመምከር፥ ከመቆጣት ይታቀባል። ምንም ኃጢአተኛና ወንጀለኛ መሆኑን ቢያውቅም፣ ጥፋቱና ሊመጣበት የሚችለው አምላካዊ ቅጣትም ሆነ ሕጋዊ ፍርድ በተለያዩ መንገዶች ቢነገረውም ንስሐ መግባት፥ ከስሕተት መታረም አይሆንለትም።

ባለንበት ዘመን የአንድን ኅብረተሰብ መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ኑሮ ለተወሳሰቡ ችግሮች ከሚዳርጉት ዐበይት ነገሮች መካከል አንዱ ቸልተኝነት ነው። የልጆቻቸውን የተበላሸ ሕይወት እያዩ ለማስተካከል የማይጥሩ ወላጆች፣ በየመሥሪያ ቤቱ ያለውን ሙስና፣ አድሎአዊ አሠራርና ብክነት እያወቁ እርምት የማይሰጡ ሠራተኞች አሠሪዎች፥ በኅብረተሰቡ መካከል ግልጽ የሆነ ወንጀል ሲፈጸም እያዩ እንዳላዩ የሚሆኑ መንግሥታዊ የሆኑ የሕግ አካላት፣ እግዚአብሔር በደሙ የዋጃቸው ምእመናን፥ ለኃጢአት፣ለኑፋቄ፣ለተለያዩ አማኝ መሰል ወራሪዎች ሲሰጡ እየተመለከቱ ዐይናቸውን የሚከድኑ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፥ የቤተ ክርስቲያን ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ሀብት /ሥርዓቷ፣ ትምህርቷ፣ ታሪኳ፣ ንዋያተ ቅድሳቷ/ በውስጥና በውጪ ጠላቶቿ ሲወድም መፍትሔ የማይፈልጉ አካላትና የመሳሰሉት ሁሉ ቸልተኝነት ያጠቃቸው ናቸው።

ለመሆኑ ቸልተኝነት በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ እንዲከሰት የሚያደርጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

1.<u>ሰዎች ለራሳቸው ከሚሰጡት ዝቅ ያለ ግምት የተነሣ</u>፡-

አንዳንድ ሰዎች በተሠማሩበት የኑሮ መስክ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ሆነው በተሰጣቸው የጊዜ፥ የገንዘብ፥ የሥልጣን፥ የአእምሮ ብቃትና ዐቅም ሥራን መሥራት ሓላፊነትን መወጣት ጽድቅን መፈጸም የሚቻላቸው ቢሆንም ብናገር፣ ብሠራ፣ ንስሐ ብገባ... ለውጥ ማምጣት አልችልም ይላሉ። ሳይጀምሩ፥ ሳይጋደሉ ይሸነፋሉ። እግዚአብሔርና ሕዝቡ ብዙ ቢጠብቁባቸውም ራሳቸውን የበታች አድርገው ስለሚያዩ ማንኛውም ዓይነት ጥፋት ሲፈጸም ቢያዩ «አይቻለኝም፥ ሰው አይሰማኝም» በማለት ችላ ይላሉ። በዚህ የተነሣ ከፊታቸው የተንጣለለ ሰፊ የሥራ ሁኔታ ቢፈጠርም «ከእግዚአብሔር ጋር ሆኜ እሠራዋለሁ፥ እወጣዋለሁ» ከማለት ይልቅ በቸልታ ያዩታል።

በራሳችን ኃይል ብቻ የምንሠራው ነገር ባይኖርም በእግዚአብሔር ረድኤት ግን የማይቻል ነገር የለም። ደካሞች መሆናችንን አምነን ራሳችንን በደካሞች አድሮ ሥራ ለሚሠራ ለእግዚአብሔር ብናስገዛ ሁሉ ይቻለናል። ይህንንም ከሊቀ ነቢያት ሙሴና ከቅዱስ ዳዊት ታሪክ እንረዳለን። ሊቀ ነቢያት ሙሴ ወደ ፈርዖን እንዲሄድ በታዘዘ ጊዜ፡- «ጌታ ሆይ፥ እኔ አፌ ኰልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆንኩ ሰው ነኝ። ትላንት ከትላንት ወዲያ ባርያህንም ከተናገርኸኝ ጀምሮ አፈ ትብ ሰው አይደለሁም።» በማለት ያለበትን ድካም ለእግዚአብሔር በመግለጡ፡ - «እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፤ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ።» ተባለ። ዘጸ.4፥10-13። ቅዱስ ዳዊት የጦር ስልትን የማያውቅ የበጎች እረኛ የነበረ ሰው ነው። ከጎልያድ ግርማ የተነሣ አናሶችና ደካሞች እንደ ሆኑ አድርገው ራሳቸውን በመገመት አእላፈ እስራኤል ግራ በተጋቡበት ወቅት ቅዱስ ዳዊት ታናሽነቱን ከማመን ጋራ «ስለ እርሱ የማንም ልብ አይውደቅ፤ እኔ ባሪያህ ሄጄ ያንን ፍልስጥኤማዊ እወጋዋለሁ።» አለ። እንዳለውም በእስራኤል አምላክ ስም ድል አደረገው።

በአገራችን ለዘመናት የተከማቹ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን በመመልከት ገና ሳይጀምሩ የሚሸነፉ ባለሥልጣናት፣ ባለ ሀብቶችና ዐዋቂዎች ብዙ ናቸው። «እኛ እንጀምረውና እግዚአብሔር ያስፈጽመናል፤ እኛ ብንጀምረው ልጆቻችን ይፈጽሙታል» ማለት ሲገባ ሰንፈው ያሳንፋሉ። «የብዙ ኪሎ ሜትሮች መነሻ አንድ ርምጃ ነው» እንደሚባለው የነገ መልካም ውጤት መሠረት ዛሬ የምናሳየው ትጋት ነው። ሀገራችንን ከተመጽዋችነት፣ወገኖቻችንን ከስደት መታደግ የምንችለው በራስ ጠጉራችን ልክ የበዙብንን ችግሮቻችንን ተመልክተን ቸልተኛ ከመሆን ይልቅ እግዚአብሔር በሰጠን አገር፣ጊዜ፣ዕውቀት የተፈጥሮ ሀብትና ሕዝብ የተቻለንን ስንሠራ ብቻ ነው።

2. <u>ፍርሃት</u>፡- «እውነቱን ብናገር፣ ብሠራ... ችግር ይደርስብኛል፣ ከሥራ ገበታየ እባረራለሁ፣ ጥቅማ ጥቅም ይቀርብኛል» ብለው የሚሰጉ ሰዎች ለማንኛውም ዓይነት ጥፋት ቸልተኞች ይሆናሉ። ከእውነት፣ ከሃይማኖት፥ ከወገን፥ ከአገር ይልቅ የግዛ ጥቅማቸውን ስለሚያስቀድሙ ጥቅማቸውን ላለማስነካት ሲሉ ሁሉን በቸልተኝነት ይመለከቱታል። የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በመናፍቃን ሲበረዝ፣ ሥርዓቷ ሲጣስ፣ ሲጓደል፣ መዝሙሯ ሲነቀፍ፣ ገንዘቧ ሲዘረፍ የበላይ የበታቹን፥ የበታቹ የበላዩን በመፍራት እያወቀ እንዳላወቀ፣ እያየ እንዳላየ ሆኖ በቸልታ ያልፈዋል። እግዚአብሔር ግን ሁሉን በረቀቀ ምሥጢሩ ይመራመራል። ነቢዩ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ምሥጢር ሊያስተምር፥ሕዝቡን በቀናው መንገድ ሊመራ የተነሣ ነቢይ ነበር። ንጉሡ ያዝያን ሥልጣኑን መከታ አድርጎ እግዚአብሔርን ተጻረረ። የካህናቱን ጩኸት ወደ ጎን አድርጎ ያለ ድርሻው ያልተሰጠውን ሠራ። የእስራኤል ጉበኛ የነበረው ኢሳይ ያስ ይህን ጉዳይ ቢያውቅም ንጉሡ ሊያመጣበት የሚችለውን ቅጣት በመፍራት ሁሉን ችላ አለ። ለንጉሡ ያለው ፍርሃት በሥጋውም በነፍሱም ሥልጣን ያለውን የእግዚአብሔርን ቁጣ አስረሳው። ንጉሡ በኃጢአቱ ተቀሰፈ፤ ነቢዩ ኢሳይያስም ሀብተ ትንቢቱ ተነሳው፤ በለምጽም ተመታ። በዘመናችንም ከሹመኞች ሊያገኛቸው የሚችለውን ጊዜያዊ መከራ በመፍራት ፍርድ ሲጓደል፥ አገር ስትጠፋ፥ ቤተ ክርስቲያን ለጉዳት ስትሰጥ በቸልታ የሚያዩ አሉ። 2ዜና.26፥16-21፤ ኢሳ. 6፥5-8።

ሰውየው በአንድ መሥሪያ ቤት የአንድ መምሪያ ሓላፊ ናቸው። ሓላፊ በሆኑበት ሥራ በተለያዩ ቦታዎች ጥፋት፥ ዝርፊያ ይፈጸማል። በዚህ ዙርያ ስንወያይ ያጫወቱኝ ነገር፡- «የጥፋቱን ምንጭ ዐውቀዋለሁ። እውነቱን ብናገር፥ እንኳን እኔና ልጆቼ፥ ውሻዬ እንኳን አንድ ቀን አያድርም» በሚል ነበር። እንዲህ ዓይነት ሰዎች «ፈሪና ተራራ ዘላለም ይኖራል» በሚል ፈሊጥ ተይዘው ቸልተኛ በመ



www.eotcmk.org

ሆን ኀሊናቸውን ያጨልማሉ:: ከፍርሃት የተነሣ በቸልተኝነት ያለፉት ጥፋት ለገዛ ልጆቻቸው የነገ ሕይወት ማነቆ ይሆናል::

3. **ፍቅር ማጣት**:- ለአንድ ሰው በተሰለፈበት የሞያ መስክ ጽናት ትጋት ከሚሰጡት ነገሮች መካከል አንዱ ፍቅር ነው:: ለሃይማኖቱ፣ ለአገሩ፣ ለሕዝቡ፣ ለሥራው ፍቅር ያለው ሰው ኃይል አለው:: ጠቢቡ ሰሎሞን «ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናት::... ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፉት ዘንድ አይችልም» ያለውም የፍቅርን ኃያልነት ያሳያል:: መኃ.8÷6-7:: ይህን ያህል ኃይል የሆነው ፍቅር ከአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ሲጠፋ ለሁሉም ነገር ቸልተኛ መሆን ይመጣል:: ሰዎች ያለ ፍላጎታቸውና ያለ ዕውቀታቸው በተጽዕኖ በአንድ የሥራ ገበታ ላይ ይመደቡና አልያም አማራጭ ሥራ ስላጡ ወይም የተደበቀ ዓላማ ይኖራቸውና ለተመደቡበት አገልግሎትና ሞያ ፍቅር ሊያጡ ይችላሉ:: የሰዓት ፊርማ ብቻ እንዳያመልጣቸው፣ ወንበሩ ባዶ እንዳይሆን ይገኛሉ:: ከወንበሩ ወይም ከተረከቡት አደራ በስተ ጀርባ ስላለው ጉዳይ ግን ደንታ ቢስ ይሆናሉ::

በመሠረቱ ማንኛውም ሰው በሥራው ውጤታማ የሚሆነው በዕውቀቱና በፍላጎቱ መሠረት ሲማራ ነው:: የድጓ፣ የቅኔ፣የአቋቋም፣የመጽሐፍ ትርጓሜ ደቀ መዝሙሩን አለቃ አልያም በሥነ መለኮት ትምህርት የተመረቀውን ገበዝ አድርጎ መመደብ ፍቅርን ያሳጣል:: በመንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችም በቅርቡ እንደ ታየው ያለ በቂ ጥናት በሽግሽግ ሰበብ ሰዎችን ዕውቀትና ልምድ ካካበቱበት ሥፍራ አንሥቶ ያለደረጃቸው ማስቀመጥ ለሥራ ያላቸውን ይጎዳል:: በ1983 ዓ.ም. በተደረገው የመንግሥት ለውጥ ወቅት የአንድ ዩኒቨርስቲ መምህር በነበሩት ላይ የደረሰውን ልንገራችሁ:: መምህሩ የትምህርት ሥነ ዘዴ /Pedagogical science/ መምህር ነበሩ:: ከነበሩበት ዩኒቨርስቲ አንሥተው በአንድ የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የአማርኛ መምህር አደረጓቸው:: እኒህ ሰው በዚህ የተነሣ ሥራውን ቸል ከማለት አልፈው ለአእምሮ ሕመም ተዳረጉ:: ሠራተኛን በሞያውና በዝንባሌው ማሠራት አገርን ለሚናፈቀው ዕድገትና ልማት ያደርሳታል::

በሌላ በኩልም ለእግዚአብሔርና ለቤቱ ፍቅር ማጣትም ከዚሁ ጋር የሚታይ ነው:: ካህኑ ዔሊ ለልጆቹ የነበረው ፍቅር ለእግዚአብሔር ከነበረው ፍቅር ይበልጥ ስለነበረ ልጆቹ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ላይ ያደረሱት በደል ቢነገረውም የሚጠበቅበትን ያህል ልጆቹን መሥራት መቅጣት ተሳነው:: ዕለት ዕለት የልጆቹን ጥፋት እየሰማ ችላ አለ:: 1ሳሙ.2÷12-36:: ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን እስከ አፍንጫው የታጠቀውን የፋሽስት ኢጣሊያን ጦር ለማሸነፍ፣ ጀግናው ዘርዓይ ድረስ በሰው አገር በአገራቸው ላይ የሚሳለቁትን ለመቅጣት የቻሉት የአገር፣ የወገንና የታሪክ ፍቅር ስለ ነበራቸው ነው፤ በዐፄ ሱስንዮስ ክሕደት የተነሣ 8000 ምእመናን በአንድ ቀን ያለቁት የሃይማኖት ፍቅር ስለ ነበራቸው ነው፤ ፍቅራቸው ጠላት በአገርና በሃይማኖት ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት በቸልተኝነት እንዳይመለከቱት ስላደረጋቸው ነው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ:- «በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ» ያለው ምእመናን ከፍቅር ማጣት የተነሣ ለቸልተኝነት እንዳይዳረጉ ነው:: ሮሜ.12÷11::

4. **ዓላማ ቢስነት**:- አንድ ክርስቲያን በተጋድሎ እንዲጸና፣ ሓላፊነቱን እንዲወጣ፣ ከኃጢአት እንዲጠበቅ ለቤተ ክርስቲያን እንዲቀናና እንዲተጋ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አንዱ ዓላማ ነው:: ቅዱስ ዳዊትን ወደ ቤቱ ድንኳን እንዳይገባ፣ ወደ አልጋውም እንዳይወጣ፣ ለዐይኖቹ መኝታ፣ ለሽፋሽፍቶቹም እንቅልፍ፣ ለጉንጮቹም ዕረፍትን ከመስጠት እንዲከለከል ያደረገው ለእግዚአብሔር ስፍራ፣ ለያዕቆብ አምላክ ማደርያ ለማግኘት የነበረው ዓላማ ነው:: መዝ. 131÷3-6:: ቅዱስ ጳውሎስንም በ2ቆሮ. 11÷23-29 ላይ የተዘረዘሩትን መከራዎች ለመቋቋም ያበቃው ለእግዚአብሔር ቤት የነበረው ዓላማው ነው:: ይህን መሰል ጽኑዕ ዓላማ የሌለው ሰው በሥራው ሁሉ ቸልተኛ ይሆናል:: የሚኖርለትና የሚተጋለት ዓላማ ስለሌለው ግዴለሽ ይሆናል:: አገራችንና ቤተ ክርስቲያናችን ከየከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻቸው በየዓመቱ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ያስመርቃሉ:: ባለሞያ ይቀጠራል:: ገንዘብ ወጪ ይደረጋል:: የሚጠበቀውን ያህል ግን ለውጥ የለም:: አሠሪውም ሠራተኛውም ዓላማው ሠላሳ ቀኖችን ሠርቶ ደመወዝ ማግኘት ብቻ ከሆነ ኑሮው ሁሉ ባለህበት እርገጥ ይሆናል:: የአብራኩ ክፋይ የሆኑ ልጆቹ ጥሩ ነገን እንዲያዩ÷ ከእርሱ ሻል ያለ ሕይወት እንዲኖራቸው ለማድረግ ካልሠራ ቸልተኝነት ይሰፍንበታል:: ሠለስቱ ደቂቅ ከሀገር ከወገን ርቀው÷ እግዚአብሔር በማይታወቅበት አገር ቸልተኝነትን አርቀው ስለ ሕገ እግዚአብሔር ሰውነታቸውን ለእሳት ለስለት አሳልፈው እንዲሰጡ ያደረጋቸው በሃይማኖት ገንዘብ ያደረጉት ዓላማቸው ነው:: ነቢዩ «ስለ ከንፈሮችህ ቃል ጭንቅ የሆኑ መንገዶችን ጠብቅሁ» ማለቱም ይህንኑ ያሳያል:: መዝ. 16÷4::

5.**የሥጋዊ ጥቅም ተገዢ መሆን**:- ሥጋዊ ጥቅም የአንድን ምእመን መንፈሳዊ ቅናትና ትጋት እንዲበርድ ያደርጋል:: በሥጋዊ ጥቅም የተያዙ ሰዎች ጥቅማቸውን እንጂ ሓላፊነታቸውን ብሎም ከሰውም ከእግዚአብሔርም ሊደርስባቸው የሚችለውን ቅጣት ሊያስተውሉት አይችሉም:: ስለ ሥራ መበደል፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መጓደል፣ ስለ ኅብረተሰቡ ጩኸት ቁብ የማይሰጣቸው ይሆናሉ:: የዘወትር ጥረታቸው ጥቅማቸውን በማስጠበቅ ላይ ይሆናል::

ይህ ሥጋዊ ጥቅምም በአንድ ጊዜ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚከሰት ሳይሆን ቀስ በቀስ ሥር የሚሰድ ይሆናል:: የከበሩ ስጦታዎች፣ የተለያዩ ግብዣዎች፣ በሓላፊነት ወንበር ላይ ያሉትን ሰዎች የሥጋዊ ጥቅም ተገዢ ለማድረግና ተገቢውን አደራቸውን እንዳይወጡ÷ ቸልተኞች እንዲሆኑ÷ ሁነኛ ምክንያቶች ናቸው:: በሕግ ከተፈቀደው ደመወዝ ውጭ ለባለ ሥልጣናት የሚቀርቡ እጅ መንሻዎችና ሙገሳዎች የባለ ሥልጣኑን አደራውን የመወጣት ዐቅም የሚሰልቡ÷ ሲበዙም ለእውነት እንዳይሠራ እደ ልቡናውን የሚያስሩ፣ እንዳይናገር አንደበቱን የሚገቱ ልጓም ይሆኑበታል:: የሚያስተ ምሩት የአምስተኛ ክፍል ተማሪ «Girl» የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል «ጀርል» ብሎ ሲያነብ መምህሩ ይሰሙታል:: ግን አያርሙትም:: «ምነው አያርሙትም ወይ?» ሲባሉ በዚህን ያህል ደመወዝ «ገርል» በል ብዬ ላስተምር ነው ወይ? አሉ:: በመንግሥት ሆስፒታል በሽተኛው በደዌ ሲሰቃይ÷ ደሙ እንደ ውኃ ሲፈስ «የሻይ ሰዓታቸውን» የሚጠብቁ «የጤና ባለሞያዎች» በግል ጤና ጣቢያዎች ትንፋሽ እስኪያጥራቸው ሲሠሩ የሚታዩት የጥቅም ነገር ከሆነስ?... በኵረ መናፍቃን ሲሞን ለቅዱስ ጴጥሮስና ለቅዱስ ዮሐንስ ብዙ ገንዘብ ይዞ የቀረበው በገንዘቡ ጥቅም ኅሊናቸውንና ልቡናቸውን ይዞ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ እንደ ፈለገ ገንዘብ ለያካብት በት ነበር:: ይሁን እንጂ ለነፍስ ጥቅም እንጂ ለሥጋ ጥቅም ያልተገዙ ቅዱሳን ሐዋርያት ቸልተኝነትን አስወግደው:- «የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ» ለማለት በቁ:: በዘመናችን የሚገኙ የሥጋም ሆነ የመንፈስ መሪዎቻችን ይህን ልብ ሊሉት ይገባል:: ሥራ. 8÷12-21::

6.**ተስፋ መቁረጥ**:- ሰዎች ሥራን፣ ጤናን፣ ሰላምን ከማጣት፣ ከሰይጣን ፈተናዎች የተነሣ ተስፋ ሲቆርጡ ይታያሉ:: በትዳራቸው ሰላም ማጣት፣ በልጆቻቸው ዋልጌነት ተስፋ የሚቆርጡ አሉ:: በመነጋገር፣በመሸነፍ ለውጥ ሊመጣ

/ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል/



www.eotcmk.org

# * የክርስትና ስም * የክርስትና አባትና እናት

ጌታቸው በቀለ

ስመ ክርስትና በግእዝ ሲሆን በአማርኛ የክርስትና ስም/የመጽሐፍ ስም፣ ስመ ጥምቀት/ በመባል ይታወቃል:: ስመ ክርስትና የቅድስና ስም ነው:: ይህ ስም ምድራዊም ሰማያዊም ነው::

የክርስትና ስም /ስመ ክርስትና/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን የሚጠሩበት መንፈሳዊ ስም ነው:: ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች የሚወለዱ ሕፃናት፤ በወላጆቻቸው ሓላፊነት፣ በክርስትና አባትና እናት ተወካይነት ወንድ በ40ኛው፣ ሴት በ80ኛው ቀን፤ ስም ነታቸውን የክርስትና አባት ወይም እናት እየመሰከረላቸው ይጠመቃሉ:: ማቴ.19.14፤ ማር10.14፤ ሉቃ18.16 ወ.ዘ.ተ::

ሰመሆኑ የስመ ክርስትና አጀማመር ጥንተ ታሪክ እንዴት ነው? ማነው የሚሰይመው? እንዴት ይሰየማል? ከዚሁ ጋር የክርስትና ስም ጥቅሙስ ምንድን ነው? ቅጽሎቹ /ዘርፎቹ/ የሚባሉት የትኞቹ ናቸው? በሀገራችን የዓለም ስምና የክርስትና ስም ተብሎ መጠሬት የተጀመረው መቼ ነው? የክርስትና አባትና እናት ማለት ምን ማለት ነው? ተግባራቸውስ ምንድን ነው? በዚህ ዙሪያ ያሉ አጠቃላይ ችግሮችና መፍትሔዎችስ ምን ይመስላሉ? ለእነዚህና ሌሎችም በምእመናን ኅሊና የሚመላለሱ ተዛማች ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ ብለን ያሰናቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት አገላብጠን ፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ጠይቀን ያዘጋጀነውን እንዲህ አቀናብረ ነዋል:: መልካም ንባብ::

## የክርስትና ስም /ስመ - ጥምቀት/

ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ወንዶች ሕፃናት በተወለዱ በአርባ /40/ ቀናቸው፣ ሴቶች ደግሞ በሰማንያ /80/ ቀናቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው እንዲጠመቁ ታስተምራለች:: ታጠምቃለች:: ስመ ክርስትናንም ትሰጣቸዋለች::

ይህንንም የምታደርገው በቅዱስ መጽሐፍ በስፋት ተተርኮ የሚገኘውን የብሉይ ኪዳን ሥርዓት መሠረት በማ ድረግ ነው:: ሊቃውንተ ቤተ ክርስ ቲያን በስፋት እንደ ሚያስተምሩት እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በምድር ላይ ከፈጠረ በኋላ፤ አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ ሔዋን በተፈጠረች በ80 ቀኗ የብርሃን ልብስ አጐናጽፎ ወደ ዔደን ገነት አስገብቷቸዋል:: "እግ ዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ ዔደን ገነትን ተከለ፤ የፈጠረውንም ሰው በዚያ አኖረ" ዘፍ. 2፥8:: በዚህ የተነሣ ወን ዶች በተወለዱ በ40 ቀናቸው፣ ሴቶች ደግሞ በ80 ቀናቸው ካህኑ ወዳለበት ወደ መገናኛው ድንኳን /ደብተራ ኦሪት/ ተወስደው እንዲባረኩ ታዟል:: ዘሌ.12፥1-8:: ኩፋሌ 4፥4-13:: በዚህ መሠረት እስራኤላውያን ሕፃናት በተ ወለዱ በ40 እና በ80 ቀናቸው ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው መሥዋዕት ይሰ ውላቸው ነበር:: ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትን ተቀ ብለው፤ የእግዚአብሔር ወገን ተብለው ይጠራሉ:: ዘጸ.4፥22::

ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን መ ሠረቱ ነውና፤ ጌታችን መድኃኒታ ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጻሜ ሕግ እንደ መሆኑ፤ በተወለደ በ40 ቀኑ ወደ ቤተ መቅደስ ተወስዷል:: ሉቃ. 2፥22-28:: ቤተ ክርስቲያንም ይህ ንን በብሉይ ኪዳን የነበረውንና ጌታ ችንም በሥራ የፈጸመውን ሥርዓት መሠረት በማድረግ ሕፃ ናትን በተ ወለዱ በአርባና በሰማንያ ቀናቸው ታጠምቃለች:: ሕፃናቱ ለሞት የሚ ያስጋቸው ሕመም ካገኛቸው፤ ከአር ባና ከሰማንያ ቀናት በፊት ሊጠመቁ ይችላሉ:: በልዩ ልዩ ምክን ያቶች ሕ ፃናቱ የመጠመቂያ ቀናቸ ውን /አርባና ሰማንያ ቀን/ አሳል ፈው ቢ መጡም ይጠመቃሉ:: በእር ግጥ አሳ ማኝ ምክንያት ሳይኖር ወላጆች በየምክንያቱ የልጆቻቸውን የመጠ መቂያ ቀን ሊያሳልፉ አይገ ባም:: ጌታችንም በወን ጌሉ "ብትወ ዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" /ዮሐ.14፥ 15/ ብሎ እንደ ተናገረው፤ ምእመ ናንም ይህን ከግንዛቤ በማድ ረግ የቤተ ክርስቲያናቸውን ሥርዓትና ትእዛዝ ሊያከብሩና ሊጠብቁ ይገ ባል:: /<u>ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው</u>፥ አንቀጽ 3/::

በብሉይ ኪዳን ዕብራውያን ለልጆቻቸው ስም የሚያወጡት /የሚሰይሙት/ ሕፃናቱ በተወለዱ በስምንተኛው ቀን ወንዶች ከሆኑ በሚገ ረዙበት ዕለት ነበር:: አብርሃም ለልጁ "ይስሐቅ" ብሎ ስም ባወጣለት በስምን ተኛው ቀን መገረዙ ተጽፏል:: "አብር ሃም የተወለደለትን፤ ሣራ የወለ ደች ለትን የልጁን ስም ይስሐቅ ብሎ ጠራው:: አብርሃምም ልጁን ይስሐ ቅን እግዚአብሔር እንዳዘዘው በስም ንተኛ ቀን ገረዘው::" ዘፍ.21፥3-4:: ይሁን እንጂ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እንደ ሚያስረዱት በተወለዱ በስምንተኛው ቀን ብቻ ሳይሆን ከመወ ለዳቸው በፊት፣ በሚወለዱበትም ዕለት ስም ይሰየምላቸው ነበር:: ለምሳሌ ያህል ብንመለከት:- ራሔል በምጥ ተጨንቃ በሞት አፋፍ ላይ በነበረ ችበት ወቅት የወለደችውን ልጅ "ቤን ኦኒ" ብላ ጠ ርታዋለች:: በኋላ ላይ አባቱ ያዕቆብ ብንያም ብሎታል:: ዘፍ. 35፥18:: አብዛ ኛውን ጊዜ ከስምንተኛው ቀን በፊት የሚሰየሙ ስሞችም እንኳን ቢሆኑ የሚ ጸድቁትና አገልግሎት ላይ የሚውሉት በስምንተኛው ቀን በግዝረት ዕለት ነው:: ለምሳሌ:- መጥምቀ መለኮት ዮሐ ንስ ስም የወጣለት ከመፀነሱ አስቀድሞ በመ ልአኩ ብሥራት ሲሆን ስያሜው ጸድቆ በስሙ መጠራት የጀመረው ግን በተወለደ በስምንተኛው ቀን በሚገረ ዝበት ዕለት ነበር:: ሉቃ.1፥13፤59፤63:: ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስም ስለ ጌታችን ስም ሲናገር "ሊገርዙት ስምንት ቀን በሞላ ጊዜ፤ በማኅፀን ሳይፀነስ በመል አኩ እንደ ተባለ፥ ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ" ሉቃ.2፥21:: ይላል:: ከላይ በአጭሩ ከተመለከትናቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች በብሉይ ኪዳን ዕብራ ውያን ለልጆቻቸው ስም የሚ ያወጡት ወይም አስቀድሞ የተሰጠውን ስያሜ የሚያጸድቁት ሕፃናቱ በተወለዱ በስም ንተኛው ቀን /በግዝረት ዕለት/ እንደ ሆነ እንረዳለን:: /ዲ/ን አየለ አሻግሬ፤ <u>ጥምቀተ ሕፃናት</u>፤ 1989ዓ.ም/::

ከዚህም በተጨማሪ የስም ለውጥ ተሰያሚውን የራስ የማድረግ መግለጫ ነው:: እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ ስማ ቸውን ለውጧል:: ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ወደ ቤተ ክርስ ቲያን የሚገቡ ሰዎችም ሆኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡ ንዋያተ ቅድሳት ሃይ ማኖታዊ የሆነ መንፈሳዊ ምሥጢርን የያዘ የስም ለውጥ ይደረግላቸዋል:: እግ ዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ሲመ ርጥ አዲስ ስም ይሰይምላቸው እንደነበር ለአብነት የሚሆኑንን የተወሰኑትን እንመልከት:- "ሐና ወንድ ልጅ ወለ




www.eotcmk.org

ደች፤ እርስዋም፡- ከእግዚአብሔር ለምኜዋለሁ ስትል ስሙን ሳሙኤል ብላ ጠራችው።" 1ኛሳሙ. 1፥20። "ከዛሬ ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፥ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና።" ዘፍ. 17፥5። "እግዚአብሔር አብርሃምን አለው፡- የሚስትህን የሦራን ስም ሦራ ብለህ አትጥራ። ስምዋ ሣራ ይሆናል እንጂ." ዘፍ. 17፥15። "ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል። ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና።" ዘፍ. 32፥28። በትንቢተ ዳንኤል እንደ ተገለጸው ዳንኤል ብልጣሶር ተብሎ ተጠርቷል። ዳን. 4፥19። ሠለስቱ ደቂቅ የተባሉት ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎም በእምነታቸው ጽናት የመጣባቸ ውን ፈተና ሁሉ ሲያሸንፉ ስማቸው አናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል ተብሎ ተለውጧል።

በሐዲስ ኪዳንም ጌታችን ቀራጩ ስምዖንን "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ" ማቴ.16፥17። ብሎታል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የቀደመ ስሙ ሳውል ነበር፤ እግዚአብሔር ሲጠራው ግን ጳውሎስ ተብሎ ተጠርቷል። የሐዋ.ሥራ 9፥10። ቅዱሳን ስም ከተለወጠላቸው በኋላ በቀረ ዘመናቸው ሁሉ በአዲሱ ስማቸው ሲጠሩ እንደኖሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። ዓለማዊ የሆነ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ተመልሶ በምክረ ካህን በፈቃደ እግዚአብሔር ሲኖር ስሙ ተለውጦ መንፈሳዊ ይባላል። እንደዚሁ ሁሉ ንዋያተ ቅድሳቱም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ስማቸው ይለወጣል። ለአብነትም ያህል የቅዱስ ሥጋው ማክበሪያ "ጻሕል"፣ የክርስቶስ ክቡር ደሙ የሚቀርብበት "ጽዋዕ"፣ ዲያቆኑ ክቡር ደሙን የሚያቀብልበት "ዕርፈ መስቀል"፣ የዕጣን መስዋዕት ማቅረቢያው "ጽንሐሕ" ይባላል። የክርስትናን ስም መስጠት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ብቻ ሳይሆን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም የተለመደ ነው። ይህም ከ2ኛው መ/ክ/ዘ ጀምሮ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት፣ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የሩስያ ኦርቶዶክስ ስምን በመለወጥ ይጠሩ ነበር። /George W.Grube; THE COMPLETE BOOK OF ORTHODOXY: 151/

በሐዲስ ኪዳን ግዝረት በጥምቀት ተተክቷል። "የሥጋንም ሰውነት በመገፈፍ በክርስቶስ መገረዝ፥ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ፤ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ። በጥምቀትም ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ።" ቆላ.2፥11-12። በመሆኑም በብሉይ ኪዳን በግዝረት ዕለት ስም እንደሚወጣ ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችን ይህንን መሠረት በማድረግ ተጠማቂዎች በሚጠመቁበት ዕለት ለእያንዳንዱ ተጠማቂ ስም ትሰይማለች። ይህም ስመ ጥምቀት /የክርስትና ስም/ ይባላል። ስመ ጥምቀት መባሉም አንድ ተጠማቂ በሚጠመቅበት ጊዜ /ዕለት/ ስለሚሰየምለት ነው።



## ስመ ክርስትናን ማነው የሚሰይመው? እንዴትስ ይሰየማል?

ስም መጠሪያ ነው። አንዱ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት መታወቂያ ነው። ክፉም ሆነ መልካም፣ ዐመፀኛም ሆነ ሰላማዊ ተለይቶ እንዲታወቅ ለሌላው በጽሑፍም ሆነ በቃል ማስተላለፍ የሚቻለው በስሙ አማካይነት /መለያነት/ ነው። መልኩን በማየት ሌሎች እንዲያውቁት ማመልከት ቢቻልም ስም የሚገልጠውንና የሚያስተላልፈውን፣ በስሙ ሊታወቅ የሚችለውን ያህል መልኩ ሊተካለት አይችልም።

የክርስትና ስም ግን የራሱ የሆነ መንፈሳዊ ምሥጢር አለው። በክርስቶስ የሚያምኑ ምእመናን ክርስቲያን ሲባሉ እምነታቸው የክርስትና እምነት ይባላል። በመሆኑም የክርስትናን ትምህርት ተምረን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በምንጠመቅበት ጊዜ ካህኑ የሚሰይምልን መንፈሳዊ ስም ነው። ይህ ስምም በክርስትና ሕይወት ስንኖር ማንነታችንን ይገልጻል።

የክርስትና ስም የሚሰየመው እንዲሁ እንዲጋጠመን፣ በዘፈቀደ አይደለም። መሠረታዊ ምክንያት አለው። አሰያየሙን በሦስት መንገድ ማየት እንችላለን፡-

*1. በቀጥታ የሚሰየም*
*2. የቅዱሳንን ስም ዘርፍ በማድረግ የሚሰየም*
*3. ቤሎች ልዩ ልዩ ስያሜዎች ናቸው።*

1. <u>በቀጥታ የሚሰየም</u>፡-

ካህኑ በቀጥታ የሚሰይማቸውን አስማተ ክርስትና /የክርስትና ስሞች/ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርገን እንመለከታለን። በካህኑ የሚሰየመው ስም የክርስትና ስም ብቻ ሆኖ እንዲቀር ሳይሆን የተጸውኦ /መጠሪያ/ ስም ሆኖ እንዲያገለግልም ነው። የእግዚአብሔር መልአክ ያዕቆብን "እስራኤል" ብሎ ጠርቶታል። ዘፍ.32፥28። የክርስትና ስም በካህኑ የሚሰየመው መጠሪያ /የተጸውኦ/ ስም ሆኖ እንዲያገለግል ነው እንጂ «ክርስትና ተነሥቻለሁ፣ የክርስትና ስም አለኝ» ለማለትና ሰውየው ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ወቅት ለፍትሐት እንዲያገለግል አይደለም። በክርስትና ስም መጠራት በስፋት ቢለመድ የሚያስደስት ተግባር ነው። ካህኑ የሚሰይምልንን ስመ ክርስትና ምእመናን በጥንቃቄ ሊይዙት ይገባል።

እንደ ገድላት፣ ድርሳናት... ወዘተ ባሉ የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት ስንመለከት "ልጁን በስምህ /በስምሽ/ የጠራውን... እምርልሃለሁ /እምርልሻለሁ/" የሚለው ቃል ኪዳን ተጽፎ ይገኛል። ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን ቃል ኪዳን መሠረት በማድረግ በቀጥታ በቅዱሳኑ ስም፤ ስመ ክርስትናን ይሰይማሉ።

ምሳሌ፡- ዮሐንስ፣ ጳውሎስ፣ ጊዮርጊስ፣ ተክለ ሃይማኖት፣ ኤልሳቤጥ ኤርምያስ፣ ዳንኤል፣ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ክርስቶስ ሠምራ፣ እግዚእ ኃርያ፣ አሮን፣ ኢየሱስ ሞዓ፣ ኤልያስ፣ እንድርያስ ገላውዴዎስ፣ እስጢፋኖስ፣ ቀሌምንጦስ፣ ቂርቆስ፣ ጴጥሮስ...ወዘተ በማለት ይሰይማሉ።

ለአብነት ያህል አዋልድ መጻሕፍት ላይ ከተጠቀሱት የተወሰኑትን እንመለከታለን። በተአምረ ማርያም ላይ እንደ ተገለጸው፡- "ዘጠኝ እስላሞች ሁለት ሕፃናትን አስከትለው ወደ ንግድ ሲሄዱ ግንቦት 21 ቀን የእመቤታችን



www.eotcmk.org

በዓል በሚከበርበት በደብረ ምጥማቅ ደረሱ። ሁለቱ ሕፃናት መሐመድና ዓሊ ይባሉ ነበር። እመቤታችን ሕፃናቱን ተመልክታ፣ መሐመድን "ሚካኤል" ዓሊ ይባል የነበረውን "ጊዮርጊስ" ብላ ሰይ ማ፣ ሕፃናቱ ተጠምቀው ክርስቲያን ሆነ ዋል።» /ተአምረ ማርያም፣ ዘከመ ገብ ረት ተአምረ በደብረ ምጥማቅ፣ ተአምር 17፣ ገጽ 79/።

በገድለ ተክለ ሃይማኖትም ላይ ተመሳሳይ ታሪክ እናገኛለን። ድር አስ ገድ የሚባል ሀገረ ገዥ ሰዎችን በአንዲ ት ዛፍ ስር ለጣዖት እያሰገደ ከዚያ በሚ ያገኘው ገቢ የሚተዳደር ነው። ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዛፏ አድሮ የሚያሰግደውን ሰይጣን አስወግደው ሀገረ ገዥውንና ሕዝቡን አስተምረው፣ አሳም ነው ወደ ክርስትና ሃይማኖት እንዲ መለሱ አድርገዋል። ድር አሰገድንና ሚስ ቱን፣ ልጆቹንም ቤተሰቡንም አጥምቀ ዋል። ድር አሰገድን አሚነ ክርስቶስ፣ ሚስቱን አክሮስያ፣ አንዱ ልጅን ሳሙ ኤል፣ ሁለተኛውንም ልጅ ብንያም፣ ሦስ ተኛውንም ልጅ ሀብተ መስቀል ብለው ሰይመዋል። /ገድለ ተክለ ሃይማኖት፣ ምዕራፍ 33፣ ገጽ 95/። ለአብነት ያህል እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት ጠቀስን እንጂ በሌሎችም መጻሕፍት ላይ ሌሎች ተመሳሳይ ታሪኮች ተጽፈው ይገኛሉ። ዛሬም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በዚህ መልኩ ስመ ክርስትና ይሰይማሉ።

## 2. የቅዱሳንን ስም ዘርፍ በማድረግ መሰየም፡-

የቅዱሳንን ስም ዘርፍ በማድረግ የሚሰየሙ የክርስትና ስሞች ሁለት ቃላት ሆነው በአንድ የተጣመሩና የሚ ናበቡ ናቸው። የመጀመሪያው ቃል ተጠ ማቂውን የሚገልጽ ሲሆን ሁለተኛው የእግዚአብሔርን፣ የድንግል ማርያምን፣ የቅዱሳን መላእክትንና የቅዱሳን ሰዎችን ስሞች ይገልጻሉ።

ዘርፎች /ቅጽሎች/ የሚባሉት፡- አመ ተ፣ አምኃ፣ በትረ፣ ብሥራተ፣ በጸሎተ፣ ገነተ፣ ገብረ፣ ወለተ፣ ወልደ፣ ከሣቴ፣ ኪ ዳነ፣ መንበረ፣ መዝገበ፣ ዐምደ፣ ነገደ፣ ፈቃደ፣ ብርሃነ፣ ትውክ ልተ፣ ማኅሌተ፣ ምሥጢረ፣ ኃይለ... ወ.ዘ.ተ ናቸው። እነ ዚህ ዘርፎች በስመ ቅዱሳን ላይ በመቀ ጸል እንደ የሁኔታው ለወንዶችም፣ ለሴ ቶችም መጠሪያነት ያገለግላሉ። የቅዱ ሳንን ስም ዘርፍ በማድረግ ሲሰየም የተ ወሰኑትን ለአብነት እንመለከታለን።

ሀ.ተጠማቂው በሚወለድበት ዕለት በሚውለው የእግዚአብሔር፣ የእመቤታ ችን፣ ወይም የቅዱሳን መታሰቢያ በዓል ስመ ክርስትናው ሲሰየም።

ለምሳሌ፡- ገብረ እግዚአብሔር፣ ገብረ ማርያም፣ አመተ ማርያም፣ ኃይለ ገብርኤል፣ ሥነ ጊዮርጊስ፣ ሥምረተ ሚካኤል፣ አስካለ ተክለ ሃይማኖት፣ አር አያ ዮሐንስ፣ በትረ መድኃኔ ዓለም፣ ብርሃነ መስቀል፣ በትረ ሥላሴ... ወ.ዘ.ተ ይባላል።

ለ. ክርስትና በሚነሣበት ዕለት በሚውለው የመታሰቢያ በዓል ሲሰየም።

ለምሳሌ፡- ወር በገባ በአንድ /የልደታ ለማርያም/ ዕለት ከሆነ ክርስትና የተነሣው፡- በትረ ማርያም፣ ወለተ ጽዮን፣ ዘውገ ማርያም፣ ገብረ ማርያም፣ ዐጸደ ማርያም፣ አምኃ ማር ያም፣ሥነ ማርያም፣ ሠርጸ ድንግል፣ ዐ ምደ ማርያም፣ታዕካ ለማርያም... ወዘተ ብሎ ካህኑ ይሰይማል።

• ወር በገባ በሰባት /የቅድስት ሥላሴ/ ዕለት ከሆነ፡- አምኃ ሥላሴ፣ አመተ ሥላሴ፣ ዐጸደ ሥላሴ፣ አስካለ ሥላሴ፣ ብርሃነ ሥላሴ፣ ገብረ ሥላሴ፣ ሀብተ ሥላሴ፣ ወለተ ሥላሴ፣ ኃይለ ሥላሴ፣ ጥበበ ሥላሴ፣ መንበረ ሥላሴ፣ ሣህለ ሥላሴ፣ ፍቅርተ ሥላሴ፣... ወዘተ ብሎ ካህኑ ይሰይማል።

•ወር በገባ በ12 /የቅዱስ ሚካኤል/ ዕ ለት ከሆነ፡- ኃይለ ሚካኤል፣ ትርሲተ ሚካኤል፣ ታቦተ ሚካኤል፣ ተድባበ ሚካ ኤል፣ ተስፋ ሚካኤል፣ ስርጉተ ሚካኤል፣ ሰዊተ ሚካኤል፣ ፍቅረ ሚካ ኤል...ወዘተ ብሎ ካህኑ ይሰይማል።

•ወር በገባ በ23 /የቅዱስ ጊዮርጊስ/ ዕ ለት ከሆነ፣ ካህኑ፡- ተክለ ጊዮ ርጊስ፣ ጸጋ ጊዮርጊስ፣ ሥነ ጊዮ ርጊስ፣ በረ ከተ ጊዮርጊስ፣ አስካለ ጊዮርጊስ፣ ገብረ ጊዮርጊስ... ወዘተ ብሎ ይሰይማል።

ሐ. ሕፃኑ በሚጠመቅበት ቤተ ክርስቲያን ስም፣ በስእለት፣ ወላጆቹ በሚመርጡት የቅዱሳን ስም በካህኑ ሙሉ ፈቃድ ይሰየማል።

ለምሳሌ፡- በቅዱሳን ስም ሊሆን ይችላል። ይህም፡- አርአያ ዮሐንስ፣ አመተ ጻድቅ፣ አምሳለ ጊዮርጊስ፣ ወለተ አረጋዊ፣ ወለተ ኤውስጣቴዎስ፣ ዘውገ እስጢፋኖስ፣ ዘር0 ያዕቆብ፣ ዝክረ ኪዳን፣ ዜና ማርቆስ ... ወዘተ ተብሎ ይሰየማል።

## 3. ሌሎች የስያሜ ሂደቶች፡-

ከላይ በዝርዝር ካየናቸው የክር ስትና ስም አሰያየሞች በተጨማሪ ሌሎ ች የክርስትና አሰያየም ዘይቤዎ ችም አሉ። ከእነዚህ ስያሜዎች አንዱ በወላ ጆች ጥያቄ የሚሰየመው ነው። እነዚህ ስሞችም በንዋያተ ቅድሳት፣ በነገረ ሃይ ማኖት ምሥጢራት... ወዘተ መሠረት ፀማድረግ የሚሰየሙ ናቸው። ዘርፋቸ ውም የተለየ ነው።

ለምሳሌ፡-ኢየሱሳዊት፣ዘአማኑኤል፣ ቀሱሳዊት፣ ክርስቶሳዊት፣ ምእመነ ድን ግል፣ ዕብነ ሰንበት፣ዘሚካኤል፣ዘማር ያም፣አቅሌሲያ፣አረጋዊ፣ዕዕሕይወት፣ዕፀ ገነት፣ ፊላታዎስ፣ ኒቆዲሞስ፣ ፍሬም ናጦስ፣ስለ ታቦት፣ ተአምረ ማርያም፣ ታኦሎጐስ...ወዘተ በማለት ካህኑ ይሰይ ማል። በዚህ መሠረት ቅድስት ቤተ ክር ስቲያን ሰዎችን እያጠመቀች የእግዚአ ብሔር ወገን ስታደርጋቸው ስመ ክርስ ትናቸውን በዚህ መልኩ በመሰየም ነው።

*በሚቀጥለው እትም*
*የማይገባ የስመ ክርስትና አሰያየም እና ስለ ክርስትና አባትና እናት ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን እናቀርባለን።*

# ቸልተኝነት...

*/ከገጽ ፳፰ የዞረ/*

የሚሰጠን እንደ ልባሙ አገልጋይ ቆላ ወርደን ደጋ ወጥተን የሚጠበቅብንን አደራ ተወጥተን ወደ ደስታው እንድ ንገባ ነው። ይህ ግን የሚቻለው ከሁሉ በፊት ቸልተኝነትን ከእኛ አርቀን ትጋ ትንና ቅንዓትን ገንዘብ ስናደርግ ብቻ ነው። ቸልተኝነት ከተጠናወተን ግን በኃጢአት ባሕር እየሰጠምን እንኳን÷ መልካሙን ያደረግን ያህል እንዲሰማንና ከንስሐ እንድንዘገይ ያደርገናል።

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ቸልተ ኝነት ርግማንን የሚያስከትል ኃጢአት ነው። ነቢዩ ኤርምያስ፡- «የእግዚአብሔ ርን ሥራ በቸልታ የሚያደርግ ርጉም ይሁን» ያለው ይህንኑ ያስረዳናል። ኤር. 48÷10። ለመሆኑ የእግዚአብሔር ሥራ የትኛው ነው? በየትኛውም መስክ ከኃጢ አት መመለስ፣ ሕዝብ የሚገለገልበት፣ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ሥራ አይ ደለምን? የኀሊናን ፍርድ ወደ ኋላ ጥሎ አለቃ ከሌለ፣ በግምገማ ካልተደ ረሰ ብን፣ ምእመናን ምሥጢራችንን ካላወቁ ብን መለገምስ ርግማንን የሚያስከትል ቸልታ አይደለምን?

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ስብከቱ ቸልተኝነ ትን አስወግደን የተጋን÷ ሓላፊነታች ንን በአግባቡ የተወጣን እንድንሆን «... ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛ ቸው እነዚያ ባርያዎች ብፁዓን ናቸው» በማለት አሳስቧል። ሉቃ.12÷37። ደግ ሞም ጌታችን ቸልተኞቹን እንዲህ አለ፡ - «...ያ ባርያ ግን ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ ሎሌዎ ችንና ገረዶችንም ይመታ÷ ይበላም÷ ይጠጣም÷ ይሰክርም ዘንድ ቢጀምር የዚ ያ ባርያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃ ትም ሰዓት ይመጣል። ከሁለትም ይሰነ ጥቀዋል። ዕድሉንም ከማይታመኑ ጋር ያደርጋል።» ሉቃ.12÷45-46። እርስዎስ?

ከእግዚአብሔር ፊት የተሰወረ ፍጥ ረት የለም። ከእርሱም እጅ የሚያ መልጥ የለም። በተሠማራንበት መስክ ሁሉ ሀገረ ስብከቱ፣ወረዳ ቤተ ክህነቱ ፣ ቄስ ገበዙ፣ ሊቀ ዲያቆኑ፣ አጋፋሪው፣ ዳኛው፣ አዲተሩ፣ ሥራ አስኪያጁ፣ ጥር ሶኔሉ፣ ፖሊሱ፣.... በአጠቃላይ አለቃው ቢያዩ ባያዩ የሚል÷ የሚያይ የሚያውቅ እንደ ዕውቀቱ በጊዜው ጊዜ የሚፈርድ እግዚአብሔር ቸልተኛም እንሁን ትጉ ኃን ያውቀናል። በመሆኑም ባለፈው ለነ በረው ቸልተኝነት ንስሐ ገብተን በቀ ረው ዘመን ለመትጋት የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን የድንግል ማር ያም አማላጅነት አይለየን። አሜን።



www.eotcmk.org

# የሥርዓት መፈጸሚያ መጻሕፍት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለልጆቿ የምትሰጣቸው አገልግሎቶች ወጥና ሥልጣነ ክህነትን ገንዘብ ያደረገ ማንኛውም አገልጋይ ያለምንም ችግር እየተመራ አገልግሎቱን ለመፈጸም የሚያስችሉት መሪ መጻሕፍት ናቸው:: ይህንንም ቀደም ሲል ማዘጋጀቷ «ስንዱ እመ ቤት» ከሚያሰኟት ነገሮች አንዱ ነው:: ነገር ግን ይኸንን ያላወቀ ወይም ቀረብ ብሎ በማየት ለማወቅና ለመረዳት ባልፈለጉ ሰዎች በቤተ ክርስቲያናችን የሚፈጸሙ ልዩ ልዩ ምሥጢራትና አገልግሎቶች በዘፈቀደ የሚፈጸሙ፤ እንደ ፈጻሚዎቹ ካህናት ዕውቀትና ችሎታም የሚለያዩ ይመስላቸዋል:: እነዚህ ሰዎች በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙትን ምሥጢራትም ሆነ አፈጻጸማቸውን ሰይጣናዊ ከሆነ ጭፍን አመለካከት ተላቀው ቀረብ ብለው እንዲያዩ፣ መጻሕፍቱንም ረብ እና ጥቅም ላለው ነገር ሊመረምሩ ይገባቸዋል:: ምእመናን ዕለት ዕለት ወደ እናት ቤተ ክርስቲያናቸው እየሄዱ የሚሳተፉባቸውን ምሥጢራትና ሥርዓቶች. መፈጸሚያና ማስፈጸሚያ የሆኑ መጻሕፍት ዝርዝርና ጠቅላላ ይዘት በማወቅ መጻሕፍቱን አንብበው እንደ ቤተ ክርስቲያን ትእዛዝ የድርሻቸውን ሱታፌ እንዲያደርጉ ከዚህ እትም ጀምሮ በአጭር በአጭሩ ማስተዋወቅ እንጀምራለን::

የሥርዓት መጻሕፍቱን ወደ ማስተዋወቅ ከመግባታችን በፊት አጠቃላይ ባሕርያቸውን በመጠኑ ለመዳሰስ እን ሞክር::

1.ምንጫቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው:- የቤተ ክርስቲያናችን አዋልድ መጻሕፍት አንዳንዶች እንደሚሉት ምንጫቸው የማይታወቅ የነሲብ ሥራዎች ሳይሆኑ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አባቶችን እያስነሣ ያጻፋቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው:: ያጻፋቸው እግዚአብሔር ነው ካልን ደግሞ ቃሉን በትርጓሜና በምሥጢር እያብራሩ የሚያጸኑና እንጂ የሚቃረኑ አይደሉም:: /2ጢሞ.3÷15–17/::

2. አሳታፊዎች ናቸው:- መጻሕፍቱ በቤተ ክርስቲያን የተደነገጉ ሥርዓቶች መፈጸሚያ በመሆናቸው ሥርዓቱን የሚፈጽሙትም ሆኑ የሚፈጸምላቸው አካላት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ናቸው:: ይህም «ዲያቆኑ ይህን ይበል፤ ካህኑ ይህን ይበል፤ ሕዝቡ ይህን ይበል» እያሉ በዝርዝር ያስቀምጣሉ::

3. የተውጣጡ /አዕውት/ ናቸው:- እነዚህ መጻሕፍት እርስ በርስ የሚደጋገፉ ሥርዓቶች መፈጸሚያ እንደ መሆናቸው በይዘቶቻቸውም አልፎ አልፎ ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል:: የሚያስፈጽሟቸውን ሥርዓቶች ምሉዕነት ለመግለጽም ሊቃውንቱ ከተለያዩ መጻሕፍት አውጥተዋቸዋል:: በመ ሆኑም ብዙዎቹ የሥርዓት መፈጸሚያ መጻሕፍት «አስተዋፅዖ» /የተውጣጡ ስብስቦች/ ናቸው ማለት ይቻላል:: ከዚህ ቀጥለን በቤተ ክርስቲያናችን ልዩ ልዩ ምሥጢራትና ሥርዓቶች ሲፈጸሙ በመሪነት አገልግሎት ላይ የሚውሉ መጻሕፍትን በዝርዝር እንቃኛለን::

*1. መጽሐፈ ቄድር*

1.1 ታሪክ

ይህ መጽሐፍ በ15ኛው መ.ክ.ዘ የደብረ ሊባኖስ ዕጨጌ በነበረው አባ ፊልጶስ በተባለ መነኩሴ እንደ ተዘጋጀ ይነገራል:: ለመዘጋጀቱም ታሪካዊ ምክንያት አለው:: እንደ ሚታወቀው በዚያ ወቅት በሀገራችን ቤተ ክርስቲያናችንን ክፉኛ የጎዳ፣ምእመናኑንም ከእምነታቸው እንዲሸሹ÷እንሸሽም ያሉትንም በሰይፍ እንዲቀሉ፣ በጦር እንዲወጉ፣ ከነቤተሰቦቻቸው በእሳት እንዲቃጠሉ ያደረገ አንድ ክስተት ተፈጥሮ ነበር- የግራኝ አሕመድ ወረራ::

ለ15 ዓመታት የዘለቀው ይህ ወረራ እግዚአብሔር ለሃይማኖታቸው ሲሉ በሰማዕትነት ያለፉትን ቅዱሳን ደም ጩኸትና የአምልኮት መፈጸሚያ የሆኑትን ንዋያተ ቅድሳት በመያዝ በስደት የነበሩትን ጸሎትና እንባ ተቀብሎ ወረራው በክርስቲያኖች የበላይነት ተጠናቀቀ:: ቤተ ክርስቲያናችንም በአምላክዋ ኃይል ጠላቷን ድል አድርጋ የቀደመ አገልግሎቷን ቀጠለች:: የአምልኮታችን መፈጸሚያና የማንነታችን መገለጫ ከሆኑ ንዋያተ ቅድሳታችን ጋር እዚሁ እንቀበራለን በማለት በየዋሻውና በየጥሻው የገቡ ልጆቿን መሰብሰብ ጀመረች:: እምነታችንን ቀይረናል ያሉትን ልጆቿንም «ኑ÷ ተመለሱ» ብላ እጇን ዘረጋች:: ምንም እንኳን የእናትነት ድምፅዋ በሁሉም ዘንድ ተሰምቶ በግዳጅ ማተባቸውን የበጠሱት ሁሉ ሊመጡ ባይችሉም በርካታዎች የእናታቸውን ድምፅ ሰምተው የዘረጋችላቸውን እጆቿን ያዙ::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዘመነ ዐፀባ በደረሰባቸው ችግር በአሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ልጆቿ መምጣት ተደስታ ወደ ዕቅፏ ለማስገባት፤ የተጻደፈ ሰውነታቸ ውን ቀድሳ የቀደመ ክብርና ጸጋቸውን ለመመለስ የሚያስችላትን ሥርዓት ሠራች:: ይኸውም «የቄድር ጥምቀት» ነው:: ይህም ጥምቀት የንስሓ ጥምቀት ነው:: ቤተ ክርስቲያን የምትፈጽመው ሥርዓት ሁሉ በዘፈቀደ ስለማይመራ፣ በፈጻሚው የግል ችሎታና ፍላጐትም የሚያጥርና የሚረዝም ባለመሆኑ ሰው አልፎ ሰው ቢተካ አገልግሎቱ ሂደቱን ጠብቆ እንዲጓዝ የሚያስችል በጽሑፍ ላይ የዋለ መፈጸሚያ መጽሐፍ እንዲዘጋጅ አዘዘች:: ሊቃውንቷ ተሰባስበው በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና ገላጭነት መጽሐፈ ቄድርን ጻፉ:: በደቀ መዝሙሩ ሥራ የመምህሩ ስም መጠራቱ የቆየ የቤተ ክርስቲያናችን አሠራር በመሆኑ መጽሐፈ ቄድርን ዕጨጌ ፊልጶስ እንደ ደረሰው ተደርጎ ይነገራል::

በ15ኛው መ.ክ.ዘ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ የተዘጋጀው ይህ የሥርዓት መፈጸሚያ መጽሐፍ ያኔ ከቤተ ክርስቲያናቸው ዕቅፍ ከሃይማኖታቸው ወጥተው የነበሩ በርካታ ወገኖቻችንን ወደ እናት ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲገቡ አድርጓል:: አገልግሎቱንም በመቀጠል እስከ ዛሬ ድረስ በመተዳደፍ ከቤተ ክርስቲያን ሕይወት ወጥተው የነበሩና ያሉ ምእመናን ወደ ቀደመች ቤታቸው እንዲመለሱ ማድረጊያ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል::

1.2 ይዘት

መጽሐፈ ቄድር እንደ በርካታዎቹ የቤተ ክርስቲያን አዋልድ መጻሕፍት ሁሉ በግእዝ ቋንቋ በብራና ላይ የተጻፈ ነው:: ምንም እንኳን አገልግሎቱ ከፍተኛ በመሆኑ መጽሐፉ ዘመናዊ የማተሚያ መሣሪያ ወደ ሀገራችን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት የመታተም ዕድል ቢገጥመውም እስከ አሁን ድረስ ወደ አማርኛ አልተተረጐመም::

መጽሐፉ እንደ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ በአዘጋጆቹ የመግቢያ ጸሎት አለው:: ይኸውም:- «በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ጽሒፈ መጽሐፈ ቀኖና ዘውእቱ መጽሐፈ ቄድር ወያብጽሐነ ለፈጽሞቱ አሜን::» በማለት ይጀምርና የመጽሐፉን ይዘትና ዓላማ በሚገልጸው ተከታዩ ምንባብ ይቀጥላል::

«ዘአንበሩ መምህራን /ከዚህ አባባል መጽሐፉ በጉባኤ መምህራን መዘጋጀቱን ልብ ይሏል/ በእንተ ዘክሕደ ሃይማኖቶ አው ዘአርኰሰ ሥጋሁ ምስለ ዘኢምእመናን አው ተባእት አው አንስት አው መነኰስ ሀያዲ ወሰራቂ ብእሴ ደም ወገፋዒ ላዌ ያስሐው ዘኢይደልዎ ለክርስቲያን...»

ከዚህ ምንባብ የምንረዳው:-ሴትም ትሁን ወንድ ከሃይማኖት መንገድ ወጥተው ከተገኙ፣በማይገባ ሥራ እግዚአብሔርን አሳዝነው ከታዩ የቄድር ጥምቀት እንደ ሚያስፈልጋቸው ነው:: በሊቃውንተ ቤተ ክርቲያን ከተዘጋጀ ጀምሮ ለዘመናት ሲያገለግል የቆየ የሥርዓት መፈጸሚያ መጽሐፍ ነው ስንልም በዚህ ምንባብ መመሪያነት ነው::

መጻሐፈ ቄድር የሥርዓት መፈጸሚያ መጽሐፍ እንደ መሆኑ ሥርዓተ ጥምቀቱ በሚፈጸመበት ጊዜ «ይበል ዲያቆን፣ ይበል ሕዝብ፣ይበል ካህን» በሚል የካህናቱም ሆነ የሕዝቡ ድርሻ በሚገባ በግልጽ ተቀምጧል:: ከመጽሐፉ ምንባባ ትም በርከት ያለውን

ወደ ገጽ ፴፰ ዞሯል





www.eotcmk.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ *መቋቋም *መስፋፋት *ወቅታዊ ችግር

/የመጨረሻ ክፍል/

*ባለፈው እትማችን በሰሜን አሜሪካ የተለያዩ ግዛቶች ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀው ከማዕከላዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር /ቅዱስ ሲኖዶስ/ በየጊዜው በሚወጣው መመሪያ እየተዳደሩ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት በአጭር በአጭሩ አስተዋውቀናል። በዚህኛው ዝግጅታችን ደግሞ በገባነው ቃል መሠረት በአካባቢው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሲገጥሟት የቆዩትንና እየገጠሟት ያሉትን ችግሮች እንዳስሳለን። በመጨረሻም ችግሮቹ ተቀርፈው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በተፋጠነ መልኩ እንዲቀጥል መፍትሔ የምንላቸውን አንዳንድ ነጥቦች እናቀርባለን።*

ረዘም ላሉ ዓመታት በሰሜን አሜሪካና አካባቢው በስደት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ዐቅፋ በመያዝ፣ ፈልገዋት የሚመጡትንም ወደ በረትዋ በማስገባት ስታገለግላቸው የቆየችዋ ቤተ ክርስቲያናችን እርሷ ልጆቿን ለማገልገል የመትጋቷን ያህል፣ ያንን የማይፈልገው ጥንተ ጠላቷ ሰይጣንም ይህን አገልግሎቷን ለማደናቀፍ እየተጋ በተለያዩ ችግሮች ሲፈትናት ቆይቷል። ዛሬም እየተፈታተናት ይገኛል።

በሰሜን አሜሪካና አካባቢው ቤተ ክርስቲያናችንን ሲያጋጥሟት የቆዩትንና እያጋጠሟት ያሉትን ችግሮች ውስጣዊና ውጫዊ በማለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን።

*1.ውስጣዊ ችግሮች*

ውስጣዊ የምንላቸው ችግሮች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ከቤተ ክርስቲያኗ የውስጥ አካላት የመጡ ችግሮችን ነው። እነዚህ ችግሮች ምንም እንኳን ውስጣዊ ቢሆኑም ዝቅ ብለን ከምናያቸው ውጫዊ ችግሮች ባልተናነሰ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንን ሲጐዷት ቆይተዋል፤ አሁንም በመጉዳት ላይ ይገኛሉ። በአጭር በአጭሩ እንደ ሚከተለው እንመለከታቸዋለን።

1.1 አስተዳደራዊ ልዩነት

ይህ ችግር በሰሜን አሜሪካ ላለው የቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት እንቅፋት ከሆኑ ውስጣዊ ችግሮች ዋነኛው ምናልባትም መሠረታዊ ሊባል የሚችል ነው። መሠረታዊ እንዲሆንና በቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት ላይ ግልጽ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲያሳድር የሚታየው ቤተ ክርስቲያኗ በአካባቢው በመስፋፋት ላይ በነበረችበት ጊዜ የመጣ ችግር በመሆኑ ነው።

ይህን ጽሑፍ በጀመርንበት እትም እንደ ገለጽነው በሰሜን አሜሪካና አካባቢው ቤተ ክርስቲያናችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመችው በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ ሰዎች ባሳዩት ፍላጐትና ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት በወቅቱ በነበረው የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ይሁንታና መልካም ፈቃድ ነው። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያኗ ከተቋቋመች በኋላ በተፈጠሩ የሚታወቁና የማይታወቁ ችግሮች የተነሣ ማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ለበርካታ ዓመታት በዚያ አካባቢ ላለው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ርዳታ አላደረገም ነበር። በዚህ የተነሣ የቤተ ክርስቲያናቸው አገልግሎት እንዲቀጥል ከፍተኛ ፍላጐት የነበራቸው የአካባቢው ምእመናን የቤተ ክርስቲያናቸውን አስተዳደር ሙሉ በሙሉ በራሳቸው እየሸፈኑ መገልገል ጀመሩ። አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ሲያቋቁሙም ሆነ የተ ቋቋሙትን ሲያስፋፉ ከካህናት ማፈላለግ ጀምሮ ያለውን እንቅስቃሴ በሙሉ የሚያከናውኑት ራሳቸው ነበሩ። ጥረታቸው ተሳክቶ አብያተ ክርስቲያናቱ ሲቋቋሙም የካህናቱንም ሆነ አጠቃላይ መንፈሳዊ አስተዳደሩን ሙሉ በሙሉ ራሳቸው ሲያከናውኑት ቆዩ። ምእመናኑን ይኸኛውን አካሄድ እንዲከተሉ የረዷቸው በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ማንም ቤተ ክርስቲያንን ለማቋቋም የፈለገ ተደራጅቶ የመጣ አካል በመንግሥቱ የተቀመጡትን መመዘኛዎች እስካሟላ ድረስ ቤተ ክርስቲያን የማቋቋም መብት የሚሰጥ ሀገር በመሆኑና በወቅቱ ቤተ ክርስቲያን በነበሩባት ችግሮች የተነሣ ውቅያኖስ አቋርጣ በአካባቢው የነበረውን አገልግሎት መምራት አለመቻሏ ነበር። በእርግጥ ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያን ደቡቡንም ሆነ ሰሜኑን የአሜሪካ ክፍል እንዲሁም ካናዳን የሚያጠቃልል ሀገረ ስብከት ብታቋቁምም የጽ/ቤቱ አጠቃላይ ድርጅት የተጠናከረ ስላልነበረ ተመድበው የሚሄዱት ሊቀ ጳጳስ በክህነት ሥልጣናቸው እንደ አንድ አባት በተጋበዙበት ቦታ ተገኝተው ከማገልገል ያለፈ የሀገረ ስብከቱን እንቅስቃሴ በመምራት ተገቢውን ቁጥር ለማድረግ አላስቻላቸውም።

ከላይ ባየነው አካሄድ የተጀመረው በሰሜን አሜሪካና አካባቢው የነበረው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጋር ያለመገናኘት ችግር ለዓመታት ባለበት ሲኼድ ከቆየ በኋላ በ1984 ዓ.ም ችግሩን ያገዘፈና ቀድሞ ያልተለያዩትን ምእመናን በጐራ ለይቶ አንጻር ለአንጻር ያቆመ ክስተት ተፈጠረ። ይኸውም ከቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ አስተዳደር ጋር ባለመስማማት የተወሰኑ አበው ሊቃነ ጳጳሳት ወደ አካባቢው መሔድ ነበር። በእነዚህ አባቶች መኼድ ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያኗ አገልግሎት የተጠናከረ ቢመስልም ቀደም ሲል የነበረውን አስተዳደራዊ ክፍተት የበለጠ እንዲሰፋ፣ በምእመኑ መካከል ያልነበረ መከፋፈልም በስፋት እንዲከሰት፣ በዚህም ዝቅ ብለን የምናነሣቸው ችግሮች እንዲፈጠሩ አድርጓል።

እንደ የደረጃቸው ቤተ ክርስቲያኗ በሰጠቻቸው ሥልጣንና መዓርግ ረዘም ላሉ ዓመታት አገልግሎት ሲፈጽሙ የቆዩት አበው ወደ አካባቢው መሄድ በመካከሉ የነበረውን አንድነት ጠብቆ የቆየውን ምእመን ለመከፋፈሉ ምክንያቱ ደግሞ የእነዚህ አባቶች "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ከእኛው ጋር ተሰዶ ወደ አሜሪካ መጥቷል" ብለው በይፋ ማወጃቸው ነበር።

ይህ የተሳሳተ ዐዋጅ፤ ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ በተነሣው የኢትዮጵያውያን በቋንቋና በጐሳ መለያየት ችግር ጋር ተዳምሮ በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ ቅድስት ቤተ ክርስቲያኑን የማንነቱ መገለጫ አድርጐ በሰላምና በፍቅር ይኖር የነበረውን ምእመን ወዳልተገባ ውዥንብርና መከፋፈል ከተተው። በዚህም መሠረት በአሁኑ ወቅት በዚያ አካባቢ የሚታዩ ክፍፍሎችን ሰፋ ሰፋ ባለ መልኩ በሦስት ምድብ ማስቀመጥ ይቻላል።

በመጀመሪያው ምድብ የሚቀመጡት ቅዱስ ሲኖዶስ እንደ ማይከፈል እንደ ማይሰደድም በማ



www.eotcmk.org

ወቅና በማመን በሀገረ ስብከቱ በኩል መንበረ ፓትርያርኩ ከሚገኝበት የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ጋር የሚገናኙት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው:: እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በስደት የሚኖረውን ምእመን በትምህርት እያጠነከሩ በምክር እየደገፉ የአካባቢውን አገልግሎት ይመራ ዘንድ ቤተ ክርስቲያኗ ካስቀመጠችው ሀገረ ስብከት መመሪያን እየተቀበሉ ይገኛሉ::

በሁለተኛው ምድብ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አንድ እንደ ሆነና መንበሩም በኢትዮጵያ ብቻ እንደ ሆነ የሚቀበሉ፣ ነገር ግን በሀገረ ስብከቱ የአስተዳደር መዋቅር የማይመሩ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው:: እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በአካባቢው አነጋገር "ገለልተኞዎች" ወይም "መሐል ሰፋሪዎች" ይባላሉ:: የሚመሩትም ከአንዳንዶች በስተቀር በ"ቦርድ" ነው:: በአብዛኛው በአስተዳደር ቦርድ ውስጥ የሚያገለግሉ አባላት አልፎ አልፎ የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ትውፊት ጠንቅቀው የማያውቁ ናቸው::

ለሚፈጸሙ አገልግሎቶችም ሆነ በአገልግሎት ሂደት ለሚፈጠሩ ችግሮች መመሪያ በመስጠትና በመሳሰሉት ሓላፊነቱን የሚወስዱት እነዚሁ በከፍተኛ የአስተዳደር ደረጃ የተቀመጡት ምእመናን በመሆኑ መናፍቃን የተሳሳተ ትምህርታቸውን ለማሥረጽ መንገድ ሲያገኙ ይታያሉ::

በሦስተኛው ምድብ የሚካተቱት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚገኘው በስደት በሰሜን አሜሪካ መሆኑን የሚቀበሉና አስተዳደራዊ ግንኙነታቸውን ሙሉ በሙሉ ከዚያ ጋር ያደረጉ ናቸው:: እንደ ሚሰማውና እንደ ሚታየው እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት መናፍቃን የለየለትን አስተዳደራዊ ክፍተት ተጠቅመው ሥራቸውን የሚሠሩባቸው ናቸው:: እዚህ ሀገር ቤት በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በኑፋቄያቸው ተወግዘው የተለዩ በስም የሚታወቁ መናፍቃን ሰፊ ቦታ ተሰጥቷቸው የሚንቀሳቀሱባቸው ናቸው:: የእንቅስቃሴያቸው መገለጫዎች የሆኑ አንዳንድ ክስተቶችም እየታዩ ነው:: ከነጫማ ወደ ቤተ መቅደስ መግባትና በኦርጋን መዘመር በምሳሌነት ሊቀርቡ ከሚችሉት ክስተቶች ዋነኞቹ ናቸው::

1.2. በዘር መከፋፈል:- ኢትዮጵያውያን በየትኛውም የዓለም አካባቢ የሚታወቁበት ጠባያቸው ኢትዮጵያዊ መልካቸውን /እምነት፣ ባሕልና ታሪክ/ ጠብቀው፤ በአንድነታቸው ጸንተው ለሌላው የዓለም ሕዝብ አርአያ ሆነው መኖራቸው ነበር:: ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ምንም እንኳን ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ባያጠቃልልም ጥቂት የማይባሉት በተወለዱበት አካባቢና በሚናገሩት ቋንቋ እየተከፋፈሉ ይታያሉ:: ይኸው በኢትዮጵያውያን ሁሉ የመጣው በሽታ በሰሜን አሜሪካና አካባቢው የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንንም አጥቅቶ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል መጠነኛ ክፍፍል እንዲታይ ምክንያት ሆኗል::

ይኸው የምእመናኑ ክፍፍል ካህናቱንም ከፋፍሎ የዚህ አካባቢ ቄስ፣ የዚህኛው አካባቢ መነኰሴ እየተባለ በቤተ ክርስቲያ ሁሉን ዐቀፍ አገልግሎት ላይ ችግር እየፈጠረ ይገኛል::

1.3 የጥቅም ግጭት:- ይኸኛው ደግሞ በሦስተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችል ውስጣዊ የቤተ ክርስቲያናችን ችግር ነው:: በአውሮፓና በሌሎች አህጉራት የአገልጋይ ካህናት እጥረት የቤተ ክርስቲያናችንን አገልግሎት ክፉኛ እየተፈታተነው የመገኘቱን ያህል በሰሜን አሜሪካና አካባቢው በርካታ ካህናት ይገኛሉ:: የእነዚህ ካህናት የገቢ ምንጭ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ምእመናን ናቸው:: በመሆኑም ከላይ በቁጥር /1.2/ ከገለጽነው ችግር ጋር ተያይዞ በአገልጋይ ካህናቱ መካከል አልፎ አልፎ የጥቅም ግጭት ይታያል:: ይህ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት እንቅፋት ሆኗል::

ከላይ ያየናቸው ችግሮች ምንም እንኳን ውስጣዊ ተብለው ቢፈረጁም በአካባቢው ላለው የቤተ ክርስቲያናችን እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደሩ ናቸው::

2.ውጫዊ ችግሮች

ውጫዊ የምንላቸው ችግሮች ከቤተ ክርስቲያኗ አካላት ውጭ የሚመጡና በአጠቃላይ አገልግሎቱ ላይ ችግር ሲፈጥሩ የሚታዩት ናቸው:: በዚህ ሥር ሊጠቀሱ የሚችሉ ችግሮችን እንደ ሚከተለው በአጭር በአጭሩ እንመለከታለን::

*የመናፍቃን ስውር ጥቃት:-*

መናፍቃን በተገኘችው ክፍተት ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው መርዛቸውን የመርጨት የቆየ አካሔድ አላቸው:: ዛሬም በሰሜን አሜሪካ መናፍቃን እያደረጉት ያለው ይኸንኑ ነው:: ከላይ በዝርዝር ባየናቸው ውስጣዊ ችግሮች የተነሣ በተፈጠሩ ክፍተቶች በመግባት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት በማወክ፣ ምእመናንን በማደናበር ሊነጥቁ ሲሞክሩ ይታያሉ:: የእነዚህ መናፍቃን እንቅስቃሴ ስውር መባል "እኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ነን፤ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተኮትኩተን አድገን ዛሬም ልናገለግላት ቆርጠን የተነሣን ነን" እያሉ በለሰለሰ አንደበት የምእመኑን ትኩረት በመሳብ ቤተ ክርስቲያንን በኑፋቄያቸው እያጠቁ በመሆናቸው ነው::

በዚህ መስመር የተሠማሩ መናፍቃን በብዛት እዚህ ሀገር ቤት በቤተ ክርስቲያን ላይ ተመሳሳይ ጥቃት ለመሰንዘር ሲሞክሩ በምእመኑ ጥቆማ ቤተ ክርስቲያን የነቃችባቸው እና ያወገዘቻቸው ሰዎች ናቸው:: እነዚህ መናፍቃን እዚህ ለይቶላቸው በመናፍቃን አዳራሽ በ«ፓስተርነት» ቆመው ሲጮኹ የነበሩ፤ በውጭ «የቤተ ክርስቲያን ልጆች ነን» እያሉ በቤታቸው መናፍቃን የሚጠናከሩበትንና ቤተ ክርስቲያናችን የምትዳከምበትን ሰይጣናዊ ሤራ ሲያሤሩ የነበሩ ናቸው:: ያሰቡት ሁሉ እዚህ አልሳካላቸው ሲል ዓላማችንን ከግቡ እናደርስበታለን» ወዳሉት አሜሪካ ተሻግረው «የዚህ አካባቢ ሰዎች በመሆናችን ተለየን፣ አስተዳደሩን በመቃወማችን ተወገዝን ወዘተ...» እያሉ በአስተዳደር የተለያዩትን አባቶች ይሁንታ እያገኙ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ይታያሉ::

መናፍቃኑ ምንም እንኳን ለምእመናን በማይታወቅ ሁኔታ መርዛቸውን መርጨታቸውን ባያቆሙም፤ ለጊዜው ያለው አስተዳደራዊ ልዩነት የበለጠ እንዲሰፋ፣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደኅንነት በሚችሉት መንገድ ሁሉ እየታገሉ ያሉ ቁርጠኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ጥረታቸው እንዲገታ የውስጥ ጠላት እንዲነሣባቸው በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

እንደ ሚታወቀው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መንፈስ ቅዱስ እየሳበ ልጆቿን ወደ ቅጽሯ ስለሚያስገባ ከትላንት እስከ ዛሬ ዐውደ ምሕረቷ ሞልቶ ሲትረፈረፍ ይታያል:: በዓለም ዙሪያ የመናፍቃኑ አዳራሽ ሰው ተርቦ ተዘግቶ እየዋለና እያደረ፤ ከዚያም አልፎ ወደ ሌላ ዓለማዊ አገልግሎት መስጫነት እየተቀየሩ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዐውደ ምሕረቶች በልጆቿ ተሞልተው ይውላሉ፤ ያድራሉም:: ይህ ደግሞ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መሥራቿ ክርስቶስ እንደ ሆነ በግልጽ ይመሰክራል::

ታድያ ልዩ ልዩ ፖለቲካዊ አመለካከት ያላቸው አካላት አስተሳሰባቸውን ወደ ሕዝቡ ለማሥረጽ ሲፈልጉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ:: ከመጡም በኋላ ባላቸው ተሰሚነትና አንጋፋነት በመጠቀም በአብያተ ክርስቲያናቱ አስተዳደር ይገባሉ:: በመሆኑም የአብያተ ክርስቲያናትን መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች በሚመሩ የአስተዳደር ቦርዶች የእነዚህ ዓይነት ሰዎች መኖር በሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ችግር ሲፈጥር ይታያል:: ምናልባትም ለምእመናኑ መለያየት እንደ አንድ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል::

ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያናችን ከላይ በመጠኑ ከዳሰስናቸው ችግሮች ሙሉ በሙሉ ተላቃ ልጆቿ በመጨረሻው ቀን ከአምላካቸው ቀኝ ቆመው የመንግሥቱ ወራሾች እንዲሆኑ የማዘጋጀት ሓላፊነቷን በሚገባ እንድ ትወጣ ሁሉም የቤተ ክርስቲያኗ አካላት ሰፊ



www.eotcmk.org

ድርሻ አላቸው:: በዚህ ረገድ የሚከተሉት አካላት የመፍትሔው ዋነኛ ባለቤት ናቸው ብለን እና ምናለን::

*1.የአባቶች ድርሻ፡-*

በዚህ ሥር በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ወደዚያ ተሻግረው እናት ቤተ ክርስቲያናቸው በዕውቀት መንፈሳዊ ተንከባክባ በማሳደግ በሰጠቻቸው ሰማያዊ ሥልጣን የሚያገለግሉ አባቶችና መምህራን ይጠቃለላሉ:: እነዚህ አባቶችና ወንድሞች የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከፍ ሲል የጠቀስነውን ሓላፊነቷን ትወጣ ዘንድ ምእመናንን በማሰለፍና አንድነታቸውን በመጠበቅ የመምራቱንና የማዝመቱን ድርሻ የሚወስዱ ናቸው:: በመሆኑም ከፍ ሲል ያየናቸው ችግሮች ተቀርፈው በስደት የሚኖረው ምእመን ኢትዮጵያዊ ማንነቱን ሳይቀይር የዘላለም ሕይወት ወራሽ ይሆን ዘንድ ከፍተኛ ሓላፊነት አለባቸው:: በአሜሪካና አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ይህንም ለማድረግ በሁለት መንገዶች ሊሄዱ ይገባል::

የመጀመሪያው ውይይት ነው:: በአገልግሎት ጉዞ እርስ በርስ መጋጨት ያለና ሁል ጊዜም ለበጐ እንደ ሆነ በማወቅ ያጋጠሟቸውንም ሆነ እያጋጠሟቸው ባሉ አለመግባባቶች ዙሪያ ጊዜ ሳይሰጡ በጋራ መወያየት አለባቸው:: ይህ አካሄድ ደግሞ ዛሬ እነርሱ የሚጀምሩት ሳይሆን በእምነታቸው ጽናት በዕውቀታቸው ስፋት ቤተ ክርስቲያናችንን ከዓላውያንና ከመናፍቃን ጠብቀው ያቆዩን አባቶቻችን ሲጠቀሙበት የቆዩትና ውጤታማ የሆኑበት መንፈሳዊ አካሄድ ነው:: ምናልባት እንደ ዕለታዊ ሥራ ቆጥረነው ካልሆነ በየዕለቱ በምእመናን ፊት ቆመን የምናስተምረው ቃለ እግዚአብሔር የሚነግረን ይኸንኑ ነው::

· በመሆኑም እነዚህ አባቶቻችን ከመለያየት አንድነትን፣ ከመከራከር መስማማትን፣ እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሁላችንም እግዚአብሔርን በድለናል ÷ አጥፍተናል» በማለት ወደ ዕርቅና መስማማት መጥተው የሰላም ድምፅ ለምእመኑ ማሰማት አለባቸው:: ይህ ደግሞ ሌላ አካል የሚመክራቸው ሳይሆን ራሳቸው ጊዜ ሳይወስዱ ሊያደርጉት የሚገባቸው የውዴታ ግዴታቸው ነው::

እነዚህ አባቶች በጸሎታቸው ሀገርንና ሕዝብን እንዲጠብቁ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ገብተዋል:: በመሆኑም በመካከላቸው የተፈጠረው ችግር ተቀርፎ ቤተ ክርስቲያን አንድነቷን ጠብቃ እንድትጓዝ የሰላሙን አምላክ በመሪር እንባ ሊለምኑት ይገባል:: እነርሱ በሚፈጽሟቸው ምስጢራት ምእመናን የበረከቱ ተካፋዮች ይሆኑ ዘንድ ከምንም በላይ ልቡናቸውን ከመጥፎ ነገር ሁሉ ነጻ ሊያደርጉ ይገባል:: እግዚአብሔር ልቡናን አንጽቶ የሚያቀርቡለትን መሥዋዕት ይቀበላልና:: ከዚህም በተጨማሪ ወደ ጋራ ስምምነትና አንድነት ለመምጣት እንዲያስችላቸው መጀመሪያ በተናጠል ሊወያዩና በግል ስምምነታቸውን ሊያጸኑ ይገባል:: ለብዙኃኑ መለያየት የእያንዳንዳችን መለያየት መሠረት ነውና::

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ምእመኑን ማስተማር ነው:: በእርሱ መለያየት የተነሣ እርስ በርስ የተለያዩ ምእመናን አንድ ይሆኑ ዘንድ ማስተማር አለባቸው:: ኢትዮጵያውያን በዓለም ዘንድ ከሚታወቁባቸውና ከሚደነቁባቸው ጠባያቸው አንዱ የሃይማኖት አባቶቻቸው የሚነግሯቸውን ሰምተው ተግባራዊ ማድረጋቸው ነው:: ስለዚህ ከዘመድ ወገኖቹ ርቆ በባዕድ ሀገር በባይተዋርነት የሚገኘውን ምእመን በትምህርታቸውና በምክራቸው ከገባበት ውዥንብርና መደናገጥ ሊታደጉት ይገባል::

*2. የምእመናን ድርሻ፡-*

በዚህ ሥር ደግሞ ከላይ በዝርዝር ያየናቸው ችግሮች ተጠቂ የሆኑት በአካባቢው የሚገኙት ምእመናን ይካተታሉ:: በዚህ ጽሑፍ መግቢያ አካባቢ በተደጋጋሚ እንደ ተገለጠው በሰሜን አሜሪካና አካባቢው የሚገኙ ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን በጥረታቸውና በትጋታቸው ከመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ ምንም እንኳን ከማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ጋር የነበራቸው ግንኙነት የላላ ቢሆንም፤ አንድነታቸውን ጠብቀው በፍቅርና በስምምነት ይኖሩ ነበር:: ነገር ግን ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ በተፈጠሩት አንዳንድ ክስተቶች የተነሣ እርስ በርስ እንደ ተለያዩና የየራሳቸውን መንገድ እየተከተሉ እንደ ሆነ ይሰማል::

"ቤተ ክርስቲያን" የሚለውን ቃል በአንድ ዘርፉ "የምእመናን አንድነት /ኅብረት/" ማለት ነው:: በመሆኑም ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን መጠናከር የምእመናን አንድነት /ኅብረት/ ያስፈልጋል:: እግዚአብሔር ዕድሜ ሰጥቶን በቤተ ክርስቲያን የትኛውም አገልግሎት የምንሳተፍ ማንኛችንም የእግዚአብሔር ልጆች በአገልግሎት ጉዞአችን ሁሉ ስለ እኛ ደህንነትና አንድነት ራሱን በመስቀል ላይ ቤዛ አድርጐ የሰጠውን መድኃኔ ዓለምን ልናስብ ይገባል:: ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ነፍሱን ቤዛ አድርጐ ሲሰጠን የሰበከልን አንድነትን ነው:: ፍቅርን ነው:: መተሳሰብን ነው:: በመሆኑም በእርሱ አምነንና ተጠምቀን ክርስቲያኖች የተባልን ሁሉ የፍቅር ሰዎች፣ የሰላም አብሣሪዎች ልንሆን ይገባል::

በምንም ዓይነት መመዘኛ ብንመለከተው በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሥር ያሉ ምእመናን መለያየት ጥንተ ጠላታቸውን ዲያብሎስን ከማስደሰትና ከማገልገል ውጭ በነፍሳቸውም ይሁን በሥጋቸው የሚያገኙት ጥቅም የለም:: ይልቁንስ እነርሱ እያዘኑ ቤተ ክርስቲያናቸውን ያሳዝናሉ:: የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውንና ለፍቅርና ለሰላም ሲል ራሱን ቤዛ አድርጐ የሰጠውን ክርስቶስን ያሳዝናሉ:: ስለዚህ በሰሜን አሜሪካና አካባቢው የሚገኙ ምእመናን እናት ቤተ ክርስቲያናቸው አሉበት ድረስ ተከትላቸው የሄደችው እንዲለያዩ ሳይሆን አንድ እንዲሆኑ፤ እንዲጣሉ ሳይሆን እንዲፋቀሩ መሆኑን ተገንዝበው በመካከላቸው ያለውን መቃቃር ሁሉ በውይይት ፈትተው አንድነታቸውን ሊያውጁ ይገባል::

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ይህንን ችግር ያመጣ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የማይወደው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ መሆኑን ተገንዝበው የቀደሙ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው እንዳደረጉት ሁሉ በግልም ሆነ በማኅበር በመሪር እንባ እግዚአብሔርን ሊጠይቁት ይገባል::

*3.የሰንበት ት/ቤቶች ድርሻ፡-*

"በአባቶችሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ" የሚለው ትንቢት ዛሬም ይፈጸም ዘንድ ፈቃዱ የሆነው እግዚአብሔር በቸርነቱ በሀገር ቤት ካለው የተጠናከረ የወጣቱ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ባሻገር ኢትዮጵያዊ መልካቸውን ባልቀየሩ ወጣቶች በባሕር ማዶም ተጠናክሮ እንደሚገኝ ይሰማል፤ ይታያልም:: በተለያዩ ጊዜያት እንደ ሚገለጠው፣ በተግባርም እንደ ሚታየው ይህ የወጣቱ በቤተ ክርስቲያኑ ዐጸድ ሥር መሰባሰብ ቤተ ክርስቲያን ከልዩ ልዩ ፈተናዎች እንድትጠበቅ፣ የነበራት ክብር ተጠብቆም ቀጣዩ ትውልድ እንዲረከባት ያደርጋል:: በመሆኑም ይህ ሐቅ በባሕር ማዶም እውን ይሆን ዘንድ በሰሜን አሜሪካና አካባቢው የሚገኙ ወጣት በአካባቢያቸው የቤተ ክርስቲያን ችግር ምን እንደ ሆነ በመረዳት ለመፍትሔው ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ምናልባትም በልዩነቱ መንገድ ተሠማርተው ያሉ ካሉ ስሕተታቸውን ፈጥነው በማረም የራሳቸውን ልዩነት በውይይት በማጥበብ ለአጠቃላይ የምእመናን አንድነት መታገል አለባቸው:: ተለያይቶ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል አባቶቻችን ያቆዩልን የአገልግሎት መንገድ አይደለምና::

የመፍትሔ ሐሳባችንን ከማጠቃለላችን በፊት በአካባቢው የተፈጠረውን ክፍተት ተጠቅመው የቤተ ክርስቲያንን ልጆች ለመንጠቅ በተኩላነት የተሠማሩ መናፍቃን የቆሙበት መንገድም ሆነ የያዙት ዓላማ የተሳሳተ መሆኑን ተገንዝበው ፈጥነው ከጥፋት ተግባራቸው በንስሓ ሊመለሱ ይገባል::

ከዚህ ጋር ባለፉት ሦስት ተከታታይ እትሞቻችን በሰሜን አሜሪካ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን የምሥረታና የዕድገት ታሪክ እንዲሁም ዛሬ ያለችበትን ሁኔታ ዳሰናል:: በመጀመሪያው እትም እንደ ገለጽነው የዚህ ዝግጅት ዓላማ ምእመናን በሰሜን አሜሪካ ያለው የቤተ ክርስቲያናችን እንቅስቃሴ ምን እንደ ሚመስል እንዲያውቁ፣ በአገልግሎት ሂደትም ያጋጠሟትንና እያጋጠሟት ያሉትን ችግሮች ተገንዝበው በሚችሉት መንገድ ሁሉ ለመፍትሔው ጥረት እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው::

ከእኛ በኩል ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ በመግለጽ ሁላችንም ድርሻችንን እንድናውቅ ያደረግን ይመስለናል:: ለችግሩ መቃለል የቀረቡት የመፍትሔ እርምጃዎች እንዳሉ ሆነው ይህንን ጽሑፍ ያነበብን በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ያለን አባቶችና ምእመናን በሙሉ ቤተ ክርስቲያናችን በአንድነቷ ጸንታ በውጭው ዓለም ያላትን ሐዋርያዊ አገልግሎት በትጋት ማበርከቷን እንድትቀጥል የበኩላችንን ጥረት እንድናደርግ አደራ እንላለን:: አምላከ አበው የቤተ ክርስቲያናችንን አንድነት ጠብቆ ያጽናልን:: አሜን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.eotcmk.org

# ኢያያዥ /CONJUNCTION/

ሀ. ወ - እና /And, As well as/ ዲ/ን ደሳለኝ ቀለብ

ለ. አው-ወይም /አ/ /or, either/

ወሚመ /ወይምና ወይስ /Or, Or else, either /

ሐ. ዳዕሙ፣አላ፣ ባሕቱ -ነገር ግን /But however.../

1 ወ=እና፣ም::

ወ በፊደልነትም ያገለግላል:: አጫፋሪ፣ከፋይ...ነው::

ሀ. ሁለት ስሞችን ሲያያይዝ ወ = ና ይሆናል::

ማርያም ወማርታ - ማርያምና ማርታ- Martha and Mary

አዳም ወሔዋን -አዳምና ሔዋን - Adam and Eve

ኢትዮጵያ ወግብፅ -ኢትዮጵያና ግብፅ - Ethiopia and Egypt

ለ.ሦስት ስሞችን ሲያያዝ - ወ፣ አች.... ም/As well as /

አብርሃም ወ ያዕቆብ ወይስሐቅ - አብርሃም እና ያዕቆብ ይስሐቅም /Abraham and Jaob as well as Isaac/

ሐ. በሁለት ግሶች =ወ =ም /And /

በልዐ ወሰትየ - በላ ጠጣም - eat and drank

2. ወ=ጠቅላይ

ጠቅላይ ስንል ስሞችን በአንድ ላይ ሲገልፅ ነው::

ምሳሌ:- በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም

In the Name of the Father and of the Son and of the Holy Spirit

3. ወ = ቦዝ

በዚህ ጊዜ ወ ከመጀመሪያው ግስ ጋር ይፈታል::

ነደገ - ተወ

ቸልታ - ውነደገ ግብሮ - ሥራውን ትቶ

ዘተረሰዐ- ሐመ ወሞተ-ታሞ ሞተ

መጽአ ወሖረ - ሐመ ወሞተ - ታሞ ሞተ

4. ወ = ውጥን ጨራሽ:: ማለት አንድ ግስ በወ የተያያዙ ስሞችን በአንድ ጊዜ በእኩል ሊያገለግል ይችላል::

ተሰቅለ ጴጥሮስ ወከማሁ እንድርያስ

ሰማይ ወምድር የኃልፍ

5. ወ = ከ ፣ ና /በቁጥር ጊዜ/

ዐሠርቱ ወአርባዕቱ-ዐሥር ከዐራት፣ዐሥርና ዐራት፣ዐሥራ ዐራት

6. ወ = በ.................ጊዜ /በቦዝ አንቀጽ ጊዜ/

ጸብሐ - ነጋ

ወጸቢሖ = በነጋ ጊዜ

7.. ወ = ስንኳ /ከአሉት ጋር = ከኢ ጋር /

ኢወሀበ ርስተ ወኢመጠነ ምክያደ እግር

ርስትን አልሰጠም፣ የእግር መረገጫ ያህል እንኳን

8. ወ = ግን፣እንጂ /ከ ኢ ጋር/

ከብረ ማትያስ ወኢከበረ ይሁዳ

ማትያስ ከበረ ይሁዳ ግን አልከበረም

ማትያስ እንጂ ይሁዳ አልከበረም

በልዐ ወኢሰትየ - በላ እንጂ አልጠጣም

9. ወ = ፍጹም:: ሁለት ግሶች ተመሳሳይ ሆነው በወ ሲያያዙ ወ የነገሩን መጠንከር /ፍጹምነት/ ያመለክታል::

ተሰብአ - ሰው ሆነ::

ተሠገወ - ሰው ሆነ

ተሰብአ ወተሠገወ /ፈጽሞ ሰው ሆነ/ በተዋሕዶ

10. ወ = አዳማቂ:: አዳማቂ በቃል ላይ ላይ እየተጨመረ ለቃሉ /ለቃላቱ/ ውበትን ከማላበስ ወይም ከማድመቅ በስተቀር ትርጉሙን አይለውጠውም::

ሰምአ - ሰማ ነገረ - ተናገረ

ስም «አኒወእንግርከ - ስማኝ ልንገርህ

ወ = ሂ፣ኒ፣ዓዲ/ እና፣ም፣ገና/

ወ = ና፣ም፣ውጥን፣ግን፣ስንኳ፣ሰ፣ለ፣ላ፣ለ፣ል፣በ፣ ባ፣ሰ፣ ሳ፣የ፣እንደ፣እንጂ፣ማ፣ጋራ፣ጊዜ፣ ሳ፣በኋላ፣ዘተረሰዓ፣ቸልታ፣ አኃዝ ጠቅላይ፣ፈጽሞ::

አጠቃላይ ወ=ሃያ ሰባት ትርጉምን እንደአገባቡ ይሰጠናል::

ለ. አወ = ወይ /ወይም/

አመተ ማርያም አው ገ/ማርያም፣ አመተ ማርያም ወይም ገብረ ማርያም

አንበሳ ወሚመ ከራድዮን- አንበሳ ወይስ ከራድዮን

ሚመ ብዙውን ጊዜ ወይስ የሚለውን ትርጉም የሚያዝና ጥያቄን የሚያመለክት ነው:: አው፣ዩጊ

፣ሚመ፣አመ፣አኮ፣ሰቦ ወይ/ወይም የሚለውን ትርጉም እንደ አገባባቸው ሊያስገኙ ይችላሉ::

ሐ. ዳዕሙ፣አላ፣ባሕቱ-ነገር ግን /But however/

በውጤት አመልካች ተውሳከ ግስ ጊዜ ተመልክተናል::

ሌሎች :- ክልኤሆሙ /ሆን -ሁለታቸው

በአሉታ = ኢ...ወ/ኢ ዳዊት- ኢ.ሰሎሞን ወኢ. ዳዊት

ምልማድ /መልመጃ/

ወልጥ ኀበ ልሳነ ግእዝ

1. ማርታ፣ማርያም እና ሰሎሜ ወደ ዮርዳኖስ ሄዱ
2. በሚካኤል፣በገብርኤል እና በሩፋኤል ቀን
3. ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተሰደደ ቤቱንም ተወ::
4. አሥራ አራት ዓመቴ ነው::
5. ጳውሎስ ከበረ:: ዴማስ ግን አልከበረም
6. ዘፋኝ ወይስ ዘማሪ
7. አንበሳ ወይስ ከራድዮን
8. አምላክ ሆይሚ ማረ እንጂ
9. ዓለማዊ ወይስ መንፈሳዊ
10. ሰማያዊ ወይስ ምድራዊ
11. አመነ እንጂ አልፈራም
12. ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም::

ውድ አንባብያን ዲያቆን ደሰላኝ በሚቀጥለው እትም ስለ እርባ ቅምር በሰፊው ያቀርብልናል:: ጠብቁት::

---

## የሥርዓት መፈጸሚያ...

/ከገጽ ፲፮ የዞረ/

ገጽ የሚይዙ ከመዝሙረ ዳዊት የተውጣጡ ምንባባት ይገኛሉ:: ከዚህ በኋላ ካህኑ እጁን በተጠማቂው ራስ ላይ ጭኖ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔርን ኅቡእ ስሞች እየጠራ የሚጸልየው አጭር የጸሎት ምንባብ ይገባል::

ከዚያም የመጀመሪያዪቱ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ ሰዎች ምዕራፍ 1 ከቁ ጥር 3-17፣ የመጀመሪያዪቱ የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት ምዕራፍ 5 ከቁጥር 5- 9፣ ይገባሉ:: ከዚያም ወደ መዝሙረ ዳዊት ይመለሳል:: በማስከተልም ጸሎተ ሐና እመ ሳሙኤል ምዕራፍ አ ራትን ይቀርባል÷ ዲያቆኑ ከመዝሙር 66 ይሰብካል:: ከዚያም ካህኑ ጸሎተ ወን ጌል አድርሶ አራቱንም ወንጌላት በየተራ /ማርቆስ፣ማቴዎስ፣ሉቃስ፣ዮሐንስ/ ያነባል:: ለመጨረሻም ቀጥሎ ካህኑ ውኃውን ባርኮ ልዩ ልዩ ጸሎቶችን ካደረሰ በኋላ ተነሳሒውን ያጠምቀዋል:: የተለያዩ የአካል ክፍሎቹ ንም ቅብዐ ቅዱስ ይቀባዋል::

ከዚህ መጽሐፍ ይዘት የምንረዳው የቤተ ክርስቲያን አዋልድ መጻሕፍት ከመነሻቸው ጀምሮ እስከ መድረሻቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ግንኙነት ያላቸውና የተለያዩ ክፍሎቹንም በአርእስትነት የያዘ ነው:: የዚህ መጽሐፍ ይዘትም የሚመሰክርልን ይኸንኑ ነው::

ስለዚህ በየአጥቢያችን መንፈሳውያት ምሥጢራትን የምንሳተፍ ምእመናን÷ይህ መጽሐፍ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር በተለየን ጊዜ በንስሐ ስን መለስ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርገንን ጸሎት የያዘ መሆኑን ዐውቀን ተጠቃሚዎች መሆን ይኖርብናል:: በሚቀጥለው እትም በሌላ የሥርዓት መፈጸሚያ መጽሐፍ እንጠብቃችኋለን:: ይቆየን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



www.eotcmk.org

# «በእውነቱ ለጥንታውያኑ መዛግብቶቻችን ባይተዋሮች ነበርን ማለት ይቻላል»

*ዶክተር ሞገስ ይገዙ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሥነ ልሳን ትምህርት ክፍል ሓላፊ*



*ዶክተር ሞገስ ይገዙ በሥነ ልሳን የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል። የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ደግሞ ቤልጅየም ከሚገኘው የብራስልስ ዩኒቨርስቲ ተቀብለዋል። ድኅረ ዶክትሬታቸውንም* (Post – Doctoral Research) *በዚያው ዩኒቨርስቲ ለአንድ ዓመት ያህል ተከታትለዋል። በአሁኑ ወቅት ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሥነ ልሳን ትምህርት ክፍል ሓላፊ በመሆን ያገለግላሉ። እርሳቸው በሓላፊነት የሚመሩት ትምህርት ክፍል በዚህ ዓመት በሀገራችን የመጀመሪያ የሆነውን «የጥንታዊ ጽሑፎች ጥናት»* (Philology) *በድኅረ ምረቃ ደረጃ ከፍቶ ተማሪዎችን ተቀብሎ በማሠልጠን ላይ ይገኛል። ስለ ሀገራችን ጥንታውያን ጽሑፎች ሲነሣ ጥንታዊው ቋንቋችን ግእዝ በግንባር ቀደምነት ይነሣል። በመሆኑም የጥናት መርሐ ግብሩ መከፈት በአንድም ኾነ በሌላ መንገድ ለግእዝ ቋንቋችን ማንሠራራት፣ ቋንቋው ሰንዷቸው ለሚገኙ በርካታ ጥንታውያን መዛግብት መዳሰስ በር ይከፍታል ብለን እንገምታለን። በመሆኑም በተከፈተው የጥናት መርሐ ግብር ዙሪያ አንዳንድ ሐሳቦችን ያካፍሉን ዘንድ ከዶክተር ሞገስ ይገዙ ጋር አጠር ያለ ውይይት አድርገናል።*

**ሐመር:–** *በትምህርት ክፍልዎ ሥር በቅርቡ የጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት እንደ ተከፈተ ይታወቃል። ስለመሆኑ የዚህ የጥናት ዘርፍ ዓላማው ምንድን ነው? እንዴትስ ሊከፈት ቻለ?*

**ዶ.ር ሞገስ:–** የጥናት ዘርፉ ከስሙ ለመገንዘብ እንደ ሚቻለው ጥንታውያን ጽሑፎችን መሠረት አድርጐ የሚከናወን ጥናት ነው። ለምሳሌ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች፣ በብራና ላይ የተጻፉ ጽሑፎች ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህን መርሐ ግብር ለመክፈት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ካሉ የሥነ ልሳን ምሁራን በኩል ምኞቱና ፍላጐቱ ነበር። ይሁን እንጂ ምኞቱና ፍላጐቱ ይኑር እንጂ መርሐ ግብሩን ለመክፈት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች አልነበሩም። በአለፉት ሁለት ዓመታት ግን ውሳኔውን አጠናክረን በመያዛችንና በመንቀሳቀሳችን ሊከፈት ችሏል።

**ሐመር:–** *የትምህርት ክፍሉ መከፈት ለእኛ ሀገር የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?*

**ዶ.ር ሞገስ:–** የጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት ለእንደኛ ዓይነቶቹ ጥንታውያን ሀገራት ሰፊ ጥቅም ይሰጣል። ሀገራችን በዓለም ላይ የደለበ ታሪክ፣ ቅርስና ትውፊት ካላቸው ሀገራት በግንባር ቀደምነት ትሰለፋለች። በመዛግብት ደረጃ እንኳን ብንመለከት በቀደሙ አባቶቻችን በብራና ተጽፈው በየ ቅዱሳት መካናቱ፣ በየግለሰቦች እጅ፣ በየአብያተ መጻሕፍቱ ወዘተ ይገኛሉ። መዛግብትን በመጻፍና በማከማቸት በእኛ ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የ2000 ዘመናት ታሪክ እንዳላት እናውቃለን። ታድያ እነዚህንም ሆነ ሌሎችን ጥንታውያን መዛግብት በሚመለከት እስከ አሁን የተሠራው ሥራ፤ ምንም እንኳን በተለያዩ ምክንያቶች የጠፉትና እየጠፉ ያሉት በርካታ ቢሆኑም፤ በተቻለ መጠን ጠብቆ ለትውልድ የማቆየት ሥራ ብቻ ነበር። ይህ በራሱ ታላቅ አስተዋፅዖ ሆኖ፤ የጐደለው አንድ ነገር ነበረው ለማለት ይቻላል። ይኸውም መዛግብቱ የያዙትን ፍሬ ነገር በመልክ በመልኩ አደራጅቶ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ ሌሎች ፍላጐቱ



www.eotcmk.org

ያላቸው እንዲያውቋቸው ማድረግ ነው:: መዛግብቱን ስናያቸው በብዛት ሃይማኖታዊ ይዘት አላቸው:: ነገር ግን ጠጋ ብለን ሞያዊ በሆነ መንገድ ስንመለከታቸው በእነዚህ መዛግብቶቻችን ውስጥ የሚያስደንቀና የሚያስመኩ የሞራል፣ የፍልስፍና፣ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የጊዜውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እውነታዎች የሚያሳዩ ጽንሰ ሐሳቦችን እናገኛለን:: በመሆኑም እነዚህንና የመሳሰሉትን ሀገር በቀል ዕውቀቶች (indigenous knowledge) ወደ ኢትዮጵያውያንና ወደ ዓለም ሕዝቦች ለማውጣት ይህ ዓይነት የጥናት መስክ ጠቃሚ ነው::

እስከ አሁን የነበረውን ሁኔታ ስንመለከት በመዛግብቶቻችን ጥናት ላይ ተሰማርተው የነበሩት፣ ባካሄዷቸው ጥናቶች አካዳሚያዊ ዕድገቶች ሲያገኙ የነበሩት ምዕራባውያን ነበሩ:: ምንም እንኳን አንዳንድ የተጉ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ቢኖሩም በብዛት በእኛ ብራናዎች ተምረው፣ ስለ እኛ ብራናዎች ይዘትና ቅርጽ የሚነግሩን እነዚሁ ሰዎች ነበሩና:: በእውነቱ ለጥንታውያን መዛግብቶቻችን ባይተዋሮች ነበርን ማለት ይቻላል:: ከአሁን በኋላ ግን ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ÷ ኢትዮጵያውያን ባለሞያዎች ያስፈልጉናል:: በአስተርጓሚ ሳይሆን በራሳቸው ሀገር ቋንቋዎች የተጻፉትን መዛግብት መርምረው ኢትዮጵያዊውን ዕውቀት በመልክ በመልኩ የሚያሳውቁን ሊቃውንት ያስፈልጉናል:: ለዚህ ደግሞ የጥናት ዘርፉ መከፈት ኹነኛ መንገድ ይመስለኛል::

**ሐመር፡-** *የመርሐ ግብሩ መከፈት በሀገሪቱ የቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት እየተዘነጋ ለመጣው የግእዝ ቋንቋ ትንሣኤ ነው ለማለት ይቻል ይሆን?*

**ዶ.ር ሞገስ፡-** ሊባል የሚችል ይመስለኛል:: ምክንያቱም የእኛ የጥንታውያን ጽሑፎች (Philology) ሀብት ሁለት ዓይነት ነው:: አንደኛው በግእዝ ቋንቋችን የተጻፉት ጥንታውያን ጽሑፎች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ በጥንታዊው የዐረብኛ ቋንቋ የተጻፉት ናቸው:: በኢትዮጵያ ደረጃ በጥንታውያን ጽሑፎች ረገድ አመዛኙ ሀብታችን በግእዝ ቋንቋችን የተቀረሰው የሥነ ጽሑፍ ሀብታችን ነው:: በዚህ ቋንቋ የሀገራችን እምነት፣ ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ወዘተ በሰፊው ተዘግቦ ተቀምጧል:: የግእዝን ያህልም ባይሆን በዐረብኛ ቋንቋም የተዘገቡ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወዘተ ታሪኮች አሉን:: በመሆኑም ቀዳሚ ትኩረታችንን በግእዝ ቋንቋ በተጻፉ መዛግብት ላይ እናደርግና በዐረብኛውም በሌላውም በተጻፉ መዛግብት ላይ ጥናትና ምርምር እናደርጋለን:: ስለዚህ አዎ÷ የዚህ ጥናት ዘርፍ መከፈት ለግእዝ ቋንቋ ተመልሶ ማንሠራራት በር ይከፍታል የሚል እምነት አለኝ::

**ሐመር፡-** *መርሐ ግብሩ ሲከፈት በቂ የግእዝ ቋንቋ ዕውቀት ያላቸው መምህራን በትምህርት ክፍሉ አሉ?*

**ዶ.ር ሞገስ፡-** ሁለት የግእዝ ቋንቋ ምሁራን አሉን:: አሁን ባለን እንቅስቃሴ በእውነቱ በመምህራን በኩል ችግር የለብንም:: ወደ ፊት ግን በእነዚህ መምህራን ብቻ ለመቀጠል የምንቸገር ይመስለኛል:: ምክንያቱም አሁን እንደ ምናየው ትምህርቱን የሚፈልጉ ሰዎች ቁጥር እየበዛ መጥቷል:: መርሐ ግብሩን ስንጀምር አምስት÷ ዐሥር ሰዎች ብናገኝ ብለን ነበር:: ነገር ግን የአመልካቾች ቁጥር ብዙ ስለነበር 17 ተማሪዎችን ያህል ለመቀበል ተገደናል:: እንደ ምንገምተው በሚቀጥለው ዓመትና በኋላ ወደ መርሐ ግብሩ የሚመጡ ተማሪዎች ቁጥር ይጨምራል:: በመሆኑም የመምህራንን ቁጥር እናበዛለን::

**ሐመር፡-** *የተማሪ መቀበያ መስፈርታችሁ ምንድን ነው?*

**ዶ.ር ሞገስ፡-** መስፈርታችን ከሌላው ለየት ይላል:: ይኸውም በቋንቋ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በሥነ ልሳንና በሥነ መለኮት የትምህርት ዘርፎች የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሆኖ የግእዝ እና/ወይም የዐረብኛ ቋንቋዎች ዕውቀት ያለው ማንኛውም ሰው አመልክቶ የመግቢያ ፈተና በመውሰድ ካለፈ ሊቀጥል ይችላል::

> **በመዛግብት ደረጃ እንኳን ብንመለከት በቀደሙ አባቶቻችን በብራና ተጽፈው በየቅዱሳት መካናቱ፣ በየግለሰቦች እጅ፣ በየአብያተ መጻሕፍቱ ወዘተ ይገኛሉ:: መዛግብትን በመጻፍና በማከማቸት በእኛ ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የ2000 ዘመናት ታሪክ እንዳላት እናውቃለን::**

**ሐመር፡-** *በአውሮፓ የግእዝ ጥናት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በጥናት ዘርፍነት ከተያዘ ቆይቷል:: ከዚህ አንጻር እኛ አልዘገየንም ይላሉ? ለምን?*

**ዶ.ር ሞገስ፡-** አዎ÷ ዘግይተናል:: ቅድም እንዳልኩት እስከ አሁን ጥቂት ኢትዮጵያውያን በዘርፉ መሰማራታቸውን ሳልዘነጋ ጥንታውያኑ መዛግብቶቻችን በሳይንሳዊ መንገድ ሲጠኑና ሲተነተኑ የነበሩት በምዕራባውያን ነበር:: ይህ የሆነበትን በርካታ ምክንያት ለመጠቃቀስ ቢቻልም ዋና ዋናዎቹ የባለሞያዎች እጥረት፣ የገንዘብ እጥረትና የግእዝ ቋንቋን ከሃይማኖት ጋር ብቻ የማያያዝ ችግሮች ናቸው:: የመጨረሻውን ምክንያት በሚመለከት በእኔ እምነት የግእዝ ቋንቋም ሆነ በግእዝ ቋንቋ የተጻፈ ብራና ሁሉ የኢትዮጵያውያን ነው:: በመሆኑም የጥናቱ መስፋፋት የሁላችንንም ይሁንታና ጥረት ማግኘት አለበት::

**ሐመር፡-** *ከመርሐ ግብሩ መከፈት ጋር ተያይዞ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያደረጋችሁት ግንኙነት ይኖራል?*

**ዶ.ር ሞገስ፡-** አለ:: እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አብዛኛዎቹን ቅርሶችን ጠብቃ ያቆየች ቤተ ክርስቲያን ናት:: በመሆኑም በዚህች ሀገር በጥንታዊ ታሪክም ይሁን በሥነ ጽሑፍ ጥናት የሚሰማራ ማንኛውም አካል ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ግንኙነት መፍጠር አለበት:: እኛም ግንኙነቱን ጀምረናል:: የጥናት መስኩን አስፈላጊነት በሚመለከት ደብዳቤ ጽፈውልናል:: ባለፈው ከጥቅምት 5 እስከ 7 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረግነው ዓለም አቀፍ ሲምፖዝየም ላይ ተገኝተው በሚደረገው ውይይት ላይ እንዲሳተፉ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን ጋብዘን ነበር:: እርሳቸው ሳይመቻቸው በመቅረቱ አንድ ተወካይ ልከውልናል:: በቅርቡም ጽ/ቤታቸው ድረስ በመሄድ አነጋግረናቸዋል:: ስለዚህ ለወደፊቱም ቢሆን በዚህ መልክ ከቤተ ክርስቲያኗ ጋር ያለንን ግንኙነት አጠናክረን እንቀጥላለን::

**ሐመር፡-** *ዶ.ር ሞገስ ይገዙ÷ በአ.አ.ዩ የሥነ ልሳን ትምህርት ክፍል ሓላፊ÷ ስለ ሰጡን ማብራሪያ በአንባብያን ስም እናመሰግናለን::*

**ዶ.ር ሞገስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ::



www.eotcmk.org

# መንገደኛው

ኃ/ገብርኤል ዘሐና

እንደ ምን ከረማችሁ? መንገደኛው እኔ እንደ ሄድኩ በመስከረም የተጀመረው ዓመት ተፈጽሞ ስንት መስከረም ተተካ? መስከረም የገንፎ ምንቸት ይዞህ ግባ ቢባልም የብርድ ምንቸት ይሆ ነው መሰለኝ የመጣው፥ ጠዋት ጠዋት የመንገደኛው አፍንጫ መቅለጥ ይዟል።

እማማ ባፈና ጎረቤቴ ናቸው። ጠላ ሸጠው ነው የሚተዳደሩት። ታድያ ደንበኞቻቸው ናቸው «ምንትስ ምን ሳይል» በር የሚያስከፍታቸው ትጋታቸው አስቀናኝ። እኔ መንገደኛው ግን ለመጠጣት መትጋት፣ ለመስከር መትጋት ሆል ተግባሬ። ለመጠጣት ካልተጋሁ ዐይኖቼ፣ እጆቼ ... ሌሎቹም ሕዋሳት ሥራቸውን ያቆማሉ።

መንገደኛው እኔም ልብ ገዛኹና እማማ ባፈናን ተቀላቀልኳቸው። ምናልባት የእማማ ባፈና አረቄ ለሚቀልጠው አፍንጫዬ መድኃኒት ቢሆነኝ ብዬ። ከአረቄው ይልቅ ወጉ «ጉድ» ነው። የእንግሊዘኛውም የአማርኛውም «ጉድ» በሉት በቃ ሁሉንም ይሆናል። ዓለም፣ ኢትዮጵያ፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ጤና፣ ግብርና፣ ትምህርት~~፣ ትዳር~~፣ ቤተ ክርስቲያን ሁሉም በእማማ ባፈና ቤት ይነበባል፣ ይተረካል፣ ይተረጎማል፣ ይመሠጠራል። የእማማ ባፈናን ቤት የፕረስ ሕግ አያውቀውም። ኢኒጋማ፣ ዋልታ፣ ኢ.ዜ.አ፣ ፋና ወይም ቢቢሲ ሌላም ... ኸረ ኤዲያ፥ በቃ፥ መንገደኛውና «ትጉዎቹ» ብቻ ናቸው የሚያውቁት።

የጥንት የጠዋቱ ደንበኛ መንገደኛውን የጎሪጥ እያየ፦ "ትላንት ጊዮርጊስ ሄጄ ..." አለ። «የትኛው?» የቢጠዎቹ ጥያቄ ነበር። «የአራዳው ነዋ! ፋራው መሰለህ?» ከዚያስ? የነዚህ ቅዱሳን ጊመዶቼ ከተማ ፈርሶ፥ እነርሱም ተሰደው፥ ሁሉም ወና ሆኖ አገኘሁት። ለእኔ ለመንገደኛው አልገባኝም። የእነርሱን ወግ ለመረዳት «ከእነርሱ ት/ቤት» መመረቅ ያስፈልጋል። ከጥግ ያለው ጓደኛው "እንኳን ቅዱሳን ዘመዶች..... የለህም!!" አለው። አንተ ደግሞ ሰው አትናቅ፣ የናቅኸው ኋላ ይንቅሃል፣ ጊዮርጊስ ጓሮ የተቀበሩት ሰዎች በሰውነት ዘመዶቼ አይደሉም? ከተማቸውስ መካነ መቃብራቸው አይደለምን? አሁንስ መታረሱን አላየህም?

መንገደኛው ልቤ ተንጠለጠለ። ሌላኛው ቀጠለ። «እባክህ ተው፥ ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል አሉ። የቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች ሞኞች ስለሆኑ ነው እንጂ የማን መካነ መቃብር ተነካና ነው?» ሁለተኛው ቀጠለ። «ታድያ ቄሶች ቦታውን በቁጠባ ካልተጠቀሙበት፣ በንጽሕና ካልያዙት የአፍሪካ መዲና የሆነችውን አዲስ አበባ በመካነ መቃብር ለዚያውም ንጽሕና በሌለው ሊሞሏት ነው?» ሦስተኛው ሠለሰ። «እባክህ ዐቅም ግንባታ ቦታውን እየሸጠ ዐቅሙን ሊገነባ ነው አሉ።»... ሁሉም ያለ ገደብ የመሰለውን ተናገረ። ያልተናገረው መንገደኛው ብቻ ነው። የሚናገረው ጠፍቶ ሳይሆን መልስ የሚመልስለት አጥቶ። እውነትም የመቃብር ቦታዎች ስለ ምን ታረሱ? ስለ ምን ፈለሱ? መንገደኛው ልቤ መራኝ፥ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ወደ ቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን። ሌሎቹን እናንተ ሂዱባቸው። የመቃብር ቦታዎቹ ለምን ታረሱ? የከተማውን ውበት ለመጠበቅ? የቦታን ጥበት ለመቀነስ? ማንስ ነው የቆፈራቸው? አጥንታቸውስ የት ደረሰ? የአባታችን ያዕቆብን ዐፅም ተሸክሞ አርባ ዓመት የተንከራተተው ሙሴ ምን አለ? መንገደኛው ልቤ የመሰለውን መላ ምት ደረደረልኝ። ይሁን እንጂ በዚያው ልቤ ደግሞ ሌላ ጥያቄ ይፈጠርብኛል።

የመቃብር ቦታዎቹ በአግባቡ ካለመያዛቸው የተነሣ የከተማይቱን ውበት ቀንሰዋል፣ የአጠቃቀም ችግር አለባቸው። ስለዚህ ታርሰው ወደ መናፈሻነት መለወጥ አለባቸው። ይህንም አስተዳደሩ በተሰጠው ሓላፊነትና ተግባር መሠረት ቦታዎቹን መረከብ አለበት። ግን ለምን? የመንገደኛው ውስጣዊ ልቡና ያፈለቀው ጥያቄ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ማልማት አትችልም ወይ? እንደሚታየው የመቃብር ቦታዎቹ የአጠቃቀምና የአያያዝ ችግር አለባቸው። ያለው አጠቃቀም የቦታ ጥበትን ችግር ያስከትላል። የአያያዙ ጉዳይ በእጅጉ ንጽሕና የለውም። ስለዚህ እነዚህ ችግሮች የመቃብር ቦታዎቹን ከቤተ ክርስቲያኒቱ እንዲወሰዱ በቂ ምክንያቶች ናቸው ወይ? መንገደኛው ልቤ ሄደ፥ ቀጠለ።

የአጠቃቀምና የአያያዝ ችግር በመመሪያና በቁጥጥር የሚስተካከል ጉዳይ ነው። የእምነት ድርጅቶች የያዙአቸውን ቦታዎች እንዴት ይጠቀሙበት? መንግሥትን የሚመለከት ነው። መመሪያው ከመጣስ በኋላ በአግባቡ ሊጠቀምበት በማይችሉት ላይ ምን ይደረግ? ይህም ውሳኔ የሚያስፈልገው ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ ማንኛውንም የልማት ሥራ ሊሠራ የሚችል 40 ሚሊዮን ምእመናንን ይዛ፣ ዕውቀት፣ ገንዘብ፣ የሰው ኃይል እንደ ሌላት ተቆጥራ በቅዱስ መስቀል ባርካ ያረፉትን የልጆቿን ሥጋ የምታሳርፍበትን ቦታ ለመንጠቅ ማሰብ ግን መንገደኛውና ቢጤዎቻችን ጥርጣሬ እንዲገባቸው አድርጓል።

አሜሪካ "አሸባሪዎች" ያለቻቸው የኢራቅ ተዋጊዎች የተሰበሰቡበትን መካነ መቃብር አክብራ ባላት መሣሪያ ተዋጊዎቹን ከነ መቃብሩ ከማፈራረስ ስትጠበቅ፦ "የእኛዎቹ" በዶዘር መቃብራችንን ማለትም የአባቶቻችንን ዐፅም ሲሰባብሩት ምን ይባላል? ወይስ በቃ የእማማ ባፈና ደንበኞች እንደ ተናገሩት መንግሥት "ዐቅማችንን ሊገነባ የሚችል ማንኛውንም ነገር ካገኘን ከመቀማት ወደ ኋላ አንልም" የሚል ዐቋም ይዞ ነው? መንገደኛው መልስ አላገኘም። መልሱን ግን ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት ወልዳ ካሳደገቻቸው ምእመናን ይፈልጋል። ለቤተ ክርስቲያን የመቃብር ቦታዎች ዘመናዊ አጠቃቀምንና መልካም አያያዝን መፍጠር አይቻልም ወይስ ቤተ ክርስቲያን በሕግና በመመሪያ መሠረት የከተማዋን ዕድገትና ውበት ሊጠብቅ የሚችል የመቃብር ቦታ አጠቃቀምን በተማሩ ልጆቿ እንዳትመራ የሚከለክላት የሕግ አንቀጽ ይኖር ይሆን? ለዛሬው በቃኝ። በቸር ያሰንብተን። አሜን።


አዲስ መጽሐፍ
የገሃነም ደጆች
በቅርብ ቀን በሥርጭት ላይ ይውላል
አዘጋጅ፦ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
አዲስ የቪድዮ እና ኦድዮ የካሴት ትምህርት
በሥርጭት ላይ ውሏል
ለጌታ ያስፈልጉታል
በዲ/ን ያረጋል አበጋዝ
አዘጋጅ፦ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
በሐመር መጽሔትና በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ
ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኙታል
ስልክ 22 86 01/ 23 45 30
ቁጥር ሁለት የኦሮምኛ መጽሐፍ
ፍኖተ አሚን
/የእምነት መንገድ/
ተዘጋጅቶ በሥርጭት ላይ ውሏል መጽሐፉ በውስጥ ይዘቱ፦
- ጸሎትን አስመልክቶ
⇨ ጸሎት ምንድን ነው?
⇨ የጸሎት ዓይነቶች
⇨ የጸሎት ጊዜያት
⇨ ለምን እንጸልያለን?
⇨ ጸሎት ለምን፣ መቼና የት? ሌሎችንም
- ምጽዋትን አስመልክቶም
⇨ የምጽዋት ትርጉም
⇨ የምጽዋት ጥቅም
⇨ የምጽዋት አፈጻጸም ሌሎችንም
በውስጡ አካትቶ ይዟል።
ዋጋ - ብር 5.00
አሳታሚና አከፋፋይ - ማኅበረ ቅዱሳን
ቁጥር አንድንም በማኅበረ ቅዱሳን
ማከፋፈያ ሱቆች ያገኛሉ
በማኅበረ ቅዱሳን የንዋያተ ቅድሳት
ማምረቻና ማከፋፈያ
▪ የካህናት አልባሳት
▪ የመዘምራን ልብስ
▪ ጧፍ፣ ዕጣን፣ ዘቢብ
▪ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች አልባሳት
▪ በተክሊል ለሚጋቡ ሙሽሮች የካባ ኪራይ
▪ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት
የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓት ጠብቀን፣ ቀጠሮ አክብረን በተመጣጣኝ ዋጋ
በጥራት እንድናዘጋጅልዎ ይጎብኙን።
አድራሻ፦
☎ 56 67 88/11 48 70/23 45 30 ✉ 80078 አ.አ.
ሜጋ ማተሚያ ድርጅት
ዋጋ ብር 3.50

'

©

!"  #$  %

& '  (  )  *  $++